በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና አዛኝ በሆነው፡፡ ምስጋና ለአላህ ይግባው ለዓለማት ጌታ ለሆነው፡፡ የአላህ (ሱ.ወ) እዝነት እና ሰላም በተከበሩት ነብዩ ሙሐመድ፣ በቤተሰቦቻቸው እንዲሁም በባልደረቦቻቸው ላይ ይስፈን፡፡

## ***<u>መግቢያ</u>***

ስለ ነብዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) ስንናገር በዚህ ዘመንም ይሁን ባለፈው ግዜ ተሰምቶ ስለማይታወቅ የታላቅ ስብዕና ባለቤት መሆኑን መገንዘብ ይኖርብሀል፡፡ ይህ ፍርድ ከስሜትና ካለማስረጃ የመነጨ አይደለም፡፡ የሕይወት ታሪካቸውን ከጭፍን ሀይማኖታዊ አስተሳሰብ በራቀ መልኩ አንብቦ ስነምግባራቸውን እና ባህሪያቸውን የተረዳ ሰው ከላይ ለሰጠነው ፍርድ ትክክለኛነት ምስክር ይሆናል፡፡ በእርግጥም ሙስሊም ያልሆኑ ፍትሀዊ ሰዎች እዚህ ላይ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፡፡

ኡስታዝ ሀሰን አልይ(ረሂመሁላህ) ‘ኑረል ኢስላም’ በሚለው መፅሄት ላይ እንዲህ ይላሉ፡- አንድ የ‘ብራህሚን’ ሀይማኖት ተከታይ የሆነ ጓደኛቸው እንዲህ አላቸው፡- “እኔ የእስላም ነብይ አለም ላይ ካሉ ሰዎች ሁሉ ምሉዕ እና ታላቅ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡”

ኡስታዝ ሀሰን፡- አንተ ዘንድ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) አለም ላይ ካሉ ሰዎች ሁሉ ምሉዕ ሊሆኑበት ያቻሉበት ምክንያት ምንድን ነው?

ብራህሚኑ ጓደኛቸው፡- ምክንያቱም አለም ላይ ባሉ ሰዎች ላይ አይቼ የማላውቀውን ታላቅ ስብዕና በእሱ ላይ ስላየሁ እና በተመሣሣይ ግዜ በአንድ ሰው ላይ ተሰብስበው የማያውቁ የብዙ ዘርፎችን ክህሎት በእሱ ላይ ስላገኘሁ ነው፡፡ የፈለገውን ነገር መስራት በሚያስችለው መልኩ ሀገራቶች ሁሉ እጃቸውን የሰጡት ታላቅ ንጉስ ነበር፡፡ ይህ ከመሆኑም ጋር እሱ ግን በራሱ ምንም ማድረግ እንደማይችልና ነገራቶች ሁሉ በጌታው እጅ መሆኑን የሚያምንና መተናነስን የሚያበዛ ሰው ነበር፡፡ አክብሮታዊ የሆኑ ገንዘቦች በካዝና እየሆኑ የሚኖርበት ከተማ ድረስ የሚመጡለት ታላቅ ሀብታም ሆኖ ታየዋለህ፥ ነገር ግን የሚቸግረውና ርሀብ ላይ በሚጥለው መልኩ ቤቱ ውስጥ ለወራት እሳት ሳይነድ ያልፋሉ፡፡ ታላቅ የጦር መሪ ሆኖ ታየዋለህ፤ በቁጥር ትንሽ በመሣሪያም ደካማ የሆነ ሰራዊት ይዞ ብዛታቸው በብዙ ሺሀ የሚቆጠሩ እና በከፈተኛ ጦር መሳሪያ የታጠቁ ሰራዊቶችን አስከፊ በሆነ መልኩ ያንበረክካቸዋል፡፡ ሰላም ወዳጅ እና ተስማምቶ መኖርን የሚመርጥ ሰው ሆኖ ታገኘዋለህ፡፡ መዋጋት በሚችልበት ሁኔታና ከጎኑ ብዙ ሺ ባልደረቦች እያሉ እሱ ግን በእርጋታ መንፈስ እና ለጠላቶቹ መመራትን በመመኘት የጦር አቋም ድርድር ሲፈራረም ታየዋለህ፡፡ ባልደረቦቹ ደግሞ እያንዳንዳቸው ጀግና ደፋር፣ ጠንካራ እና የማያፈገፍግ አንዱ ብቻውን ለሺ ጠላት የሚበቃ አይነት ነበሩ፡፡ ይህ ከመሆኑም ጋር ልቡ የሚራራ፣ አዛኝ እና ጠብታ ደም ከማፍሰስ የተጠበቀ ሰው ነበር፡፡ በአረብ ምድረ ሰላጤ ስላሉት ሁሉ በማሰብ ተጠምዶ ታየዋለህ፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ግን ስለቤቱ፣ ስለሚስቶቹ፣ ስለልጆቹ፣ እንዲሁም ስለ ሚስኪኖች እና ስለደሀዎች ጉዳይ ምንም ነገር አያመልጠውም፡፡ ጌታቸውን ረስተው ከሱ ስለራቁ ሰዎች ጉዳይ ይጨናቃል፡፡ እነዚህ ሰዎች እንዲስተካከሉለት ይጓጓል፡፡ በአጠቃላይ አለም ላይ ስላለ ነገር ሁሉ የሚያስብ ሰው ነው፡፡ ይህ ከመሆኑም ጋር ከዱንያ ተቆራርጦ ፊቱን ወደ አላህ ያዞረ ሰው ነው፡፡ እዚህ አለም ላይ ሆኖ የሌለ ሰው ነው፡፡ ምክንያቱም ልቡ አላህን ከሚያስተደስቱ ነገሮች ውጭ ተገናኝቶ ስለማያውቅ ነው፡፡ ስለራሱ ብሎ አንድን ሰው ተበቅሎ አያውቅም እንደውም ለጠላቶቹ ጥሩን ነገር ዱዓ የሚያደርግና የሚመኝ ሰው ነበር፡፡ የአላህን(ሰ.ወ) ጠላቶች ግን ይቅር አይላቸውም፤ አይተዋቸውምም። ከአላህ መንገድ ያፈነገጡ ሰዎችን ከመምከርና

በጀሀነም ቅጣት ከማስጠንቀቅ ተወግዶ አያውቅም፡፡ በዱንያም ጉዳይ ላይ ግድ የለሽ፤ አላህን ለማስታወስ እና ለማዋየት ሌሊቱን ሲሰግድ የሚያድር ሆኖ ታየዋለሁ፡፡ ከባህሪያቶቹ ውስጥ ጀግና ወታደር፥ በሰይፍ የሚጋደል የሚሉትን እንደምታገኝ ሁሉ አስተዋይና ጠንቃቃ መልዕክተኛ እና ጥብቅ ነብይ የሚሉትን ታገኛለህ፡፡ አገራቶችን በድል የሚከፍት፣ አምባገነኖችን የሚደመስስ መሆኑን እያይህ ሳለ ከተምር ዛፍ ቅጠል በተሰራ ሰሌን ላይ በገለባ ከተጠቀጠቀ ትራስ ላይ ተኝቶ ታገኘዋለህ፡፡ ይህ ሰውማ የአረብ ንጉስ ነው ብለህ ስታስብ ታላላቅ ገንዘቦች ከአረም ምድረ ሰላጤ እየጎረፈለት ባለበት ወቅት እሱና ቤተሰቦቹ ግን ርሀብ እና ችግር ውስጥ ታገኛቸዋለህ፡፡ የመጣው ሀብት መስጂድ ውስጥ ተቆልሎ እንዲሁም በጦርነት የተማረኩ አገልጋዮችን ጭምር ለሙስሊሞች እያከፋፈሉ ባሉበት ሰዓት የዐይናቸው ማረፊያ፣ ያብራካቸው ክፍያ የሆነችው ልጃቸው ፈጢማ(ረ.ዐ) ሰውነቷ እስኪጎዳ ድረስ እየተሸከመች እንደሆነ እንዲሁም እጇ እስኪላጥ ድረስ በድንጋይ ወፍጮ እየፈጨች እንደሆነ ባጠቃላይ የቤት ውስጥ ስራ ስለከበዳት አገልጋይ እንዲሰጧት በጠየቀች ጊዜ ብርታቱን እንዲሰጣት አላህን የምትለምንበት ቃላት ብቻ አስተምረው ነው የሸኟት፡፡

አንድ ቀን ወዳጃቸው ኡመር(ረ.ዐ) ቤታቸው መጥቶ ቢያማትር ያየው ነገር ቢኖር ጋደም ያሉበትና ሰውነታቸው ላይ ምልክት ያሳረፈው ከቅርጫት የተሰራ ሰሌን፣ በእቃ የተቀመጠ አንድ ቁና ገብስ እና ግድግዳ ላይ የተንጠለጠለች ውሃ መያዣ እቃ ናቸው፡፡ ግማሹን የአረብ ግዛት በተቆጣጠሩበት ወቅት እንኳን የሳቸው ሀብት ይህ ብቻ ነበር። ዑመር(ረ.ዐ) ይህንን ያየ ጊዜ አይኖቹ እንባውን መቆጣጠር አልቻሉም፡፡ ረሱልም(ሰ.ዐ.ወ) "አንተ ዑመር ሆይ! ምንድነው የሚያስለቅስህ?" ብለው ጠየቁት፡፡ ዑመርም(ረ.ዐ) "ቄሳር እና ኪስራ በዱንያ ፀጋ እየተንደላቀቁ የአላህ መልዕክተኛ ሀብት ግን የማያቸው ነገራቶች ብቻ ሲሆኑ እንዴት አላለቅስም?" ረሱልም(ሰ.ዐ.ወ) "አንተ ዑመር ሆይ የቄሳር እና ኪሳራ እጣ የዱንያ ፀጋ ሆኖ ለኛ ደግሞ ከሰዎች በተለየ መልኩ የመጪው አለም ፀጋ ቢሆን አትወድምን?!"

ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ከነጦር ሰራዊታቸው መካን በድል ሊከፍቱ ዙሪያዋን በከበቧት ጊዜ አቡሱፊያን እና የነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) አጎት አባስ(ረ.ዐ) አንድ ላይ ሆነው የሙስሊሙን ሰራዊት ይመለከታሉ፤ የዚያን ጊዜ አቡሱፊያን አልሰለመም ነበርና የሙስሊሞችን ብዛትና አብሯቸው የመጣውን የአረብ ጎሳ ብዛት ግድብ እንደማይመልሰው ጎርፍ በመካ መግቢያ ላይ እየተጋፋ ሲያይ ለአባስ፦ "አንተ አባስ ሆይ ዛሬ እኮ የወንድምህ ልጅ ትልቅ ንጉስ ሆኗል" አለው። አባስም "ይህ ጉዳይ የንግስና ሳይሆን የነብይነት ጉዳይ ነው" ሲል መለሰለት፡፡

በቸርነቱ ታዋቂ የሆነው እና የጠይ ጎሳ መሪ የነበረው አዲይ ኢብኑ ሀቲም በክርስትና ሀይማኖት ላይ በነበረበት ጊዜ የነብዩን ታላላቅ ሰሀቦች መሳሪያ ታጥቀው ባያቸው ጊዜ ይህ ሰው ነብይ ነው ወይስ የጦር መሪ እያለ እራሱን ይጠይቅ ገባ፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለ አንዲት አገልጋይ የሆነች ደሀ ሴት ወደ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ ትመጣና "ያረሱለላህ! ያማዋይህ ሚስጥር አለኝ" ትላቸዋለች፡፡ እሳቸውም "ከመዲና ጎዳናዎች የፈለግሽውን ስፍራ ምረጭ እና ልትነግሪኝ ትችያለሽ" አሏት፡፡ ከዛም ከሷ ጋር ሄደው ችግሯን ፈትተውላት ተመለሱ፡፡ በባልደረቦቻቸው ዘንድ እንደ ንጉስ የሚታዩን የረሱል (ሰ.ዐ.ወ) መተናነስ እና ትህትና ኢዲይ አብኑ ሀቲም በተመለከተ ግዜ የነበረበት ጨለማ ተገለጠለት፡፡ እውነት ግልፅ ብላ ታየችው፡፡ ይህ ጉዳይ የነብይነት ጉዳይ መሆኑን እርግጠኛ ሆነ፡፡ መስቀሉን አውልቆ ከረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ባልደረቦች ጋር የእስልምናን ብርሃን ተቀላቀለ፡፡

ምስራቃውያኖች ስለረሱል (ሰ.ዐ.ወ) የተናገሩትን ንግግሮች መሀል መሀል ላይ ጠቅሻለሁ፡፡ ለኛ እንደሙስሊምነታችን የሙሐመድን(ሰ.ዐ.ወ) መልዕክተኛነት ለመረዳት የእነሱ ንግግር አያስፈልገንም። ነገር ግን ለሚከተሉት 2 ምክንያቶች ስል ለመጥቀስ ተገድጃለሁ፡፡

1ኛ. ከእስልምና ስሙን እንጂ ሌላን የማያውቁ ሙስሊሞች፥ ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎች እነሱ ስለረሱት ነብያቸው የሚናገሩትን ነገር ሰምተው ወደ ትክክለኛው መስመር ይገባሉ በሚል፤

2ኛ. ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎች እንዲያነቡት እና ከራሳቸው ወገን ሰዎች አፍ ስለዚህ ታላቅ ነብይ ደረጃ እና ሁኔታ እንዲረዱ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ወደ እስልምና እንዲገቡ አልያም ስለእስልምና ማጥናት እንዲጀምሩ ምክንያት ሊሆናቸው ይችላል። ለእነዚህ ሰዎች የምመክረው ነገር እራሳቸውን ከወገንተኝነት ካፀዱ እውነትን ከውሸት፣ ትክክለኛን ከስህተት መለየት የሚችሉበት አዕምሮ ስላላቸው በሌላ ሰው አስተሳሰብ በጭፍን እንዳይመሩ ነው፡፡ ለነዚህ ሰዎች ጌታዬን የምለምነው አላህ ልባቸውን ለእውነት ከፍቶት ወደ እርሱ እና ወደቀጥተኛው መንገድ እንዲመራቸው ነው፡፡

ዶ/ር አብዱራህማን ቢን አብዱልከሪም አሸይሀ

alsheha@yahoo.com

WWW.islamland.org

# ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ማን ናቸው?

## የዘር ሀረጋቸው

አብልቃሲም ሙሐመድ ቢን አብዱላህ ቢን አብዱል ሙጠሊብ.... እያለ እስከ የነብዩ ኢስማዒል(ዐ.ሰ) ልጅ የሆነው አድናን ይደርሳል፡፡ ነብዩ ኢስማዒል(ዐ.ሰ) ደግሞ የአላህ(ሱ.ወ) ወዳጅ የሆኑት የነብዩ ኢብራሂም(ዐ.ሰ) ልጅ ናቸው፡፡ እናታቸው ደግሞ አሚና ቢንት ወሀብ ስትሆን ዘር ግንዷም ወደ የኢስማዒል(ዐ.ሰ) ልጅ አድናን ይደርሳል፡፡

ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ "አላህ(ሱ.ወ) ከኢስማኢል ልጆች ውስጥ ኪናናን መረጠ፡፡ ከኪናና ውስጥ ደግሞ ቁረይሽን መረጠ ከቁረይሽ ውስጥ ደግሞ በኒ ሀሽምን መረጠ፡፡ ከበኒ ሀሽም ውስጥ ደግሞ እኔን መረጠ(ሰሒህ ሙስሊም)። በዚህም አማካኝነት መሬት ላይ ካሉት የዘር ሀረጎች ውስጥ ምርጡ የሳቸው ነው፡፡ ይህ ስለመሆኑም ጠላት እንኳን መስክሮላቸዋል፡፡ ከመስለሙ በፊት የጠላቶቻቸው ዋና የነበረው አቡሱፍያን(ረ.ዐ) እንኳን የሩም መሪ ከነበረው ሂረቅል ፊት ቆሞ በዚህ ላይ ምስክርነት ሰጥቷል፡፡ አብደላህ ኢብን አባስ እንዳስተላለፉት፡- በአንድ ግዜ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ቄሳር እስልምናን እንዲቀበል ደብዳቤ ፅፈው ደሂየተል ከልቢን ይልኩታል፡፡ እሱም ለበስራው አስተዳዳሪ ሰጥቶት እሱ ደግሞ ለዋናው ቄሳር እንዲሰጠው ነግረው ይልኩታል፡፡ በዚያን ግዜ ቄሳሩ የፋርሶችን ጦር አሸንፎ ስለነበር ደስታውን ለማክበር ከሒምስ ተነስቶ ወደ እየሩሳሌም ሄዶ ነበር፡፡ የነብዩን(ሰ.ዐ.ወ) ደብዳቤ ካነበበ በኋላ "ስለዚህ ነብይ የምጠይቀው ከሱ ወገን የሆኑ ሰዎችን ፈልጉና አምጡልኝ" አለ፡፡ ኢብኑ አባስ (ረ.ዐ) አቡሱፉያን እንዲህ ብሎኛል ይላሉ "በቁረይሽ እና በረሱል(ሰ.ዐ.ወ) የጦር አቁም ስምምነት ወቅት ወደ ሻም(ሶሪያ) ከተወሰኑ የቁረይሽ ሰዎች ጋር ሂጄ ነበር፡፡ የቄሳር ወታደሮች በሻም ውስጥ አግኝተውኝ እኔንና የተወሰኑ ጓደኞቼን ወደ እየሩሳሌም ወሰዱን፡፡ ቤተመንግስቱ ውስጥ ስንገባ ቄሳርን በዙፋኑ ላይ ከነሙሉ ግርማ ሞገስ ተቀምጦ፤ እንዲሁም በዙሪያው አማካሪዎቹ ተደርድረው እየጠበቁን ነበር፡፡ ቄሳሩ ለአስተርጓሚው "ነብይ ነኝ ለሚለው ሰው በዝምድና ማን ቅርብ እንደሆነ ጠይቅ" አለው፡፡

አቡሱፍያንም፡- "እዚህ ካለነው ለሱ ቅርብ የሆንኩት እኔ ነኝ" አለ፡፡

ቄሳሩ፡- "በመካከላችሁ ያለው ዝምድና ምንድነው?"

አቡሱፍያን፡- የአጎቴ ልጅ ነው (በዚያን ሰዓት ከአቡሱፍያን ውጪ ከበኒ አብዲመናፋ ጎሳ የሆነ ሰው አልነበረም)

ቄሳሩ፡- ወደእኔ ቀረብ በል። (ጓደኞቹንም ከትከሻው ጀርባ እንዲቆሙ አዘዘ) ለጓደኞቹም "እኔ ስለዚህ ነብይ ነኝ ስላለው ሰው እጠይቀዋለሁ፡፡ ውሸት የሚያወራ ከሆነ ምልክተ ስጡኝ" አላቸው፡፡ (አቡሱፍያን፡- "በአላህ ይሁንብኝ ጓደኞቼ ውሸታም ይሉኛል ብዬ ባልፈራ ኖሮ ስለነብዩ ስጠይቀኝ እዋሸው ነበር፡፡" ብሏል)

ቄሳሩ፡- ይህ ሰው በናንተ ውስጥ የዘር ሐረጉ እንዴት ነው?

አቡሱፈያን፡- የሱ ጎሣ የታወቀ እና የተከበረ ነው፡፡

ቄሳሩ፡- ከናንተ ውስጥ ከዚህ በፊት እንዲህ አይነት ነገር የተናገረ ሰው አለ?

አቡሱፈያን፡- የለም

ቄሳሩ፡- ይህን ነገር ከመናገሩ በፊት በውሸት ጠርጥራችሁት ታውቃላችሁ

አቡሱፈያን፡- አናውቅም

ቄሳሩ፡- ከአባቶቹ መሀል ንጉስ የነበረ ሰው አለ?

አቡሱፈያን፡- የለም

ቄሳሩ፡- የሚከተሉት ሰዎች መሪዎችና የተከበሩ ናቸው ወይስ ደካማና ድሃዎች?

አቡሱፈያን፡- ደካማዎች ናቸው።

ቄሳሩ፡- ቁጥራቸው እየጨመረ ነው ወይስ እየቀነሰ?

አቡሱፊያን፡- ኧረ እየጨመረ ነው፡፡

ቄሳሩ፡ ሀይማኖቱን ከተቀላቀለ በኋላ ጠልቶት ተመልሶ የወጣ ሰው አለን?

አቡሱፊያን፡- የለም

ቄሳሩ፡- ቃሉን አፍርሶ ያውቃል?

አቡሱፊያን፡- አያውቅም፡፡ ነገር ግን አሁን ያለነው በስምምነት ወቅት ነው፡፡ በዚህ ላይ ይከዳናል የሚል ፍራቻ አለን፡፡ (ነብዩ ላይ መጥፎ ለመናገር ያገኘሁት እድል ይህች ብቻ ናት)

ቄሳሩ፡- ጦርነት አካሂዳችሁ ታውቃላቹ?

አቡሱፊያን፡- አዎን

ቄሳሩ፡- የጦርነቱ ውጤት ምን ይመስል ነበር?

አቡሱፊያን፡- በመካከላችን የተካሄደው ጦርነት አንዴ ለሱ ሲሆን ሌላ ግዜ ደግሞ ለኛ ሆኗል፡፡

ቄሳሩ፡- በምንድነው የሚያዛችሁ?

አቡሱፊያን፡- አላህን በብቸኝነት በሱ ምንንም ሳናጋራ እንድናመልክ፤ አባቶቻችን የሚያመልኩትን ነገር እንድንተው ያዘናል፡፡ ሰላትን እንድንሰግድ፣ ሰደቃ እንድናወጣ፣ ጥብቅ እንድሆን፣ ቃላችንን እንድናከበር እና አደራን እንድንመልስ ያዘናል፡፡

ቄሳሩ፡- ስለ ዘር ሀረጉ ስጠይቅህ ከተከበሩት መካከል ነው አልከኝ፡፡ መልዕክተኞች እንዲህ ናቸው፡፡ ከሕዝባቸው መሀል ከተከበሩት ዘር ሀረግ ነው የሚመረጡት፡፡ ከዚህ በፊት የሱን አምሳያ ንግግር የተናገረ ሰው እንዳለ ስጠይቅህ የለም አልከኝ፡፡ ከዚህ በፊት ተመሳሳይ ነገረ ተደርጎ በነበር ከሱ በፊት ያለውን ሰው አይቶ ነው እል ነበር፡፡ ያለውን ከማለቱ በፊት በውሸት ትጠረጥሩት እንደነበር ስጠይቅህ በውሸት ታምቶ እንደማያውቅ ነገርከኝ፡፡ ሰዎችን የማይዋሽ ስለአላህ እንደማይዋሽ አውቃለሁ፡፡ ከአባቶቹ መሀል ንጉስ የነበረ ሰው እንደነበር ስጠይቅህ የለም አልከኝ፡፡ ከአባቶቹ መሀል ንጉስ የነበረ ሰው ቢኖር የአባቶቹን ንግስና የሚፈልግ ሰው ነው እል ነበር፡፡ ተከታዮቹ የተከበሩ ሰዎች ናቸው ወይስ ደካማዎች ብዬ ስጠይቅህ ደካማዎች እንደሆኑ ነገርከኝ፡፡ የነብያቶች ተከታዮች እነርሱ ናቸው፡፡ ተከታዮቹ ይጨምራሉ ወይስ ይቀንሳሉ ብዬ ስጠይቅህ እንደሚጨምሩ ነገርከኝ፡፡ የኢማን ነገር እስኪሞላ ድረስ እንደዚህ ነው፡፡ ከመሃከላቸው ሀይማኖቱን ጠልቶ ወደነበረበት የሚመለስ ሰው እንዳለ ስጠይቅህ የለም አልከኝ፡፡ የኢማን ብርሃን ቀልብን ሲቀላቀል እንደዚህ ነው ማንም ሰው ሊጠላው አይችልም፡፡ ቃሉን የሚያፈርስ እንደሆነ ስጠይቅህ እንዳልሆነ ነገርከኝ፡፡ ነብያቶች እንደዚሁ ናቸው አይክዱም፡፡ ተዋግታችሁ እንደሆነ ስጠይቅህ እንደተዋጋችሁና አንድ ግዜ እንዳሸነፋችሁና ሌላ ግዜ እንዳሸነፋችሁት ነገርከኝ፡፡ በእርግጥ ነብያቶች ይፈተናሉ ሁል ግዜም ግን የመጨረሻው ድል ለእነሱ ነው፡፡ በምን እንደሚያዛችሁ ስጠይቅህ አላህን በብቸኝነት እንድታመልኩ በእሱም ምንም እንዳታጋሩ አባቶቻችሁ ያመልኩት የነበረውን ነገር እንድትተዉ፣ በሰላት፣ በሰደቃ፣ በጥብቅነት፣ ቃልን በማክበርና በታማኝነት እንደሚያዝ ነገርከኝ፡፡ እነዚህ ሁሉ እንደሚመጣ አውቅ የነበረው ነብይ ባህሪያቶች ናቸው፡፡ ነገር ግን ከናንተ ይሆናል ብዬ አልጠረጠርኩም ነበር፡፡ የነገርከኝ ነገር እውነት ከሆነ ሁለት እግሮቼ የቆሙበትን ቦተ ይቆጣጠራል፡፡ ብችል ኖሮ እሱ ዘንድ ብሄድ ደስ ይለኛል፡፡ አጠገቡ ብሆን ኖሮ እግሮቹን አጥብ ነበር፡፡” ከዛም ቄሳሩ የረሱልን(ሰ.ዐ.ወ) ደብዳቤ በድጋሚ እንዲነበብ አዘዘ፡፡ ደብዳቤውም እንዲህ ይል ነበር፡፡ “በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ

በሆነው። ከአላህ ባሪያና መልዕክተኛ ሙሐመድ ወደ ሩም ገዥ ሒረቅል፡፡ ቅኑን መንገድ በተከተለ ሰው ላይ ሁሉ ሰላም ይስፈን፡፡ ከዚህ በመቀጠል ወደ እስልምና እጠራሀለው፡፡ እስልምናን ተቀበል ሰላም ትሆናለህ፡፡ አላህም ምንዳህን እጥፍ አድርጎ ይሰጥሃል፡፡ እምቢ ካልክ ግን የአርያኖችን ወንጀል ጨምረህ ትሸከማለህ፡፡ *"የመጽሀፉ ባለቤቶች ሆይ! በእኛና በእናንተ መካከል ትክክል ወደኾነች ቃል ኑ። (እርሷም)አላህን እንጂ ሌላን ላንገዛ፣ በእርሱም ምንንም ላናጋራ፣ ከፊላችንም ከፊሉን ከአሏህ ሌላ አማልክት አድርጎ ላይይዝ ነው፤ በላቸው፡፡ እምቢ ቢሉም፡- እኛ ሙስሊሞች መሆናችንን መስክሩ በሏቸው፡፡"*

አቡ ሱፊያን እንዲህ ብሏል፡- ልክ ቀይሳሩ ንግግሩን ሲጨርስ አማካሪዎቹና ሚኒስትሮቹ መድረኩን በጩኸት አናጉት፡፡ ምን እንዳሉ መረዳት አልቻልኩም፡፡ ከዛም እኛ እንድንወጣ ታዞ ወጣን፡፡ ውጪ ወጥተን ከጓደኞቼ ጋር ገለልታ ስፍራ ስንሆን እንዲህ አልኳቸው "በእርግጥም ኢብኑ አቢከብሻ(ሙሐመድ) ሀያል ሆኗል፡፡ ይህ የበኒአስፈሮች(የሩሞች) ንጉስ ፈርቶታል፡፡" ከዚህ ክስተት በኋላ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ሀይማኖት ምድር ላይ እንደሚስፋፋ እርግጠኛ ሆንኩ፡፡ (ሶሂህ ቡኻሪ)

## <u>ውልደት እና እድገታቸው፡፡</u>

ነብዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) እ.ኤ.አ በ571፤ አረቦች በጣም ከሚያልቁት እና በጣም ከሚያከብሩት የቁረይሽ ጎሳ፤ የአረብ ምድረ ሰላጤ የሀይማኖት መናገሻ በሆነችዋ በመካ ከተማ ላይ ተወለዱ፡፡ መካ የተከበረ ቦታ የሆነበት ምክንያት በነብዩ ኢብራሂም እና በልጃቸው ነብዩ ኢስማኤል የተገነባው የተከበረው ካዕባ መገኛው እዛ ስለሆነ ነው፡፡ በአረብ ባህረ ሰላጤ ያሉ ዓረቦች በሙሉ ቤቱን ለመጎብኘት እዛ ይተማሉ፡፡ የረሱል(ሰ.ዐ.ወ) አባት ገና እናታቸው ሆድ ውስጥ እያሉ የነው የሞተው፡፡ ከተወለዱ ትንሽ አመታት በኋላ እናታቸውም ሞተች፡፡ የሙት ልጅ ሆነው አያታቸው አብዱልሙጠሊብ ዘንድ አደጉ፡፡ አያታቸው በሞቱ ግዜም አጎታቸው አቡጣሊብ ተወካይነቱን ወሰዱ፡፡ በዚያን ወቅት የሳቸውም ሆነ በዙሪያቸው ያሉ ጎሳዎች በሙሉ ከፊሎቹ ከእንጨጥ ከፊሎቹ ከድንጋይ ከፊሎቹ ደግሞ ከወርቀት የተሰሩ ጣኦታትን አምላኪ ነበሩ፡፡ እነዚህን ጣኦቶች ጠቃሚ እና ጎጂ ናቸው ብለው አምነው በካዕባ ዙሪያ ደርድረዋቸው ነበር፡፡ የረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ህይወት በሙሉ በእውነተኛነት እና በታማኝነት የተሞላ ነበር፡፡ በሕዝቦቻቸውም መካከል 'አልአሚን'(ታማኙ) በሚል ቅጥያ ስም ይታወቁ ነበር፡፡ የመካ ሰዎች ጉዞ ሊወጡ ባሰቡ ግዜ ንብረቶቻቸውን በአደራ የሚያስቀምጡት እሳቸው ጋር ነበር፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የሚናገሩትና የሚያወሩት ሁሉ እውነት ስለነበር በእውነተኛነታቸውም በጣም የታወቁ ነበሩ፡፡ መልካም ስነምግባር ያላቸው፣ ጥሩ ነገር የሚናገሩና ተናግረው የሚያሳምኑ ነበሩ፡፡ ለሰው ጥሩ የሚመኙ ነበሩ፡፡ ሕዝቦቻቸውም በጣም ይወዷቸው ነበር፡፡ ቅርብም ሩቅም ያለው ሰው ያከብራቸው ነበር፡፡ መልካቸው ያማረ እና በመመልከት የማይጠገቡ ነበሩ፡፡ ስነምግባራቸውም አፈጣጠራቸውም ውብ ነበር፡፡

አላህ(ሱ.ወ) ስለሳቸው እንዲህ ብሏል፡-

وَإِنَّكَ لَعَلَىٰ خُلُقٍ عَظِيمٍ [٦٨:٤]

"አንተም በታላቅ ጠባይ ላይ ነህ" (አልቀለም 4)

ቶማስ ካረሊል The heroes በሚለው መጽሀፉ ውስጥ እንዲህ ብሏል

"ሙሐመድ ገና በጠዋቱ አስተዋይ ወጣት መሆኑ ታውቆ ነበር፡፡ ጓደኞቹ "አልአሚን"(ታማኙ) ብለው ሰይመውታል፡፡ እውነተኛ እና ቃሉን የማያፈርስ ሰው ነበር፡፡ ስራውም፣ ንግግሩም እንዲሁም አስተሳሰቡም በእውነት የተሞላ ነበር፡፡ ንግግሩ

በጥበብ የተሞላ እንደሆነ አስቀድመው ገና በጠዋቱ ተረድተዋል፡፡ ብዙውን ግዜ ፀጥታን የሚመርጥ ነበር መናገር ከሌለበት አይናገርም፡፡ ከተናገረ ግን ንግግሩ መሬት የሚወድቅ ነገር የለውም፡፡ ሕይወቱን በሙሉ አቋመ ጠንካራ፣ ቆራጥ ሰው፣ አዛኝ፣ ቸር፣ ሩህሩህና አላህን ፈሪ ሆኖ ተመልክተነዋል፡፡ በጣም ቁም ነገረኛ ከመሆኑም ጋር ለዘብተኛ እና ተግባቢ ነው፡፡ ተጫዋች እንዲሁም ፊቱ ፈገግታን የተላበሰ ሰው ነው፡፡ እንደውም አንዳንዴ ቀልድ ነገርም ይቀላቅላል፡፡ ትምህርት ቤት አልተማረም፡፡ አስተማሪም አልነበረውም፡፡ ከእነዚህ ነገር የተብቃቃ ነበር፡፡ ብቻውን በበረሀው ጥልቀት ውስጥ ሆኖ ግን ስራው ተወጥቷል፡፡”

ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ልክ ነብይ ከመደረጋቸው በፊት ባለው ጊዜ ብቻቸውን መሆን ይወዱ ነበር፡፡ በሒራ ዋሻ ውስጥ ሌሊቱን በሙሉ ኢባዳ እያደረጉ ያድሩ ነበር፡፡ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ሕዝቦቻቸው ከሚሰሯቸው የሞኝ ተግባራት በጣም የራቁ ነበሩ፡፡ አስካሪ መጠጥ ጠጥተው አያውቁም፡፡ ለጣኦት አጎብድደውም ሆነ በነርሱ ምለው አያውቁም፡፡ ሕዝቦቻቸው እንደሚያደርጉት ለጣኦት ቁርባን አርደው አያውቁም፡፡

ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ለወገኖቻቸው በግ ጠብቀዋል፡፡ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ “አላህ ማንንም ነብይ አልላከም በግ የጠበቀ ቢሆን እንጂ” ሰሃቦችም “አንተም ቢሆን?” ብለው ጠየቁ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) “አዎን ለመካ ሰዎች በትንሽዬ ደሞዝ እጠብቅ ነበር” (ሰሂህ ቡኻሪ)

ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እድሜያቸው 40 ዓመት በሞላ ግዜ በሒራ ዋሻ ውስጥ አምልኮ እየፈፀሙ ባለበት ግዜ ከሰማይ ራዕይ መጣላቸው፡፡ የምዕመናን እናት ዓኢሻ(ረ.ዐ) እንዲህ ትላለች፡- የረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ወህይ የጀመረው እንቅልፋቸው ላይ በሚያዩት ደጋግ ሕልም ነው፡፡ አንድን ሕልም ባዩ ግዜ ልክ እንደ ጎሕጮራ እውን ሆኖ ይከሰት ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ብቻቸውን መሆን መምረጥ ጀመሩ፡፡ በሒራ ዋሻ ውስጥ ብቻቸውን ሆነው በተከታታይ ስንቃቸው እስኪያልቅ ድረስ የተወሰኑ ሌሊቶችን በአምልኮ ያሳልፉ ነበር፡፡ ስንቃቸው ባለቀ ግዜ ወደ ሚስታቸው ኸድጃ ይመጡና ለተመሳሳይ ቀናት ያህል የሚበቃቸውን ስንቅ ይዘው ደግመው ወደ ሒራ ዋሻ ይወጣሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ ሳሉ አንድ ቀን በሒራ ዋሻ ውስጥ ጅብሪል(ዐ.ሰ) መጣና “አንብብ!” አላቸው፡፡ “ማንበብ አልችልም” አሉት በዚህ ግዜ ትንፋሽ እስኪያጥራቸው ድረስ ጨመቃቸው፡፡ ከዚያም ለቀቃቸውና “አንብብ!” አላቸው፡፡ “ማንበብ አልችልም” አሉ ለሁለተኛ ግዜ ትንፋሽ አስኪያጥራቸው ድረስ ጨመቃቸውና ከዚያም ለቀቃቸው፡፡ አሁንም “አንብብ!” አላቸው፡፡ እሳቸውም “ማንበብ አይሆንልኝም” አሉት፡፡ ለሦስተኛ ግዜ ትንፋሽ እስከሚያጥራቸው ድረስ ጨመቃቸው፡፡ ከዚያም ለቀቃቸውና እንዲህ አለ *“አንብብ በዚያ (ሁሉን) በፈጠረው ጌታህ ስም፡፡ ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው፡፡ አንብብ ጌታህ በጣም ቸር ሲሆን፤ ያለብዕር ያስተማረ፡፡ ሰውን ያላወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ሲሆን፡፡”* ከዛም ልባቸው እየራደ ከዋሻው ተመልሰው ኸድጃ ቤት ገቡና “ደርቡልኝ፣ ደርቡልኝ” ብለው ድንጋጤው እስኪለቃቸው ድረስ ጋደም አሉ፡፡ ለኸድጃም ያጋጠማቸውን ነገር ሁሉ ነገሯትና “ስለራሴ ፈርቻለሁ” አሏት፡፡ ኸድጃም “በጭራሽ አላህ አንተን አያዋርድም፡፡ አንተ እኮ ዝምድናን ትቀጥላለህ፣ ደካሞችን ትረዳለህ፣ ለሰዎች ቸር ነህ፣ እንግዳን ታስተናግዳለህ፣ አደጋ የደረሰበትን ታግዛለህ” ኸድጃም ረሱልን(ሰ.ዐ.ወ) ይዛ ወደ ወረቃ ኢብኑ ነውፈል ሄደች። ወረቃ ማየት የተሳነው በእብራይስጥ ቋንቋ ከወንጌል የሚጽፍ ሽማግሌ ክርስቲያን ነበር፡፡ ኸዲጃም “የአጎቴ ልጅ ወረቃ ሆይ! የአጎትህ ልጅ ሙሐመድ የሚለውን ስማ” አለችው፡፡ ወረቃም “ምንድነው ያጋጠመህ?” አላቸው፡፡ ረሱልም(ሰ.ዐ.ወ) ያጋጠማቸውን በሙሉ ነገሩት፡፡ ወረቃም “ይህማ በነብዩ ሙሳ ላይ ወርዶ የነበረው ናሙስ ነው፡፡ ወገኖችህ ከሀገርህ ሲያባርሩህ በህይወት ብኖር ምኞቴ ነው” አለ፡፡ ረሱልም(ሰ.ዐ.ወ) “ከሀገሬ ያስወጡኛል እንዴ?” አሉ ወረቃም “አዎን አንተ ይዘህ የመጣህውን ነገር ይዞ የመጣ ሁሉ ወገኖቹ ጠላት አድርገው ይፈርጁታል፡፡ የዚያን ግዜ በህይወት ብደርስ ኖሮ

ብርቱ የሆነን እርዳታ እረዳህ ነበር" ከዚያ በኋላ ወረቃ ብዙም ሳይቆይ ሞተ፡፡ ወሕዩም ለትንሽ ግዜ ጋብ አለ፡፡" (ሰሂህ ቡኻሪ)

'ኢቅራ' የሚለው የቁርአን አንቀፅ የነብይነታቸው የመጀመሪያ ወሕይ ሲሆን ከዚያ በመቀጠል የሚከተለው አንቀጽ ወረዷል።

يَا أَيُّهَا الْمُدَّثِّرُ ۝ قُمْ فَأَنذِرْ ۝ وَرَبَّكَ فَكَبِّرْ ۝ وَثِيَابَكَ فَطَهِّرْ ۝ وَالرُّجْزَ فَاهْجُرْ ۝ وَلَا تَمْنُن تَسْتَكْثِرُ

"አንተ (ልብስህን) ደራቢው ሆይ! ተነስ አስጠንቅቅም፡፡ ጌታህንም አክብር፣ ልብስህንም አጥራ፣ ጣዖታትንም ራቅ፡፡ ማብዛትን የምትፈልግ ሆነህ አትለግስ፡፡" (አልሙደሲር 1-6)

ይህ የቁርአን አንቀጽ በይፋ ሰዎችን መጥራት የጀመሩበት ነበር፡፡ የመካን ሰዎች ወደ እስልምና መጣራት ጀመሩ፡፡ ይህን በማድረጋቸው መከራን እና ስቃይን አስተናገዱ፡፡ ይህን መከራ የተቀበሉበት ምክንያት ጥሪያቸውን ያቀርቡላቸው ሰዎች አዲስ እና የማያውቁት ነገር ስሆነባቸው ነው፡፡ እንዲሁም የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሀይማኖታዊ የኑሮ ዘይቤያቸውን ስለሚቀይርባቸው ነው፡፡ ጥሪያቸው አላህን በብቸኝነት አምልኩ፣ ከሱ ውጭ ያለን ነገር ከማምለክ ተቆጠቡ፣ እናንተም ጣኦቶቻችሁም ሞኞች ናችሁ በሚል ብቻ የተገደበ አልነበረም፡፡ የህብታቸው፣ የመፎካከሪያቸውና የመዝናኛቸው መሰረት የነበሩትን አራጣን፣ ዝሙትን፣ ቁማርና አስካሪ መጠጥን የሚከለክል ጭምር ነበር፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በሰዎች መሀል ፍትሕ እንዲሰፍን ማንም ከማንም አላህን በመፍራት ካልሆነ በቀር እንደማይበለጥ ጥሪ አድርገዋል፡፡ የቁረይሽ መኳንንት እና መሳፍንቶች ከባሪያ ጋር እኩል ነህ የሚለው አስተምህሮ እንዴት ይዋጥላቸዋል? በዚህም ምክንያት ጥሪህን አንቀበልም ብለው ብቻ አልተቀመጡም፡፡ ሰደቧቸው፣ አንገላቷቸው፣ እብድ ነው፣ ድግምተኛ ነው፣ ውሸታም ነው እያሉ አስወሩባቸው፡፡ ጥሪያቸውን በይፋ ከማውጣታቸው በፊት ሊያደርጉባቸው የማያስቡትን ነገር ሁሉ አደረጉባቸው፡፡ አብደላህ ኢብኑ መስኡድ(ረ.ዐ) እንዲህ ይላል፡፡ "ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ካዕባ አጠገብ እየሰገዱ ሳለ ቁረይሾች መሰባሰቢያቸው ላይ በአንድ ሆነው ተቀምጠው ነበር፡፡ ከመካከላቸው አንዱ "ይህን ክብረ ቢስ አትመለከቱትም እንዴ? ማነው የእገሌ ግመል ዘንድ ሄዶ ፈርሷን፣ ደሟንና የእንግዴ ልጇን ይዞ መጥቶ ሱጁድ እስኪያደርግ ጠብቆ ጀርባው ላይ የሚደፋው?" ብሎ ሲል አንድ የተረገመ ሰው እኔ ብሎ ተነሳና ሱጁድ በወረዱበት ሰዓት ጀርባቸው ላይ ጣለባቸው፡፡ በዚህ ግዜ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እዛው ሱጁድ ላይ ረጉ፡፡ ሰዎቹ ይህንን ባዩ ግዜ ከት ብለው አንዱ ባንዱ ላይ እስኪወድቅ ድረስ ሳቁ፡፡ ጁወይሪያ ለፋጢማ ሄዳ የተከሰተውን ስትነግራት እየሮጠች መጥታ ከጀርባቸው ላይ ወርውራ ሰዎቹን ሰደበቻቸው፡፡" (ሶሂህ ቡኻሪ)

ሙኒብ አልአዝዲ እንዲህ ይላል፡- በጃሂሊያ ዘመን ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) "እናንተ ሰዎች ሆይ! 'ላኢላሀ ኢለሏህ' በሉ ትድናላችሁ" ሲሉ ተመልክቻለሁ፡፡ከሰዎች መካከል ፊታቸው ላይ የተፋባቸው አለ፣ አፈርንም የበተነባቸው አለ፣ እንዲሁም የሰደባቸው አለ፡፡ እኩለ ቀን በደረሰ ሰዓት አንዲት ሴት ልጃቸው በባልዲ ውሃ አምጥታ ፊታቸውን እና እጃቸውን ታጥበው ሲያበቁ እንዲህ አሏት "አንቺ ልጅ ሆይ! በአባትሽ ላይ ድህነትን እና ውርደትን አትፍሪ፡፡"

ኡርዋ ኢብኑ ዙበይር እንዲህ ይላል፡- አብደላህ ኢብን አምር ኢብን አል አስን አጋሪዎች በረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ያደረሱባቸውን አስከፊ እንግልት እንዲነግረኝ ጠየቅኩት፡፡ እሱም እንዲህ አለኝ "ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ካዕባ አጠገብ እየሰገዱ ሳሉ ኡቅባ ቢን አቢሙአይጥ መጣና በሀይል ልብሳቸውን ጨምድዶ አነቃቸው፡፡ የዚህን ግዜ አቡበክር(ረ.ዐ) መጣ፡፡ የኡቅባን ትከሻ ይዞ ገፈተረውና እንዲህ አለው "አንድን ሰው ከጌታችሁ ዘንድ ማስረጃ ይዞ መጥቶ ጌታዬ አላህ ነው ስላለ ትገድሉታላችሁን፡፡" (ሶሂህ ቡኺሪ)

እነዚህ እና የመሳሰሉት ኢጋጣሚዎች ረሱልን(ሰ.ዐ.ወ) ካዳዕዋቸው እንዲያፈገፍጉ ወይም እንዲሸሹ አላደረጋቸውም:: በሀጅ ወቅት ወደ መካ ለሚመጡ የአረብ ጎሳዎች ጥሪ ያድጉ ነበር:: በዚህ መልኩ ከየስሪብ(መዲና) ሰዎች የተወሰኑት ተቀበሏቸው:: ወደ ሀገራቸውም ከመጣ እንደሚረዱት እና ከጠላቶቹ እንደሚጠብቁት ቃል ገቡ:: ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ከባልደረቦቻቸው መካከል ሙስአብ ኢብኑ ኡመይርን (ረ.ዐ) እስልምናን እንዲያስተምራቸው ከነሱ ጋር አብረው ላኩት:: የአላህ መልዕክተኛ እና ከሳቸው ጋር የነበሩት አቅመ ደካማ ሙስሊሞች በመካ ካስተናገዱት መከራ እና እንግልት በኋላ አላህ(ሱ.ወ) ወደ መዲና እንዲሰደዱ ፍቃድ ሰጣቸው:: የመዲና ሰዎችም በደመቀ መልኩ አቀባበል አደረጉላቸው:: በዚህ መልኩ መዲና የዳዕዋቸው ማዕከል እና የእስልምና ዋና ከተማ ሆነች:: ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ለተከታዮቻቸው እዛ ተቀምጠው ተቀምጠው ቁርአን እና የሀይማኖታቸውን ሕግጋት ያስተምሯቸው ጀመሩ:: ተከታዮቻቸውም ከረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ባዩት ታላቅ ስብዕና መልካም ስነምግበር እና ተማርከው ከራሳቸው አስበልጠው ወደዷቸው:: እሳቸውን ለማገልገል በሚወዱት እና ውድ በሆነ ሀብታቸው በሙሉ ይሽቀዳደሙ ነበር:: በዚህ መልኩ ደስታ፣ ፍቅር፣ ወንድማማችነት እና መስማማት የሰፈነበት ኑሮ መኖር ጀመሩ::

ሀብታሙም ድሃውም፣ መሪዎቹም ተራ ሰዎችም፣ ጥቁርም ነጭም፣ አረቡም አረብ ያልሆነውም በዚህ ሀይማኖት ጥላ ስር እኩል ሆኑ:: የሚበላለጡት እና የሚለያዩት አላህን በመፍራት ብቻ ነው:: አንድ አመት ያክል በመዲና ተረጋግተው ከተቀመጡ በኋላ የበደል እና የግፍ አይነት የፈፀሙባቸውን ሰዎች ጦር መግጠም ጀምሩ:: በእስልምና ታሪክ የመጀመሪያው ጦርነት የበድር ጦርነት ሆኖ ተመዘገበ:: በሁለቱ ቡድኖች መካከል የመሳሪያም ሆነ የቁጥር ሰፊ ልዩነት ነበር:: የሙስሊሞች ቁጥር 314 የነበረ ሲሆን የኢጋሪዎች ቁጥር ደግሞ 1000 ነበር:: አላህ (ሱ.ወ) ረሱልን እና አማኞችን ረድቶ ድል የነሱ ሆነች:: ከዛም በኋላ ሙስሊሞች እና በኢጋሪዎች መሀከል የተለያዩ ጦርነቶች ተካሂደዋል:: ከ8 ዓመት በኋላ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) 10000 የጦር ሰራዊት አዝምተው እነዚያን የመከራን ዓይነት ሲያወርዱባቸው የነበሩትንና ንብረታቸውን፣ ልጆቻቸውን እና ሀገራቸውን ጥለው እስኪሰደዱ ድረስ ያሰቃዩዋቸውን ሰዎች ደምስሰው መካን ተቆጣጠሩ:: ይህ ድል በእስልምና ታሪክ ታላቅ ድል ነበር:: የድሉ አመትም ‘አመል-ፈትህ’ በመባል ታወቀ:: ይህን አስመልክቶ አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

إِذَا جَاءَ نَصْرُ اللَّهِ وَالْفَتْحُ ۝ وَرَأَيْتَ النَّاسَ يَدْخُلُونَ فِي دِينِ اللَّهِ أَفْوَاجًا ۝ فَسَبِّحْ بِحَمْدِ رَبِّكَ وَاسْتَغْفِرْهُ ۚ إِنَّهُ كَانَ تَوَّابًا ۝

*“የአላህ እርዳታና (መካን) መክፈት በመጣ ጊዜ፤ ሰዎችንም ጭፍሮች እየሆኑ በአላህ ሀይማኖት ውስጥ ሲገቡ ባየህ ግዜ፤ ጌታህን ከማመስገን ጋር አጥራው ምህረትንም ለምነው እርሱ ፀፀትን በጣም ተቀባይ ነውና::” (አን-ነስር 1-3)*

ከዛም ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) የመካን ሰዎች ሰብስበው “ምን የማደርጋችሁ ይመስላችኋል? አሏቸው እነሱም “አዛኝ ወንድማችን ነህ:: የአዛኝ ወንድማችን ልጅ ነህ:: ጥሩን ነገር እንጂ ካንተ አንጠብቅም::” አሉ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) “ሂዱ ነፃ ናችሁ” አሏቸው። (ሱነን ባይሀቂ)

በዚህ ምክንያት ብዙ የመካ ሰዎች እስልምናን ተቀበሉ:: ከዛም በኋላ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ወደ መዲና ተመለሱ:: መዲና የተወሰነ ግዜ ከተቀመጡ በኋላ ሀጅ ለማድረግ 114,000 ባልደረቦቻቸውን አስከትለው ወደመካ መጡ:: ይህ ሀጅ ‘የስንብት ሀጅ’ በመባል ይታወቃል:: ምክንያቱም የመጨረሻ ሀጃቸው ስለነበረ ነው::

ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) በመዲና ከተማ በ11ኛ አመት ሂጅራ በረቢኡ-ሳኒ 12 በሰኞ ቀን ከዚህ አለም በሞት ተለዩ። እዛው የሞቱበተ ቦታም ተቀበሩ:: የተወሰኑ ሰሃቦች ይህን ዜና እስካለማመን ድረስ ከፍተኛ ድንጋጤን ደነገጡ:: ከእነዚህ ሰሀቦች መካከልም

አንዱ ዑመር(ረ.ዐ) ነበር፡፡ እንዲህ ይል ነበር "ሙሐመድ ሞቷል እያለ ሲያወራ ያገኘሁት ሰው አንገቱን እቆርጠዋለሁ፡፡" በዚህ ሁኔታ ላይ ሳሉ አቡበከር(ረ.ዐ) ተነስቶ የሚከተለው የቁርአን አንቀፅ አነበበ፡-

وَمَا مُحَمَّدٌ إِلَّا رَسُولٌ قَدْ خَلَتْ مِن قَبْلِهِ الرُّسُلُ ۚ أَفَإِن مَّاتَ أَوْ قُتِلَ انقَلَبْتُمْ عَلَىٰ أَعْقَابِكُمْ ۚ وَمَن يَنقَلِبْ عَلَىٰ عَقِبَيْهِ فَلَن يَضُرَّ اللَّهَ شَيْئًا ۗ وَسَيَجْزِي اللَّهُ الشَّاكِرِينَ [٣:١٤٤]

"ሙሐመድም ከበፊቱ መልዕክተኞች በእርግጥ ያለፈ የሆነ መልዕክተኛ እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ ታዲያ ቢሞት ወይም ቢገደል ወደኋላችሁ ትገለበጣላችሁን?፤ ወደኋላው የሚገለበጥም ሰው አላህን ምንም አይጎዳም፡፡ አላህም አመስጋኞቹን በእርግጥ ይመንዳል፡፡" (አል ኢምራን 144)

ሰይድና ኡመር(ረ.ዐ) ይህንን የቁርዓን አንቀጽ ሲሰሙ ቆሙ፡፡ ሰይድና ዑመር(ረ.ዐ) የአላህን(ሱ.ወ) ንግግር ሲሰሙ ቀጥ ብለው የሚቆሙ ሰው ነበሩ፡፡

ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ሲሞቱ እድሜያቸው 63 ነበር፡፡ መካ ውስጥ ነብይ ከመሆናቸው በፊት 40 ዓመት፥ ነብይ ከተደረጉ በኋላ ደግሞ ወደ ተወሒድ ሰዎችን እየተጣሩ ለ13 ዓመታት ተቀምጠዋል፡፡ ከዛም ወደ መዲና በስደት ከሄዱ በኋላ ለ10 ዓመት እዛው ቆዩ፡፡ በእነዚህ አስር ዓመታት ውስጥ ቁርአን ሙሉ የእስልምና ህጋግት ይዞ በመውረድ ተጠናቋል፡፡

Dr. G.Lebon የአረብ ስልጣን በሚል መፅሀፉ ውስጥ እንዲህ ይላል፡- "የሰዎችን ደረጃ የምንመዝነው በሰሩት ስራ ልክ ከሆነ ታሪክ እንደ ሙሐመድ አይነት ታላቅ ሰው አስተናግዶ አያውቅም፡፡ ምዕራባውያን ሙሁራኖች ስለሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) ታላቅነት እተረዱ መጥተዋል፡፡ ይህ ከመሆኑም ጋር ግን አሁንም አብዛኛው የታሪክ ፀሀፊዎች የሀይማኖት ወገንተኝነት አጥቅቷቸው የሳቸውን ደረጃና ልክ እንዳያውቁ እውር አድርጓቸዋል፡፡"

## <u>ስለ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ገለፃ</u>

ሰዎችን በመግለፅ የሚታወቀው ሂንድ ኢብኑ አቢሃላ አትተሚሚይ ስለ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ተክለ ሰውነት እና ባህሪ ገለፃ ሲያደርግ እንዲህ ብሏል፡-

"ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ፊታቸው ግርማ ሞገስ ያለውና ውበት የተላበሰ ነበር፡፡ ፊታቸው እንደ ሙሉ ጨረቃ የሚያበራ ነበር፡፡ ቁመታቸውም በጣም ያልረዘመ፣ በጣምም ያላጠረ መካከለኛ ነበር፡፡ ጭንቅላታቸውም ትልቅ ነበር፡፡ ፀጉራቸው በጣም ውብ ነው፡፡ ካልረዘመ በስተቀር አይጎነጉኑትም፡፡ ብዙውን ግዜ ፀጉራቸው ከታችኛው የጆሮ ክፍል አያልፍም፡፡ መልካቸው የሚያበራ ቅላት አለው፡፡ ግንባራቸው ሰፊ ነው፡፡ ቅንድቦቻቸው ቀጠን ብለው የረዘሙ እና ያልተገጣጠሙ ናቸው፡፡ በብዛታቸውም ጥቅጥቅ ያሉ ናቸው፡፡ በሁለቱ ቅንድቦች መሀል በቁጣ ግዜ የሚወጣር የደምስር አለ፡፡ አፍንጫቸው ሰልካካ እና የሚያበራ ነበር፡፡ በቁመትም ከአይናቸው መሀል ከፍ ብሎ ይታያል፡፡ ፂማቸው ጥቅጥቅ ያለ ነበር፡፡ ጉንጫቸው ለስላሳ እና ፈታ ያለ ነበር፡፡ አፋቸው የፊቶቹን ጥርስ በሚያሳይ መልኩ የሰፋ ነው፡፡ ከላይኛው ከንፈር በላይ ቀለል ያለ ጸጉር አለ፡፡ ጥርሳቸውም ላይ ፍንጨት ነበር፡፡ ደረታቸው ላይ ያለው ፀጉር ቀለል ያለና መሀል መስመሩን የያዘ ነበር፡፡ አንገታቸው ያምራል፡፡ መልኩም እንደ ነጭ ብር ይመስላል፡፡ ሰውነታቸው ደልደል ያለ ነው፡፡ ወፈር ብለው ጠንከር ያሉ ናቸው፡፡ ደረታቸውና ሆዳቸው አይለያዩም፡፡ ደረታቸው ሰፍቶ ትከሻቸው የተራራቁ ናቸው፡፡ መገጣጠሚያቸውም ትልቅ ነው፡፡ ከላይኛው ደረታቸው አንስቶ እስከ እምብርታቸው ድረስ መስመር ሰርቶ የሚወርድ ፀጉር አለ፡፡ ከመሀል ውጪ ደረታቸውም ላይ ሆነ ሆዳቸው ላይ ጸጉር የለም፡፡ እጃቸው ላይ ከክርናቸው አንስቶ እስከ ትከሻቸው ደረስ ፀጉር አለባቸው ክንዳቸውም ረዘም ያለ ነው፡፡ መዳፎቻቸው ሰፊ ናቸው፡፡ የእጃቸውም ሆነ የእግራቸው ቁርጭምጭሚት ጠንከር ያለ ነው፡፡

የውስጥ እግራቸው መሀል የገባ ነበር፡፡ የውስጥ እግራቸው በጣም ለስላሳ ከመሆኑ የተነሳ ውሃ ላዩ ላይ አይቀመጥም፡፡ ሲራመዱ ረጋ ብለው ቢሆንም እግራቸውን ግን አይጎትቱም፡፡ እግራቸውን ረዘም አድርገው እየጣሉ ሳይቸኩሉ ሳይንቀረፈፉም ይሄዳሉ፡፡ ሲዞሩ አይናቸውን ሰበር አድረገው ሳያንጋጥጡ ነው የሚሄዱት፡፡ ሲዞሩ በአንገታቸው ብቻ ሳይሆን በመላ አካላቸው ነው። አይናፋር ከመሆናቸው የተነሳ ቀና ብለው ከሚያዩበት ወደ መሬት የሚያዩበት ጊዜ ይበዛል፡፡ አብዛኛውን ግዜ ሰው ሲያዩ አፍጥጠው ሳይሆን በጨረፍታ ነበር፡፡ ከሰሃቦች ጋር ሲሄዱ ከኋላ ይሆኑ ነበር፡፡ ያገኙትን ሰው ሰላምታ ለማቅረብ ይቸኩላሉ፡፡

ስለንግግራቸው አብራራልኝ አልኩት፡- "ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ለረጅም ሰዓት ይተክዙ ነበር፡፡ ሁልጊዜ ያለእረፍት ያሰላስሉ ነበር፡፡ ዝምታን ያበዙ ነበር፡፡ ያለምክንያት አይናገሩም ነበር፡፡ ንግገርን ሲጀምሩም ሆነ ሲጨርሱ ሙሉ የመናገሪያ አካላቶቻቸውን ይጠቀሙ ነበር(እንደ ኩራተኛ የከንፈራቸውን ጫፍ ብቻ በመጠቀም አያወሩም)፡፡ ንግግራቸው ጠቅለል ያለ ነበር (ትንሽን ቃላት ይዞ ብዙትርጉም ያለውነው)፡፡ ግልፅ እና አጠር መጠን ያለ ነው፡፡ የተወሳሰበ ሳይሆን ሁሉም የሚረዳው ነው፡፡ ንግግራቸው የተከበረና ሁሉንም ሰው የሚመለከት ነው፡፡ ትንሽም ብትሆን ፀጋን አይንቁም፡፡ የሚበላን ነገር አያናንቁም አያዳንቁምም፡፡ ዱንያ እና ከዱያ ጋር የተያያዘ ነገር አያስቆጣቸውም፡፡ ሐቅ የተነካ ግዜ ግን ሀቁን እስኪያስመልሱ ድረስ ቁጣቸውን የሚያቆመው አልነበረም፡፡ ስለራሳቸው ተቆጥተውም ይሁን ተበቅለው አያውቁም፡፡ ሲጠቁሙ ሙሉ እጃቸውን ይጠቀማሉ፡፡ ሲገረሙ ግዜ እጃቸውን ያጠላልፉ ነበር፡፡ ንግግር ላይ ሲሆኑ የቀኝ እጃቸውን መዳፍ ከግራ እጃቸው አውራ ጣት ላይ ያደርጉ ነበር፡፡ ሲቆጡ ፊታቸውን ያዞራሉ፡፡ ሲደሰቱ አይናቸውን ይሰብራሉ፡፡ አብዛኛው ሳቃቸው ፈገግታ ነበር፡፡ ሲስቁ ነጭ በረዶ የሚመለስለውን ጥርሳቸውን ብቻ ያሳያሉ።

ይህንን ገለፃ ለሁሴይን(ረ.ዐ) ሳልነገረው ብዙ ግዜ ቆይቼ ነበር፡፡ በኋላ ስነግረው ግዜ ለካስ እሱ ቀድሞኝ አባቱን አልይ(ረ.ዐ) ጠይቆ አውቆ ኖሯል፡፡ ሁሰይን(ረ.ዐ) በተጨማሪም ቤት አገባባቸውን፣ አወጣጣቸውን እና አቀማመጣቸውን ጠይቋል፡፡

⇒ ሁሴን፡- ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ቤታቸው ሲገቡ አገባባቸው እንዴት ነበር?

⇒ አባቱ(አሊይ (ረ.ዐ))፡- "ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ቤታቸው ለመግባት ጥቅል ፍቃድ ነበራቸው፡፡ ወደ ቤታቸው በገቡ ወቅትም ያላቸውን ግዜ ለ3 ይከፍሉ ነበር፡፡ አንዱን ለአላህ፣ ሌላውን ለቤተሰባቸው፣ የቀረውን ለነፍሳቸው፡፡ ለነፍሳቸው የሰጡትን ግዜ ደግሞ በሰዎች እና በራሳቸው መሀል ለ2 ይከፍሉታል፡፡ ለሰዎች የሰጡትን ግዜ ምንም ሳያባክኑ ከሰዎች ጋር ያሳልፉት ነበር፡፡ ለሰዎች የሰጡትን ሰዓት እንደ ኢማን ደረጃቸው ለሰዎቹ ያከፋፍላሉ፡፡ ለታላላቆቹ ሰሃቦች ብዙውን ጊዜ ይሰጣሉ፡፡ ከሰዎች መሀል ባለአንድ፣ ባለሁለት አልያም ባለብዙ ባለጉዳይ ይኖራል፡፡ ለኡማው የሚጠቅም ጉዳይ ላይ በማስተማር ይጠመዳሉ፡፡ የሰማ ላልሰማ እንዲያስተላለፍ ያበረታታሉ፡፡

"ጉዳዩን ወደኔ ማድረስ ላልቻለ ሰው አድርሱለት፡፡ ጉዳዩን ለአስተዳዳሪ ማድረስ የማይችልን ሰው ጉዳይ ለአስተዳዳሪ ያደረሰ ሰው የውመል ቂያማ አላህ ተደላድሎ እንዲቆም ያደርገዋል" ብለው ይላሉ፡፡

⇒ ሁሴይን(ረ.ዐ)፡- "ከቤት ውጪ ያለው ሁኔታቸውስ እንዴት ነበር?"

⇒ አልይ(ረ.ዐ)፡-ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ምላሳቸውን አስፈላጊ እስካልሆነ ድረስ ይቆጥቡ ነበር፡፡ ሰዎች እርስ በእርስ እንዲስማሙ እና እንዳይለያዩ ያደርጉ ነበር፡ ከየጎሳቸው የተከበሩትን ሰዎች ያከብሩ ነበር፡፡ በየሕዝቦቻቸው ላይ መሪ አድርገው ይሾሟቸው ነበር፡፡ ሰዎችን ያስጠንቅቁ ነበር፡፡ ራሳቸውንም ከሰዎች ይጠብቃሉ፡፡ ማንንም ሰው ግን አያስከፋም፡፡ ከባልደረቦቻቸው መሀል አንዱ ሲጠፋ "እገሌ የት ጠፋ?" ይላሉ፡፡ ስለ ሰዎች ሁኔታ ያጠያይቃሉ፡፡ ጥሩን ነገር ሲያዩ ያበረታታሉ፡፡ መጥፎን ነገር ሲመለከቱ መጥፎ እንደሆነ አስተምረው ሰው እንዲርቀው ያስጠንቅቃሉ፡፡ በነገራቶች ላይ

መካከለኛ ናቸው፡፡ ለሁሉም ሰው ሳያሳንሱም ሆነ ሳያበዙ በአቅሙ ልክ ይሰጣሉ፡፡ እሳቸው ዘንድ ምርጡ ሰው ሰዎችን የሚመክር ሰው ነው፡፡ እሳቸው ዘንድ በደረጃ ትልቁ ደግሞ ሰዎችን የሚረዳ እና ለሰዎች ጠቃሚ የሆነ ሰው ነው፡፡

⇒ ሁሰይን (ረ.ዐ)፡- አቀማመጣቸውስ እንዴት ይመስል ነበር?

⇒ አልይ (ረ.ዐ)፡-ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ሲቆሙም ሆነ ሲቀመጡ አላህን ያወሱ ነበር፡፡ ለራሳቸው የተለየ ቦታን አይዙም፡፡ ሰዎችንም ከዚህ ተግባር ይከለክሉ ነበር፡፡ የተቀመጡ ሰዎች ዘንድ ሲመጡ ያገኙት ክፍት ቦታ ላይ ይቀመጡ ነበር፡፡ ሰዎችንም በዚህ ያዙ ነበር፡፡ አብሯቸው ለሚቀመጥ እንዳንዱ ሰው በልኩ ቦታ ይሰጡ ነበር፡፡ አብሯቸው የተቀመጠ ሰውም እሳቸው ዘንድ ከሱ በላይ የተወደደ ሰው ያለ አይመስለውም ነበር፡፡ ጉዳዩን ሊያዋያቸው የመጣንም ሰው እራሱ ተነስቶ እስኪሄድ ድረስ ጥለውት አይነሱም፡፡ የሆነን ነገር የጠየቃቸውን ሰው ሳይሰጡት አይሸኙትም፡፡ ካልቻሉ ግን በትንሹ በጥሩ ንግግር ይሸኙታል፡፡ ባህሪያቸው እና አቀራረባቸው ከመመቸቱ የተነሳ ለሁሉም ሰው አባት ናቸው፡፡ እሳቸው የተቀመጡበት ስብሰባ እውቀት፣ ትዕግስት፣ ስርዓት፣ ዓይናፋርነት እና ታማኝነት የሚቀሰምበት ነው፡፡ ከፍ ያለ ድምፅ አይሰሰማም መጥፎ ነገር አይወራም ሁሉም ሰው እኩል የሆነበት እና አላህን በመፍራት ካልሆነ በቀር የማይበላለጡበት ነው፡፡ እርስ በእርሳቸው ይከባበራሉ፤ ትልቅ ሰው ያከብራሉ፣ ለልጆች ያዝናሉ፣ ባለጉዳይን ያስቀድማሉ፣ እንግዳን ያከብራሉ፡፡

⇒ ሁሴን፡- ከአቀማማጮቻቸው ጋር ያላቸውን ሁኔታ ንገረኝ?

⇒ አይል፡- ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ሁልጊዜ ለዘብ ያሉ እና ቀላል ሰው ነበሩ፡፡ ዐመለ መጥፎ፣ ቁጡ እና ኮስታራ አልነበሩም፡፡ አፀያፊ ነገር ከመናገር እና ሰዎችን ከማራቅ የፀዱ ናቸው። እሳቸውን ከማይመለከታቸውና ጥርጣሬ ካለበት ነገር ይርቃሉ፡፡ ማናንንም ሰው አያዋርዱም፣ አያሳንሱም፣ ነውሩንም አይከታተሉም፣ ጥቅም ያለው ነገር ካልሆነ በቀር አይናገሩም። እሳቸው ሲናገሩ ባልደረቦቻቸው አናታቸው ላይ ወፍ የተቀመጠ ይመስል አቀርቅረው ፀጥ ይላሉ፡፡ ተናግረው ሲያበቁ ይናገራሉ፡፡ እሳቸው አጠገብ አይከራከሩም፡፡ አንድ ሰው ከተናገረ እስኪጨርስ ድረስ ሁሉም ጸጥ ይላሉ፡፡ ባልደረቦቻቸው ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) የሚያወሩት ነገር ይገባቸዋል፡፡ በሚያስቃቸውም ነገር ይስቃሉ፡፡ በሚያስገርማቸውም ነገር ይገረማሉ፡፡ እንግዳ ሰው በንግግሩ ላይም ይሁን በጥያቄው ላይ በሚያሳየው ስርዓት አልበኝነት ይታገሳሉ፡፡ "ባለጉዳይን ያገኛችሁ ግዜ ወደሚፈልገው ነገር አመላክቱት" ይላሉ፡፡ አንድን ሰው በሚያወራ ግዜ እስኪጨርስ ድረስ አያቋርጡትም፡፡

⇒ ሁሰይን (ረ.ዐ)፡- የረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ዝምታ ምን ይመስል ነበር?

⇒ አይል (ረ.ዐ)፡- የረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ዝምታ በአራት ሁኔታ ነበር፡፡ በትዕግስት፣ ለማስተማር፣ ለማመዛዘን እና ለማስተንተን ናቸው፡፡ ለማመዛዘን የተባለው የሰዎችን ሀሳብ ለመስማት እና አወዳድሮ ለመቀበል ነው፡፡ ለማስተንተን የተባለው ደግሞ የዱንያን እና የአኼራን ሁኔታ ለማሰላሰል ነው፡፡ እንዲሁም ነገራቶች እያስቆጣቸውም አያስደነግጡዋቸውምም። አላህ ትዕግስተኛ አድርጓቸዋል፡፡ ለማስተማር የተባለው 4 ነገርን ይይዛል። ጥሩን ነገር እየሰሩ ሰዎች እንዲከተሏቸው፣ መጥፎን ነገር እየራቁት ሰዎች እንዲከለከሉ፣ ለተከታዮቻቸው ጠቃሚ የሆኑ ነገሮችን 'ኢጅቲሀድ' እያደረጉ አልያም ለዱንያ እና ለአኼራ በሚጠቅም ጉዳይ ላይ ሲቆሙ።

# የተወሰኑ የረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ባህርያት እና ስነምግባራት

1. **ብሩህ አእምሮ**

ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ከሳቸው ውጪ ማንም ሰው ያልደረሰበትን ከፍተኛ የአስተሳሰብ ደረጃ ደርሰዋል፡፡ ቃዲ ኢያድ እንዲህ ይላል፡- የእሳቸውን ትልቅነት እና በተለያዩ ዘርፎች ያላቸውን ልዩ ክህሎት የምትረዳው ታሪካቸውን በጥልቀት መመርመር ስትችል ነው፡፡ ንግግራቸው ላይ ማተኮር ስትችል ነው፡፡ የጸባያቸውን መልካምነት፣ የንግግራቸውን ጥበብ፣ በኢንጂል እና ተውራት ላይ ያላቸውን እውቀት፣ ከዚህ በፊት የነበሩትን ሕዝቦች ታሪክ እና ክስተቶች ላይ ያላቸው እውቀት፣ ምሳሌ አሰጣጣቸው፣ ፖለቲካዊ ትንተናቸውን፣ ህግ አረቃቀቃቸውን፣ ሰዎችን እንዴት ስርዓት እንደሚያስይዙ እና መጥፎ ልምዶችቻቸውን እንዴት እንደሚያስተዋቸው መመልከት ስትችል ነው፡፡ እንዲሁም በአምልኮ፣ በህክምና፣ በውርስ ጉዳይ፣ እና በሌሎም ዘርፎች ላይ ያሉ ምሁራኖች የሳቸውን ንግግር እንደማስረጃ እና ለእውቀታቸውም እንደመሠረት እንደሚጠቀሙበት ስታውቅ ነው፡፡ ይህ የሆነው ደግሞ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ት/ቤት ሳይገቡ፣ መፅሀፍቶችን ሳያነቡ እንዲሁም ከምሁራኖች ጋር ሳይገናኙ ኸረ እንደውም መፃፍ እና ማንበብ ሳይችሉ ነው፡፡ አላህ ባሳወቃቸው ወደፊት የሚመጣውንና በፊት ያለፈውን ነገር ማወቃቸውም የሚገርም የአስተሳሰብ ችሎታቸውን እና የደረሱበትን የምጥቀት ደረጃ የሚያሳይ ነው፡፡

2. **ምንዳን ከአላህ ብቻ መፈለግ**

ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) በሚሰሩት ስራ ሁሉ የሚፈልጉት የአላህን ውዴታ ነበር፡፡ ዳዕዋ በማድረግ ላይ ብዙ መከራን እና ስቃይ አስተናግደዋል፡፡ ምንዳቸውን ከአላህ በመፈለግ ታግሰው አሳለፉት፡፡ አብዱላህ ኢብኑ መስኡድ(ረ.ዐ) እንዲህ ብለዋል፡- ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ስለ አንድ ነብይ ሲተርኩልኝ የነበረበት ሰዓት በምናቤ እየታየኝ ነው፡፡ ህዝቦቹ ደብድበውት ከፊቱ ላይ ደሙን እየጠረገ እንዲህ ይላል፡- "አላህ ሆይ ህዝቦቼን ማርልኝ እነሱ አላዋቂ ናቸውና።" (ሰሂህ ቡኻሪ)

ጁንዱብ ኢብኑ ሱፍያን(ረ.ዐ) እንዲህ ይላል፡- በአንድ የጦር አውድማ ላይ የነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ጣት ደማ እና እንዲህ አሉ፡- "የደማሽው አንድ ጣት አይደለሽ፤ ያውም በአላህ መንገድ ላይ የተገኘሽ" (ሰሂህ ቡኻሪ)

3. **ስራን ለአላህ አጥርቶ መስራት**

ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) አላህ(ሱ.ወ) እንዳዘዛቸው በሚሰሩት ስራ ሁሉ ለሱ ብለው ነበር፡፡ አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

قُلْ إِنَّ صَلَاتِي وَنُسُكِي وَمَحْيَايَ وَمَمَاتِي لِلَّهِ رَبِّ الْعَالَمِينَ۝لَا شَرِيكَ لَهُ ۖ وَبِذَٰلِكَ أُمِرْتُ وَأَنَا أَوَّلُ الْمُسْلِمِينَ

*"ስግደቴ፣ መገዛቴም፣ ሕይወቴም፣ ሞቴም ለዓለማት ጌታ ለአላህ ነው" በል። ለእርሱ ተጋሪ የለውም፡፡ በዚህም(በማጥራት) ታዘዝኩ እኔም የሙስሊሞች መጀመሪያ ነኝ" (በል)። (አንዓም 162-163)*

4. **በመልካም ስነምግባር መኗኗር**

ባለቤታቸው ዓኢሻ(ረ.ዐ) ስለባህሪያቸው ስትጠየቅ እንዲህ ትላለች፡-

"ስነምግባራቸው ቁርዓን ነበር፡፡" የዚህ ትርጉም ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ቁርዓን የሚያዘውን ነገር የሚታዘዙ፣ የሚከለክለውን ነገር የሚከለክሉ፣ አስተምህሮቶቹን የሚተገብሩ እና ድብቅም ይሁን ግልጽ አፀያፊ ተግባራትን የሚርቁ ነበሩ ማለት ነው፡፡ ይህን መባላቸውም የሚገርም ነገር አይደለም፡፡ እራሳቸውም እንዲህ ብለዋል፡-

*"እኔን አላህ የላከኝ መልካም ስነምግባራትን እና ጥሩ ስራዎችን ላሟላ ነው፡፡"(ቡኻሪ)*

አላህም(ሱ.ወ) እንዲህ ሲል አወድሷቸዋል፡-

وَإِنَّكَ لَعَلَىٰ خُلُقٍ عَظِيمٍ [٦٨:٤]

*“አንተም በታላቅ ጠባይ ላይ ነህ”(አልቀለም 4)*

አስር ዓመት ሙሉ ረሱልን(ሰ.ዐ.ወ) ያገለገለው አነስ ኢብኑ ማሊክ(ረ.ዐ) እንዲህ ይላል፡- “ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ከሰዎች በበለጠ መልኩ መልካም ስነምግባርን የተላበሱ ናቸው፡፡”

አስከትሎም “ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) አፀያፊ ነገር የሚናገሩ፣ የሚራገሙ ወይም የሚሳደቡ አልነበሩም፡፡” አንድን ሰው ሲወቅሱ “ምን ሆኖ ነው? ግንባሩ አፈር ይልበስና” ይሉ ነበር፡፡

5. **ስነስርዓት**

ሰህል ኢብኑ ሰዓድ(ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) የሚጠጣ ነገር መጣላቸውና ትንሽ ከጠጡ በኋላ ወደቀኝ ሲያዩ ያለው ልጅ ነው፡፡ ወደግራ ደግሞ ትልልቅ ሰዎች ናቸው፡፡ ከዛም ለልጁ “እነዚህን ሰዎች እንዳስቀድም ትፈቅድልኛለህን?” አሉት ልጁም፡- “በአላህ ይሁንብኝ አንቱ የአላህ መልክተኛ! ያንቱን እድል ለማንም አሳልፌ አልሰጥም” አላቸው፡፡ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ልጁን በእጃቸው አጠጡት፡፡ (ሰሂህ ቡኻሪ)

6. **ሰዎችን ማስማማት**

ሰህል ኢብኑ ሰዕድ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፡- የቁባዕ ሰዎች በአንድ ግዜ ተጣልተው ድንጋይ እስከመወራወር ደረሱ፡፡ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ስለዚህ ጉዳይ ሲሰሙ “እንሂድና እናስተርቃቸው” አሉ፡፡ (ሰሂህ ቡኻሪ)

7. **በጥሩ ማዘዝ እና ከመጥፎ መከልከል**

አብደላህ ኢብኑ አባስ(ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፡- ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) አንድ ሰው እጅ ላይ የወርቅ ቀለበት ተመለከቱ እና አውልቀው ጣሉበት፡፡ ከዛም እንዲህ አሉ “አንድ ሰው በፍላጎቱ የእሳትን ጠጠር እጁ ላይ ያስቀምጣልን፡፡” ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ከሄዱ በኋላ ሰዎች ለሰውየው ‘ቀለበትህን አንሳና ሽጠህ ተጠቀምበት’ ሲሉት እሱም “በጭራሽ፥ በአላህ ይሁንብኝ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) የጣሉትን ነገር ጎንበስ ብዬ አላነሳም” አለ፡፡ (ሰሂህ ሙስሊም)

8. **ንፅህናን መውደድ**

ሙሀጂር ኢብኑ ቀንፈዝ(ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፡- ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እየተፀዳዱ ባሉበት ሰዓት መጥቶ ሰላምታ አቀረበላቸው፡፡ እሳቸው ግን ወጥተው ውዱ እስኪጨርሱ ድረስ ሰላምታውን አልመለሱለትም፡፡ ከዛም ይቅርታ ጠይቀውት እንዲህ አሉት “በንፅህና ላይ ሳልሆን የአላህን ስም ማውሳት ጠልቼ ነው፡፡” (ሰሂህ ኢብኑ ኹዘይማ)

9. **ምላስን መጠበቅ**

አብደላህ ኢብኑ አውፍ(ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት “ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) አላህን ማስታወስ ያበዙ ነበር ጨዋታን አያበዙም ነበር፡፡ ሶላትን አስረዝመው ኹጥባን ያሳጥሩ ነበር፡፡ ባሎቻቸው ከሞቱባቸው ሴቶችና ከምስኪኖች ጋር በመሄድ ጉዳያቸውን ይፈፅሙላቸው ነበር፡፡” (ሰሂህ ኢብኑ ሂባን)

10. **ኢባዳ ማብዛት**

እናታችን ዓኢሻ(ረ.ዐ) እንዲህ ትላለች፡- “ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) እግራቸው እስኪሰነጠቅ ድረስ ሌሊቱን ይሰግዱ ነበር፡፡ “ያሳለፍከውንም ሆነ የሚመጣውንም ወንጀል አላህ ምሮህ ሳለ ራስህን እንዲህ ለምን ታስቸግራለህ?” አልኳቸው። ረሱልም(ሰ.ዐ.ወ) “አመስጋኝ ባሪያ መሆን የለብኝምን?” አሉ። (ሰሂህ ቡኻሪ)

11. **አዛኝ እና ለዘብተኛ መሆን**

አቡሁረይራ(ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት ጡፈይል ኢብኑ አምር አድደውሲይ እና ጓደኞቹ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ መጡና “የደውስ ሰዎች በአላህ ላይ አምፀዋልና አላህ እንዲያጠፋቸው ዱዓ አድርግባቸው፡፡” አሏቸው፡፡ በዚህን ግዜ ሰዎች

ደውስ በቃ ጠፋች አሉ፡፡ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ግን እጃቸውን አንስተው እንዲህ አሉ “አላህ ሆይ! ደውስን ወደ ትክክለኛው መንገድ ምራት፡፡” (ሶሂህ ቡኻሪ)

12. <u>ቆንጆ እና ፅዱ ሆኖ መታየት</u>

በራዕ ኢብኑ አዚብ(ረ.ዐ) እንዲህ ብሏል፡- የረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ተክለ ሰውነት መካከለኛ ነበር፡፡ ደረታቸው ሰፋ ያለ ነበር፡፡ ፀጉራቸው እስከ ታችኛው የጆሮ ክፍል ይደርሳል፡፡ ቀይ ሙሉ ልብስ ለብሰው ነበር ያየኋቸው፡፡ ከሳቸው የበለጠ ያማረ ነገረ አይቼ አላውቅም፡፡ (ሰሂህ ቡኻሪ)

13. <u>ዱንያዊ ነገራቶች ላይ ቸልተኛ መሆን</u>

አብዱላህ ኢብኑ መስኡድ(ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፡- ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ሰሌን ላይ ተኝተው ሲነሱ ሰውነተቸው ላይ ምልክት አሳርፏል፡፡ ሰሃቦቹም ፍራሽ ነገር ብናደርግላችሁ? አሉ፡፡ ረሱልም(ሰ.ዐ.ወ) ዱንያ ምን ታደርግልኛለች፡፡ እኔ እኮ ዱንያ ላይ እንደመንገደኛ ነኝ። ትንሽን ሰዓት በዛፍ ስር እረፍት ያደርግና ተነስቶ ጥሏት ይሄዳል፡፡ (ሱነን ቲርሚዚ)

አምር ኢብነል ሀሪስ(ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፡- ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ሲሞቱ ከነጯ በቅሏቸው፣ ከጦር መሣሪያዎቻቸውና ለሰደቃ ከሰጡት መሬት በስተቀር ዲናርም፣ ዲርሀምም፣ በሪያም ይሁን ሌላ የተዉት ነገር አልነበረም፡፡(ሰሂህ ቡኻሪ)

14. <u>ከራስ በፊት ሌላን ሰው ማስቀደም</u>

ሰህል ኢብኑ ስዕድ(ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፡- አንዲት ሴት ‘ቡርዳ’ ይዛ መጣች፡፡ ረሱልም(ሰ.ዐ.ወ) “ቡርዳ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁን?” አሉ፡፡ ሰሃቦቹም “አዎን ከሱፍ የተሰራ እንደ ጋቢ ያለ ልብስ ነው፡፡” አሉ ሴትዮዋም፡- ያረሱላህ! ይህ ልብስ እርሶ እንዲለብሱት ብዬ በእጄ የሰራሁት ነው፡፡” አለች፡፡ ረሱልም(ሰ.ዐ.ወ) እሺ ብለው ተቀበሉና ለብሰውት መጡ፡፡ ከሰሃቦች አንዱም “ያረሱለላህ! ልብሱን ስጡኝ” አላቸው፡፡ ረሱልም(ሰ.ዐ.ወ) ቤት ሄደው ልብሳቸውን ቀይረው ላኩለት፡፡ ሰዎችም “አንተ ሰው ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እቃ ተጠይቀው እምቢ እንደማይሉ እያወቅክ መጠየቅህ ተገቢ አልነበረም” አሉት፡፡ ሰውየውም “በአላህ ይሁንብኝ ለሌላ ነገር ሳይሆን ስሞት ከፈን እንዲሆነኝ ብዬ ነው የጠየቅኳቸው” አለ። ሰህልም “ይህ ሰሀባ በሞተ ሰዓት በዛች ልብስ ተከፍኗል” ብለዋል፡፡ (ሰሂህ ቡኺሪ)

15. <u>በአላህ መመካት እና የእምነት ጥንካሬ</u>

አቡበከር ሲድቅ(ረ.ዐ) እንዲህ ብለዋል፡- በዋሻ ውስጥ ከረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ጋር ሆነን ሳለ የአጋሪዎችን እግር በላያችን ላይ ሁነው አየሁት፡፡ ለረሱል(ሰ.ዐ.ወ) “ያረሱለሏህ! አንደኛቸው ጎንበስ ብሎ ከእግሩ ስር ቢያይ እኮ ያገኘናል” አልኳቸው፡፡ ረሱልም(ሰ.ዐ.ወ) “አንተ አቡበከር ሆይ! ሶስተኛቸው አላህ በሆነ ሁለት ሰዎች ላይ ጥርጣሬህ ምንድነው” አሉ፡፡ (ሶሂህ ሙስሊም)

16. <u>ማዘን እና መራራት</u>

አቡ ቀታዳ(ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፡- ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ኡማማ ቢንት አበል ዓስን በትካሻቸው ላይ አድርገዋት ወደኛ መጡ። ሩኩዕ ሲያደርጉ እያስቀመጧት ሲነሱ ደግሞ እያነሷት ሰገዱ፡፡(ሰሂህ ቡኻሪ)

17. <u>ማግራራት</u>

አነስ(ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- እኔ ሰላት ማሰገድ እጀምራለሁ፡፡ ማስረዘም እፈልግና የህፃን ለቅሶ እሰማለሁ፡፡ እናትየዋ በልጇ ለቅሶ ትጨነቃለች እልና ሶላቱን አሳጥረዋለሁ፡፡ (ሱሂህ ቡኻሪ)

18. <u>አላህን(ሱ.ወ) መፍራት እና መጠንቀቅ</u>

አቡሁረይራ(ረ.ዐ) እንዳስተላለፉተ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- እኔ ወደ ቤቴ ስመለስ በፍራሽ ላይ ተምር ወድቆ አገኛለሁ፡፡ ልበላት አነሳትና ሶደቃ ትሆናለች ብዬ ሰግቼ እጥላታለሁ፡፡ (ሰሂህ ቡኻሪ)

19. <u>መለገስ</u>

አነስ ኢብኑ ማሊክ(ረ.ዐ) እንዲህ ብለዋል፡- ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) በእስልምና ላይ የተጠየቁትን ነገር ሁሉ ይሰጣሉ፡፡ አንድ ግዜ አንድ ሰው መጣና በሁለት ጋራዎች መሀል የነበሩ በጎችን ሰጡት፡፡ ሰውየውም ወደ ህዝቦቹ ተመለሰና "ወገኖቼ! እስልምናን ተቀበሉ፡፡ ሙሐመድ ድህነትን የማይፈራ ሰው አሰጣጥ ይሰጣል" አለ፡፡ (ሰሂህ ሙስሊም)

20. <u>መተጋገዝን መውደድ</u>

እናታችን አኢሻ(ረ.ዐ) ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ቤታቸው ውስጥ ምን ይሠራሉ? ተብላ ስትጠየቅ "ቤተሰባቸውን እያገዙ ይቆዩ ነበር የሰላት ሰዓት ሲደርስ ወደ መስጂድ ይወጣሉ"ብላለች፡፡ (ስኒህ ቡኻሪ)

በራዕ ኢብኑ አዚብ(ረ.ዐ) እንዲህ ብሏል፡- ረሱልን(ሰ.ዐ.ወ) የኸንደቅ ቀን የደረታቸው ፀጉር በአፈር እስኪሸፈን ድረስ ሲቆፍሩ ተመልክቻለሁ፡፡ ደረታቸው ላይ ያለው ፀጉር ደግሞ በዛ ያለ ነበር፡፡ የአብደላህ ኢብኑ ረዋሀን ግጥም የተወሰኑ ስንኞች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እያሉት ነበር፡፡

አላህ ሆይ ባንተ ባይሆን ባልተመራን ነበር፤
ባልሰገድን ሶደቃም ባላወጣን ነበር፤
መረጋጋትን በኛ ላይ አወርድልን፤
ከጠላቶቻችን ጋር ከገጠምን ፅኑ አድርገን፤
በእርግጥ ጠላቶቻችን ድንበር አልፈውብናል፤
ፈተናን ሲፈልጉ እኛ ግን እምቢ ብለናል፡፡ (ሶሂህ ቡኸሪ)

21. <u>እውነተኛነት</u>

እናታችን አዒሻ(ረ.ዐ) እንዲህ ትላለች፡- ለነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ከውሸት የበለጠ በጣም የተጠላ ነገር አልነበረም፡፡ አንድን ሰው ሲዋሽ ካዩት ተውበት ማድረጉን እስካላወቁ ድረስ እዛ ሰው ላይ ቅሬታ ይኖራቸዋል፡፡(ሱነን ቲርሚዚ)

በእውነተኛነታቸው ላይ ጠላቶቻቸው እንኳን ይመሰክሩላቸዋል፡፡ በኃይለኛ ጠላትነት የሚታወቀው አቡጃህል እንኳ አንድ ቀን እንዲህ ብሏቸዋል፡- "አንተ ሙሐመድ ሆይ! እኔ ውሸታም ነህ አላልኩም፡፡ ነገር ግን ያመጣህውን ነገር እና ሰዎችን የምትጣራበትን ነገር ክጃለሁ፡፡" በዚህ ግዜ አላህ(ሱ.ወ) የሚከተለውን የቁርዓን አንቀጽ አወረደ፡-

قَدْ نَعْلَمُ إِنَّهُ لَيَحْزُنُكَ الَّذِي يَقُولُونَ ۖ فَإِنَّهُمْ لَا يُكَذِّبُونَكَ وَلَٰكِنَّ الظَّالِمِينَ بِآيَاتِ اللَّهِ يَجْحَدُونَ [٦:٣٣]

*"እነሆ ያ የሚሉህ ነገር እንደሚያሳዝንህ በእርግጥ እናውቃለን፡፡ እነርሱም (በልቦቻቸው) አያስተባብሉህም፡፡ ግን በዳዮቹ በአላህ አንቀፆች ይክዳሉ፡፡" (አንዓም 33)*

22. <u>የአላህን ህግጋቶች ማክበር</u>

እናታችን አዒሻ(ረ.ዐ) እንዲህ ብላለች፡- ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) በሁለት ነገር መካከል ምርጫ ሲቀርብላቸው ወንጀል እስካልሆነ ድረስ ገሩን ይመርጡ ነበር፡፡ ወንጀል ከሆነ ግን እንደሳቸው የሚርቀው የለም፡፡ በአላህ ይሁንብኝ ለራሳቸው ክብር ብለው አንድንም ቀን ተበቅለው አያውቁም፡፡ የአላህ ክብር ሲነካ ግን ይበቀላሉ፡፡(ሰሂህ ቡኸሪ)

23. <u>በሻሻ ፊት</u>

አብደላህ ኢብኑ ሀሪስ(ረ.ዐ) እንዲህ ይላል፡- ከረሱል(ሰ.ዐ.ወ) የበለጠ ፈገግታን የሚያበዛ ሰው አላየሁም፡፡(ሱነን ቲርሚዚ)

24. <u>ታማኝነት እና ቃልን አክባሪነት</u>

የረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ታማኝነት ለየት ያለች ነበረች፡፡ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ዳዕዋቸውን ከጀመሩ በኋላ በጠላትነት የፈረጇቸው እንዲሁም እሳቸውንም ተከታዮቻቸውንም ሲያሰቃዩ እና ሲያንገላቱ የሚውሉት የመካ ባላባቶች እንኳን በመካከላቸው ያለው ፀብ እና አለመስማማት ሳይታያቸው አምነዋቸው አደራቸውን እየወሰዱ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ጋር ያስቀምጡ ነበር፡፡ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) በደረሰባቸው መከራ ምክንያት ወደ መዲና ሊሰደዱ በወሰኑ ግዜ አደራ መመለሻቸው ቀነ ቀጠሮ ደርሶ ስለነበር የአጎታቸውን ልጅ አልይን(ረ.ዐ) ለሶስት ቀን ወደኋላ ቀርቶ አደራዎችን ወደየባለቤቶቻቸው እንዲመልስ አዘዙት፡፡

ቃልን በማክበር በኩልም ቢሆን ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እንደዚሁ ነበሩ፡፡ በቁረይሾች እና በረሱል(ሰ.ዐ.ወ) መካከል የተደረገው የሁደይቢያ ስምምነት ግዜ ከስምምነቶቹ አንዱ "ከቁረይሾች መሀል አንድ ሰው ሰልሞ ወደ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ቢሄድ ሊመልሱት፡፡ ከነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ወደ ቁረይሽ የሸሸ ሰው ካለ ግን ላይመልሱት..." የሚል ነበር፡፡ ይህን ስምምነት ተፈራርመው ወደ መዲና ከተመለሱ በኋላ ቁረይሾች አስረውት የነበረው አቡጀንደል የተባለ ሰሃብ አምልጦ ወደ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ ይመጣል፡፡ የቁረይሽ አጋሪዎችም እሱን በመፈለግ እንዲህ ብለው መልዕክት ላኩ "የገባህልንን ቃል አታፍርስ!" ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ለአቡጀንደል እንዲህ አሉት "አንተ አቡጀንደል ሆይ ታገስ ምንዳህንም ከአላህ ፈልግ፡፡ አላህ ላንተ እና ከአንተ ጋር ላሉ ደካሞች ድል እና መውጫ መንገድ ያበጅላችኋል፡፡ እኛ ከሰዎቹ ጋር ስምምነት ተፈረራርመን ቃል ተገባብተናል፡፡ ቃልን ደግ አናፈርስም፡፡" (ሱነን በይሀቂ)

25. **ጀግንነት እና ደፋርነት**

አልይ (ረ.ዐ) እንዲህ ይላል፡- የበድር ቀን በረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እንሸሸግ ነበር፡፡ ከሁላችንም እሳቸው ለጠላት ቅርብ ነበሩ፡፡ የዛን ቀን ከሳቸው የበለጠ ጀግና አልነበረም፡፡" (ሙሰነድ ኢማሙ አህመድ)

ከጦር አውድማ ውጪ ስላለው ጀግንነታቸው አነስ ኢብኑ ማሊክ(ረ.ዐ) እንዲህ ይላል፡፡ "ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ከሰዎች ሁሉ ቆንጆ እና ጀግና ነበሩ፡፡ አንድ ለሊት የመዲና ነዋሪዎች ጩኸት ሰምታው በመደንገጥ ጩኸት ወደሰሙበት አቅጣጫ ተሰብስበው አመሩ፡፡ በመንገድ ላይ ሳሉም ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) "አይዟችሁ አትደንግጡ" እያሉ ነገሩን አጣርተው ከአቡጠልሀ በተዋሱት ፈረስ ሰይፍ አንግተው እየተመለሱ ነበር፡፡" በእርግጥም ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እንደ ውቅያኖስ ነበሩ፡፡(ሶሂህ ቡኻሪ) የመዲና ሰዎች ደንግጠው ተሰብስበው ሲወጡ እሳቸው ግን ኮርቻ በሌለው ፈረስ ወደጩኸቱ ቦታ ቀደመዋቸው ሰዎች እንዳይረበሹ ያረጋጋሉ፡፡ ሰይፍ የያዙበት ምክንያት ምናልባት ጉዳዩ መሣሪያ የሚያስፈልገው ሊሆን ስለሚችል ነው፡፡ ሌላ ሰው እንደሚያደርገው ጉዳዩን ለማጣራት ሰዎች እስኪሰበሰቡ አልጠበቁም፡፡

የኡሁድ ጦርነት ግዜ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ባልደረቦቻቸውን እያማከሩ ነበር፡፡ ሰሃቦችም እንዋጋ የሚለውን ሀሳብ አጠናከሩ፡፡ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ጦር ላለመግጠም እያሰቡ ነበር፡፡ ነገር ግን የባልደረቦቻቸውን ሀሳብ ተቀበሉ፡፡ በኋላ ሰሃቦች ረሱልን(ሰ.ዐ.ወ) ባልፈለጉት ሃሳብ ስላስገደዷቸው ተፀፅቱና ወደነብዩ መጥተው ያረሱለላህ! የምትፈልገውን ስራ፡፡ ጉዳዩን ላንተ ትተናል አሉ፡፡ ረሱልም(ሰ.ዐ.ወ) "አንድ ነብይ የጦር ልብሱን ከለበሰ በኋላ ከመጋደል ውጭ ሌላ አማራጭ የለውም" አሉ፡፡ (ሙስነድ ኢማሙ አህመድ)

26. <u>ቸርነት እና ለጋስነት</u>

ኢብኑ አባስ(ረ.ዐ) እንዲህ ይላሉ፡- ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) በጣም ቸር ነበሩ፡፡ እጅግ በጣም ቸር የሚሆኑት ደግሞ ረመዷን ውስጥ ጅብሪል በሚያገኛቸው ግዜ ነበር፡፡ ጅብሪል(ዐ.ሰ) ረመዷን ውስጥ በየሌሊቱ እየመጣ ቁርአንን ይማማሩ ነበር፡፡ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ከተላከች ንፋስ በፈጠነ መልኩ ቸር ነበሩ። (ሰሂህ ቡኻሪ)

አቡ ዘር(ረ.ዐ) እንዲህ ይላል፡- በመዲና በርሃ ላይ ከረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ጋር እየሄድን ሳለ ኡሁድ ተራራ ጋር ደረስን። "አንተ አቡ ዘር ሆይ!" አሉኝ። "አቤት" አልኳቸው። ኡሁድን የሚያክል ወርቅ ቢኖረኝ አንድ ዲናር እንኳን አንድ ወይም ሶስት ለሊት እኔ ዘንድ እንዲቀመጥ አልፈልግም። በአላህ መንገድ የምጠቀመው አልያም ለአላህ ባሪያዎች የምሰጠውን ይህን ይህን ይህን የሚያክል ሲቀር(በቀኛቸው፣ በግራቸው፣ እና ከኋላቸው አሰመሩ።) (ሰሂህ ቡኻሪ)

ጃቢር ኢብኑ አብደላህ(ረ.ዐ) እንዲህ ይላል፡- ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) አንድንም ነገር ተጠይቀው እምቢ ብለው አያውቁም፡፡ (ሶሂህ ቡኻሪ)

27. <u>አይናፋርነት</u>

አቡሰኢድ አልኹድሪ(ረ.ዐ) እንዲህ ይላል፡- ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) በጫጉላ ላይ ካለች ድንግል የበለጠ አይናፋር ነበሩ፡፡ የሚጠሉትን ነገር ሲያዩ በፊታቸው ላይ እናውቅ ነበር፡፡ (ሰሂህ ቡኻሪ)

28. <u>መተናነስ</u>

ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) በጣም የሚተናነሱ ሰው ነበሩ፡፡ በጣም ከመተናነሳቸው የተነሳ አንድ ሰው መስጂድ ሲገባ ከባልደረቦቻቸው መለየት ይከብደው ነበር፡፡

አነስ ኢብኑ ማሊክ(ረ.ዐ) እንዲህ ይላሉ፡- መስጂድ ውስጥ ከረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ጋር ተቀምጠን ሳለ አንድ ሰው ግመሉን ይዞ መጥቶ መስጂድ ውስጥ አሰረው፡፡ ከዛም "ከናንተ መሀል ሙሐመድ ማነው?" አለ፡፡ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) በመሀላችን ደገፍ ብለው ተቀምጠው ነበር፡፡ "ይህ ደገፍ ብሎ የተቀመጠው ነጩ ሰው ነው አልነው፡፡" (ሲሂህ ቡኽሪ)

ይህ የተከሰተበት ምክንያት ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ከባልደረቦቻቸው እና ከአቀማማጮቻቸው ስለማይለዩ ነው፡፡

ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ከደካሞች፣ ከምስኪኖች እና ከባለጉዳዮች ጋር ጉዳዮቻቸውን ለማስፈጸም አብሮ ለመሄድ አይኮሩም ነበር፡፡ አነስ(ረ.ዐ) እንዲህ ብሏል፡- ከመዲና ሴቶች አንዷ የሆነ ነገር አሳስቧት ለረሱል(ሰ.ዐ.ወ) "የማዋይህ ሚስጥር አለኝ" አለቻቸው፡፡ ረሱልም(ሰ.ዐ.ወ) "አንቺ እገሊት ሆይ የፈለግሽውን የመዲና ጎዳና ምረጪ እና ጉዳይሽን ልትነግሪኝ ትችያለሽ" አሏት፡፡ ከዛም አብረው ሄደው የሆነ መንገድ ላይ ጉዳይዋን ፈፅመውላት ተመለሱ፡፡(ሶሂህ ሙስሊም)

29. <u>ርህራሄ እና እዝነት</u>

አቢ መስኡድ አልአንሳሪ(ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፡- አንድ ሰውዬ ወደ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ መጣና፡- "አንቱ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እገሌ ሲያሰግድ ስለሚያስረዝም ከሱብሂ ሰላት ለመቅረት እየተገደድኩኝ ነው፡፡" አላቸው፡፡ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እንደዛ ቀን በጣም ተቆጥተው መክረው አያውቁም፡፡ "እናንተ ሰዎች ሆይ ከናንተ መሀል አባራሪዎች አሉ፡፡ ማንኛችሁም ብትሆኑ ሰዎችን ስታሰግዱ አሳጥሩ፡፡ በሰዎች መሀል ሽማግሌ፣ ደካማ እና ባለጉዳይ ይኖራል፡፡" (ሶሂህ ቡኻሪ)

ኡስማ ኢብኑ ዘይድ(ረ.ዐ) እንዲህ ይላሉ፡- ከረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ጋር አብረን እያለን ከልጃቸው መሀል አንዷ ልጇ በሞት ጣር ላይ በመሆኑ እንዲመጡላት መልክተኛ ላከች፡፡ ረሱልም ለመልክተኛው "ሂድ እና የሰጠውም ሆነ የወሰደው ያአላህ እንደሆነና ሁሉም ነገር እሱ ዘንድ በቀነገደብ እንደሆነ ንገራት፡፡ እንድትታገስ እና ምንዳዋን ከአላህ እንድትፈልግም እዘዛት" አሉት፡፡ እንደሚመጡላት ምላ እንደገና መልክተኛ ላከች፡፡ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ከሰዓድ ኢብኑ ኡባዳ እና ከሙአዝ ኢብኑ ጀበል ጋር በመሆን አብረው ሄዱ፡፡ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ልጁን አቅፈውት ነፍሱ ሲንቀጠቀጥ ባዩ ግዜ አነቡ፡፡ ሰዓድም "ያረሱለላህ ይህ ምንድነው?" አላቸው፡፡ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) "ይህማ አላህ በባሮቹ ልብ ውስጥ ያደረገው እዝነት ነው፡፡ አላህ ከባሪያዎቹ የሚያዝንላቸው አዛኞችን ነው፡፡"(ሶሂህ ቡኻሪ)

30. <u>ይቅር ባይነት እና መበቀል እየቻሉ መታገስ</u>

አነስ ኢብኑ ማሊክ እንዳስተላለፉት፡- አንድ ግዜ ከነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ጋር አብረን እየሄድን ከነጅራን የመጣ ወፍራም አንገትዬ ያለው ኩታ ለብሰው ነበር፡፡ አንድ ገጠሬ መጣና ምልክት እያኪያወጣባቸው ድረስ አንገታቸውን በልብሳቸው አንቋቸው "አንተ ጋር ካለው የአላህ ገንዘብ(እንዲሰጡኝ) እዘዝልኝ" አላቸው፡፡ ረሱልም (ሰ.ዐ.ወ) ሳቅ አሉና እንዲሰጠው አዘዙለት፡፡

ስለታጋሽነታቸው ሌላው ምሳሌ የዘይድ ኢብኑ ሰዕና ሐዲስ ነው፡፡ ይህ ሰው የአይሁድ ሊቃውንት ነበር፡፡ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ከዚህ አይሁድ የተወሰነ ብድር ተበድረውት ነበር፡፡ ዘይድ እንዲህ ይላል፡- "ብድር መመለሻው ቀን ከመድረሱ 2 ወይም 3 ቀን በፊት ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) አንድ የአንሷር ሰው ሞቶ ሊቀብሩ ወጡ፡፡ ከሳቸው ጋር አቡበከር፣ ኡመር፣ ኡስማንና የተወሰኑ ሰሃቦች አሉ፡፡ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ሰላተል ጀናዛ ከሰገዱ በኋላ ወደ ግርግዳው ጠጋ ብለው ተደገፉ፡፡ የልብሳቸውን ጫፍ ይዤ ኮስተር ባለ ፊት "አንተ ሙሐመድ! ገንዘቤን አትመልስልኝም? በአላህ ይሁንብኝ እናንተ የበኒ አብዱል ሙጠሊብን ሰዎች አውቃችኋለሁ፡፡ ብድርን ማዘግየት ትወዳላችሁ!!" አልኳቸውና ወደ ኡመር ዘወር ብዬ ባይ አይኑ ልክ እንደተወርዋሪ ኮከብ በፊቱ ላይ ይጉረጠረጣል፡፡ ከዛም እንዲህ አለኝ "አንተ የአላህ ጠላት ለረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ጆሮዬ የሚሰማውን ነገር ትናገራለህን፤ አይኔ የሚያየውን ነገር ትሰራለህን!! ያመልጠኛል ብዬ የምሰጋው ነገር(ጀነት) ባይኖር በሰይፌ አንገትህን እቀነጥስልህ ነበር፡፡ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ወደ ኡመር ረጋ ባለመንፈስ እየተመለከቱ "ዑመር ሆይ እኛ ካንተ የምንጠብቀው ሌላን ነገር ነበር፡፡ እኔን እዳየን እንድመልስ እሱም ስርዓት ባለው አጠያየቅ እንዲጠይቅ ማደረግ ነበረብህ፡፡ በል አሁን ይዘሀው ሂድና ሀቁን ስጠው ያስፈራራህበትን ካሳ ደግሞ 20 ቁና ጨምርለት፡፡"

ዘይድ እንዲህ ይላል "ኡመር ይዞኝ ሄደ እና ገንዘቤን ሰጥቶኝ 20 ቁና ቴምር ጨመረልኝ፡፡" ይህ ጭማሪ ምንድነው?" አልኩት፡፡ ዑመርም "ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ስላስፈራራሁህ እንድከስህ አዝዘውኝ ነው፡፡" አለ፡፡

ዘይድም፡- ዑመር ሆይ ለመሆኑ ታውቀኛለህን?

ዑመር፡- አላውቅህም፡፡ አንተ ማነህ?

ዘይድ፡- እኔ ዘይድ ኢብኑ ሰዕና ነኝ

ዑመር፡- የአይሁዱ ሊቅ ዘይድ ነህን?

ዘይድ፡- አዎን

ዑመር፡- ረሱልን(ሰ.ዐ.ወ) የተናገርካቸውንም ሆነ የሰራህባቸውን እንድትፈፅም የገፋፋህ ነገር ምንድን ነው?

ዘይድ፡- ረሱልን(ሰ.ዐ.ወ) ባየኋቸው ሰዓት ሁሉንም የነብይነት ምልክቶች ተመልክቼ ነበር፡፡ ነገር ግን ሁለት ምልክቶች ቀርተውኝ ነበር፡፡ እነሱም "ትዕግስቱ አለማወቁን ይቀድማል፡፡ እሱ ላይ የሚሰራበት የመሀይማን ተግባራት ትዕግስትን እንጂ ሌላን አይጨምረውም፡፡ አሁን ሁለቱንም አግኝቻቸዋለሁ፡፡ ዑመር ሆይ አንተ ምስክር ሁነኝ እኔ በእርግጥም በአላህ አምላክነት፣ በእስልምና ሀይማኖትነት እና በሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) ነብይነት ወድጃለሁ፡፡ አሁንም አንተ ምስክር ሁነኝ የንብረቴን ግማሽ ለሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) ተከታዮች በሙሉ ሰጥቻለሁ፡፡"

ዑመር፡- ሁሉንም እንኳን ስለማታዳርስ በተወሰኑት ላይ በል፡፡

ዘይድ፡- እሺ በተወሰኑት ላይ፡፡

ከዛም አብረው ወደ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ ተመለሱና ዘይድ፡- "ከአላህ በቀር ሌላ የሚመለክ አምላክ እንደሌለና ሙሐመድም የእሱ ባሪያውና መልክተኛው እንደሆነ እመሰክራለሁ" አለ፡፡ ከዛም በኋላ እምነቱ ጠንክሮ ከረሱል(ሰ.ዐ.ወ)

ጋር በመሆን ብዙ ዘመቻዎች ላይ ተሳትፏል፡፡ በመጨረሻም በተቡክ ዘመቻ ላይ ሳያፈገፍግ ተጋድሎ ተሰውቷል፡፡ ዘይድን አላህ ይዘንለት፡፡(ሶሂህ ኢብኑ ሂባን)

ምናልባትም ትልቁ የረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ይቅር ባይነት መረዳት የሚቻለው መካን በድል ከፍተው ሲገቡ የመከራን አይነት አውርደውባቸው ለነበሩት እና ከሀገራቸው አባረዋቸው ለነበሩት የመካ ሰዎች ምን እንዳሏቸው ስንመለከት ነው፡፡ "ምን የማደረጋችሁ ይመስላችኋል" አሏቸው፡፡ እነሱም "ጥሩን ነገር ነው የምንጠብቀው አንተ አዛኝ ወንድም ነህ፡፡ የአዛኝ ወንድማችን ልጅ ነህ" አሉ፡፡ ረሱልም(ሰ.ዐ.ወ) "ሂዱ ከዚህ በኋላ ነፃ ናችሁ" አሏቸው፡፡

31. **ታጋሽነት**

ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ለታጋሽነት ምሳሌ ነበሩ፡፡ ዳዕዋቸውን ከመጀመራቸው በፊት ወገኖቻቸው በሚሰሩት የመሀይማን ተግባር ይታገሱ ነበር፡፡ በይፋ ጥሪያቸውን ከጀመሩ በኋላ በመካ ከገጠማቸው ድብደባ፣ መከራ እና እንግልት እንዲሁም በሁለተኛ ደረጃ በመዲና ከሙናፊቆች ጋር ባላቸው ግንኙነት ከአላህ ምንዳቸውን በመፈለግ ትዕግስት አድርገው አሳልፈዋል፡፡ የሚወዷቸውን ሰው ሲያጡ ትዕግስት በማድረግ ላይም ታላቅ ምሳሌ ናቸው፡፡ ባለቤታቸው ኸድጃ ሞተችባቸው፣ ልጆቻቸው ከፋጢማ በቀር ሁሉም እሳቸው በሕይወት እያሉ ሞቱ፣ አጎታቸው አባስ ሞተ በእነዚህ ሁሉ አጋጣሚዎች ሁሉ ታጋሽ እና ምንዳቸውን ከአላህ የሚፈልጉ ነበሩ፡፡

አነስ ኢብኑ ማሊክ(ረ.ዐ) እንዲህ ይላሉ፡- የረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ወንድ ልጃቸው ኢብራሂም ተንከባካቢ ወደነበረው አቢሰይፍ አልቀይን ዘንድ ከረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ጋር አብረን ገባን፡፡ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ኢብራሂምን አቀፉትና ሳሙት፡፡ ከዛ በኋላ የኢብራሂም ነፍስ እየታገለች ሳለ ተመልሰን ገባን፡፡ የረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ዓይኖች እምባ ያጎርፍ ጀመር፡፡ አብዱራህማን ኢብኑ አውፍ "ያረሱለላህ አንተም!" አላቸው፡፡ ረሱልም(ሰ.ዐ.ወ) "አንተ የአወፍ ልጅ ሆይ ይህ እኮ እዝነት ነው፡፡ አይን ታለቅሳለች፡፡ ልብም ያዝናል አላህን የሚያስደስት ነገር እንጂ አንናገርም፡፡ ኢብራሂም ሆይ አንተን በመለየት በጣም አዝነናል፡፡" (ሰሂህ ቡኻሪ)

32. **ፍትሀዊነት**

ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) በሁሉም የሕይወታቸው ዘርፍ ላይ ፍትሀዊ ነበሩ፡፡ ሸሪዓን በመተግበር ላይም ፍትሀዊ ነበሩ፡፡ እናታችን አዒሻ(ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፡- አንዲት የመኽዙም ጎሳ አባል የሆነች ሴት ሰርቃ ጉዳዩ የቁረይሽን ሰዎች አሳሰባቸው፡፡ "ማንነው ስለሷ ረሱልን(ሰ.ዐ.ወ) የሚሸመግልልን? ብለው ጠየቁ፡፡ ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ወዳጅ ከኡሳማ ቢን ዘይድ ውጪ የሚደፍር ሰው የለም ተባባሉ፡፡ ኡሳማ ረሱልን መጥቶ ሲያናግራቸው እንዲህ አሉት፡- "በአላህ ውሳኔ ላይ ሽምግልና ትመጣለህን?" ከዛም ተነስተው ንግግር አደረጉ "ከናንተ በፊት የነበሩት ሰዎች የጠፉበት ምክንያት ከነሱ መካከል የተከበረ ሰው ሲሰርቅ ይተውታል፡፡ ደካማ የሆነ ሰው ሲሰርቅ ግን ድንጋጌውን ይፈፅሙበታል፡፡ በአላህ ይሁንብኝ የሙሐመድ ልጅ ፋጢማ እንኳን ብትሰርቅ እጇን ከመቁረጥ ወደኋላ አልልም፡፡" (ሶሂህ ቡኻሪ)

የረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ፍትሀዊነት በራሳቸውም ላይ ጭምር ነበር፡፡ ኡሰይድ ኢብኑ ሁደይር(ረ.ዐ) እንዲህ ይላል፡- አንድ ከአንሷር የሆነ ሰው ሰዎች በተሰበሰቡበት ቀልድ እየተናገረ ያስቃቸዋል፡፡ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) መጡና በያዙት እንጨት ሽንጡ ላይ መታ አደረጉት፡፡ እሱም "ካሳ ስጡኝ" አለ፡፡ እሳቸውም በል እሺ አሉት፡፡ እሱም "ያረሱለላህ፡- ሲመቱኝ ግዜ እኔ ላይ ልብስ አልነበረም አንቱ ላይ ቀሚስ አለ" አላቸው። ልብሳቸውን ከፍ ሲያደርጉለት ቶሎ ሄዶ ሳማቸው፡፡ "ያረሱለላህ እኔ የፈለኩት ይህን ነበር" አላቸው፡፡ (ሱነን አቡዳውድ)

33. **አላህን መፍራት**

ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ከሰዎች በተለየ መልኩ አላህን በጣም ይፈሩ ነበር፡፡ አብደላህ ኢብኑ መስኡድ እንዲህ ይላል፡፡ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) "በኔ ላይ ቅራብኝ" አሉኝ፡፡ እኔም "ያረሱለላህ! ቁርአን አንቱ ላይ ወርዶ በአንቱ ላይ እቀራለሁኝን?" አልኩኝ፡፡ እሳቸውም "አዎን" አሉ፡፡ ሱረቱ ኒሳዕን አነበብኩኝ፡፡ *"ከሕዝቦችም ሁሉ መስካሪን ባመጣን ጊዜ አንተንም በእነዚህ ላይ መስካሪ አድርገን ባመጣን ጊዜ(የከሃዲዎች ሁኔታ) እንዴት ይሆን?"* የሚለው አንቀፅ ጋር ስደርስ "እዚህ ላይ ይብቃህ" አሉኝ፡፡ ወደ እሳቸው ቀና ብል ግዜ አይናቸው እያነባች ነበር፡፡" (ሰሂህ ቡኻሪ)

እናታችን አዒሻ(ረ.ዐ) እንዲህ ትላለች፡- ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ደመናን ባዩ ግዜ ይሄዳሉ፣ ይመለሳሉ፡፡ ይወጣሉ ይገባሉ፡፡ ፊታቸውም ይለዋወጣል፡፡ ዝናብ የዘነበ ግዜ ጭንቀታቸው ይሄዳል፡፡ ይህንን ጉዳይ አዒሻ(ረ.ዐ) ስትጠይቃቸው ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ፡፡ "አላውቅም፤ ምናልባትም *"ሸለቆዎቻቸውን ተቅጣጪ አግዳሚ ደመና ኾኖ ባዩትም ጊዜ "ይህ አዝናቢያችን የኾነ ደመና ነው" አሉ፡፡ (ሁድም) "አይደለም፤ እርሱ ያ በእርሱ የተቻኮላችሁበት መዐት ነው፡፡ በውስጧ አሳማሚ ስቃይ ያለበት ነፋስ ናት፡፡"* እንደተባለው ይሆናል ብዬ ነው፡፡" ሶሂህ ቡኻሪ

34. <u>**በራስ መብቃቃት**</u>

ኡመር ኢብኑል ኸጣብ እንዲህ ይላሉ፡- የረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ቤት ገባሁ፡፡ ምንም ያልተነጠፈበት ሰሌን ላይ ተኝተዋል፡፡ ትራሳቸው የተጠቀጠቀው ከገለባ ነው፡፡ ከግርጌያቸው በኩል በእቃ የተቀመጠ ውሃ አለ፡፡ ከራስጌያቸው በኩል ደግሞ የተንጠለጠለ ልብስ አለ፡፡ ይህንን ስመለከት አለቀስኩኝ፡፡ "ምንድነው የሚያስለቅስህ?" አሉኝ፡፡ እኔም "ቂሳርና ኪስራ እንደዛ በዱንያ እየተንደላቀቁ አንተ ግን የአላህ መልክተኛ ሁነህ እንደዚህ?" ረሱልም (ሰ.ዐ.ወ) የእነሱ እጣ ዱንያ ሆኖ ለኛ ደግሞ አኼራ መሆኑ አያስደስትህምን?" አሉ፡፡ (ቡኻሪ)

35. <u>**ለሰዎች ጥሩ ነገር መመኘት፡፡ ለጠላቶቻቸውም እንኳን ቢሆን**</u>

የአላህ መልዕክተኛ ባለቤት ዓኢሻ(ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፡- ለረሱል(ሰ.ዐ.ወ) "ከኡሁድ ቀን የባሰ መጥፎ ቀን አጋጥሞህ ያውቃልን?" ብዬ ጠየቅኳቸው፡፡ "ከሕዝቦችሽ የመከራ አይነት ደርሶብኛል፡፡ ከዛ ውስጥ አስከፊው ቀን ግን እራሴን ለኢብን አብድ ያለይል ኢብን ኪላል ያቀረብኩኝ ቀን ነው፡፡ ወደፈለኩት ነገር አልተቀበለኝም፡፡ በጣም አዝኜ ተመለስኩኝ፡፡ 'ቀርን አሰዓሊብ' የሚባል ቦታ እስከምደርስ ድረስ እራሴን አላውቅም ነበር፡፡ ራሴን ቀና ባደርግ ደመና አስጠልሎኛል፡፡ ወደ ደመናው ስመለከት ጅብሪልን በውስጡ አየሁት፡፡ "አላህ ህዝቦችህ ያሉህን ነገር ሰምቷል፡፡ የተራራን መላኢካ የፈለግከውን ነገር እንድታዘው ልኮልሀል፡፡" የተራራው መላኢካም ጠራኝና ሰላምታ አቀረበልኝ፡፡ ከዛም "አንተ ሙሐመድ ሆይ! የምትፈልገውን ነገር እዘዘኝ፣ ከፈለክ እነዚህን ሁለት ተራራዎች አንስቼ በላያቸው ላይ ላጣብቅልህ?" ረሱልም(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉት "አይሆንም ተው፡፡ ከልጆቻቸው ውስጥ አላህን በብቸኝነት የሚገዛ በሱም ምንም የማያጋሩ ሰዎች አላህ እንዲያወጣልኝ ምኞቴ ነው፡፡" (አልቡኻሪ)

አብደላህ ኢብኑ ዑመር እንዲህ ይላል "አብደላህ ኢብን ኡበይ ኢብን ሰሉል የሞተ ግዜ፤ ልጁ አብደላህ ወደ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ መጣና አባቱን ለመከፈኛ ቀሚሳቸውን እንዲሰጡት ጠየቃቸው፡፡ እሳቸውም ሰጡት፡፡ ከዛም እንዲሰግዱበት ጠየቃቸው፡፡ ረሱልም(ሰ.ዐ.ወ) ሊሰግዱበት ተነሱ፡፡ ዑመር(ረ.ዐ) ልብሳቸውን እየጎተተ "ያረሱለላህ! አላህ ከልክሎህ ሳለ ልትሰግድበት ነው እንዴ!" አላቸው፡፡ ረሱልም(ሰ.ዐ.ወ) "አላህ እኮ አማርጦኛል፡፡" *"ለእነርሱ ምሕረትን ለምንላቸው፤ ወይም ለእነርሱ ምህረትን አትለምንላቸው፡፡ ለእነርሱ 70 ግዜ ብትለምንላቸው አላህ ለነሱ በፍፁም አይምርም"* ስለዚህ እኔ ከ70 በላይ እጨምራለው" አሉ፡፡ ኡመርም "እሱ እኮ ሙናፊቅ ነው" አለ፡፡ ከዛም ከሰገዱበት በኋላ አላህ የሚከተለውን አወረደ *"ከእነሱም በአንድም በሞተ ሰው ላይ ፈፅሞ አትስገድ፡፡ በመቃብሩም ላይ አትቁም..." (ሰሂህ ቡኸሪ)*

## ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ስነስርዓት መካከል የተወሰኑት

1. **ከባልደረቦቻቸው ጋር ያላቸው ቅርርብ እና ከእነርሱ ጋር መቀላቀላቸው**

   ይህ ግልፅ ነገር ነው፡፡ ምክንያቱም የረሱልን(ሰ.ዐ.ወ) የሕይወት ታሪክ ከላይ ስለዘረዘርነው። ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) በሕይወት ጉዳያችን በሙሉ ምሳሌ ልናደርጋቸው የሚገባ ሰው ናቸው፡፡ ጀሪር ኢብኑ አብደላህ(ረ.ዐ) እንዲህ ይላል ከሰለምኩኝ ግዜ ጀምሮ አንድቀንም ይሁን ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ከልክለውኝ አያውቁም፡፡ ሁሌም ሲያገኙኝ ፈገግ ይላሉ፡፡ ፈረስ መጋለብ እንደሚከብደኝ ስነግራቸው፤ ደረቴን መታ መታ አድርገው "አላህ ሆይ አደላድለው ሰዎችን ወደ ቅናቻ የሚመራ ሰውም አድርገው፡፡" (ሶሂህ ቡኻሪ)

   ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ከባልደረቦቻቸው ጋር ይዝናኑ እና ይቀላለዱ ነበር፡፡ አነስ ኢብኑ ማሊክ(ረ.ዐ) እንዲህ ይላል፡- ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) በመልካም ስነምግባር ወደር አልነበራቸውም፡፡ አቡ ኡመይር የሚባል ታናሽ ወንድም ነበረኝ፡፡ (ጡት የጣለ ልጅ ነው ያለ ይመስለኛል)፡፡ የሚጫወትባት ኑገይር የምትባል ትንሽ ወፍ ነበረችው፡፡ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ሲያገኙት "አንተ አቡ ኡመይር ሆይ ኑገይር ምን ሰራች?" እያሉ ያጫውቱት ነበር፡፡ (ሰሂህ ሙስሊም)

   ቀልዶቻቸው በንግግር ብቻ የተወሰኑ ሳይሆን አንዳንዴ በተግባርም ነበር፡፡ አነስ ኢብኑ ማሊክ እንዳስተላለፉትት- አንድ ዛሂር ቢን ሀራም የሚባል የገጠር ሰው ነበር፡፡ ለረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ስጦታ ያመጣላቸው ነበር፡፡ አንዳንድ ነገራቶችንም ያበጅላቸው ነበር፡፡ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) "ዛሂር የኛ ገጠራችን ነው፤ እኛም የሱ ከተማ ነን" ይሉ ነበር፡፡አንድ ግዜ ዛሂር ገበያ ውስጥ እቃውን እየሸጠ ሳለ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ከጀርባው ሄደው ሳያያቸው አቀፉት፡፡ እሱም "ማነው የያዘኝ ልቀቀኝ" አለ፡፡ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) መሆናቸውን ሲያውቅ ጀርባውን ከደረታቸው አስጠግቶ መተሻሸት ጀመረ፡፡ ረሱልም(ሰ.ዐ.ወ) "ይህን ባሪያ የሚገዛኝ ማን ነው?" አሉ እሱም አንተ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ እኔ እርካሽ ነኝ እንዴ? አለ። ረሱልም(ሰ.ዐ.ወ) "አላህ ዘንድ ግን በጣም ውድ ነህ፡፡" አሉት (ሰሂህ ኢብኑ ሂባን)

2. **ባልደረቦቻቸውን ያወያያሉ፡፡ ቁርአን ያልወሰነበት ጉዳይ ከሆነ የነሱን ሀሳብ ይተገብራሉ፡፡**

   አቡሁረይራ(ረ.ዐ) እንዲህ ይላል፡- ከረሱል(ሰ.ዐ.ወ) የበለጠ ባልደረቦቹን የሚያዋይ ሰው አልተመለከትኩም፡፡(ሱነን ቲርሚዚ)

3. **ሙስሊምም ይሁን ካፊር የታመመን መጠየቅ**

   ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ስለባልደረቦቻው "እገሌ የት ጠፋ?" እያሉ ይጠይቁ ነበር፡፡ እንደታመመ ካወቁ አብረዋቸው ካሉ ሰሃባ ጋር ለመጠየቅ ይቻኮላሉ፡፡ ሲጠይቁ ደግሞ ሙስሊም የሆኑትን ብቻ ሳይሆን ሙስሊም ያልሆኑትንም ጭምር ነበር፡ አነስ ኢብኑ ማሊክ(ረ.ዐ) እንዳስተላለፈው፡- አንድ ረሱልን(ሰ.ዐ.ወ) ያገለግል የነበረ አይሁድ ልጅ መታመሙን ሰሙ፡፡ ለባልደረቦቻቸው እንሂድ እና እንጠይቀው ብለው ተነሱ፡፡ እቤቱ ሲገቡ አባቱ ከራስጌው በኩል ተቀምጦ ነበር፡፡ ረሱልም(ሰ.ዐ.ወ) "የውመል ቂያማ ሸማግሌ እንድሆንህ 'ላኢላሀ ኢለላህ' በል" አሉት፡፡ ልጁም ወደአባቱ ዞሮ መመልከት ጀመረ፡፡ አባትየውም "አቡል ቃሲም የሚልህን ነገር ስማ" አለው፡፡ ልጁም "ከአላህ በቀር የሚመለክ አምላክ አለመኖሩንና ሙሐመድም የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን እመሰክራለሁ፡፡" አለ፡፡ ረሱልም(ሰ.ዐ.ወ) "ከጀሀነም እሳት ላዳነው አላህ ምስጋና ይገባው" አሉ፡፡(ሰሂህ አብኑ ሂባን)

4. **ጥሩ የዋለልህን ሰው ማመስገን እና ውለታን መመለስ**

ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- "በአላህ ስም ጥበቃን የፈለገን ሰው ጠብቁት፣ በአላህ ስም የጠየቀን ስጡት፣ የጋበዛችሁን ሰው ግብዣውን አክብሩ፣ መልካም ነገርን የዋለላችሁን ሰው ውለታውን መልሱ፣ የምትመልሱበት ነገር ካላገኛችሁ ውለታውን መመለሳችሁን እስኪታውቁ ድረስ ዱዓ አድርጉለት፡፡(ሙስነድ ኢማሙ አህመድ)

እናታችን ዓኢሻ(ረ.ዐ) እንዲህ ትላለች፡- ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ስጦታን ይቀበሉ ነበር መልሰውም ይሰጡ ነበር፡፡ (ሰሂህ ቡኻሪ)

5. **ጥሩ እና ቆንጆ ለሆነ ነገር ያላቸው ውዴታ**

አነስ(ረ.ዐ) እንዲህ ይላል፡- የረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እጅ ነክቼ ከማውቃቸው ሀር ሁሉ የበለጠ ለስላሳ ነው፡፡ ጠረናቸውም አሸትቸው ከማውቀው ሽቶ የበለጠ ነው፡፡(ሰሂህ ቡኻሪ)

6. **ለበጎ ስራ እና በጥሩ ነገር ሜዳ ላይ ገብተው ለመሽምገል ያላቸው ጉጉት**

ኢብኑአባስ(ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት "የቡረይራ ባል ሙጊስ የሚባል ባሪያ ነበር፡፡ ከኋላ ከኋላ እየተከተላት ጺሙ እስኪረጥብ ድረስ እያለቀሰ ይለምናት ነበር፡፡ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ለዓባስ አንተ አባስ ሆይ ሙጊስ ለቡረይራ ያለው ፍቅር፤ በተቃራኒው ደግሞ ቡረይራ ለሙጊስ ያላት ጥላቻ አያስገርምህምን?" ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ለቡረይራ "ምናለበት እሺ ብትይው" አሏት፡፡ እሷም "እያዘዙኝ ነውን?" አለች፡፡ ረሱልም(ሰ.ዐ.ወ) "አይ አይደለም፡፡ ሽምግልና ነው፡፡" አሏት፡፡ እሷም "ለሱ ምንም አይነት ፍላጎት የለኝም" አለች፡፡ (ቡኻሪ)

7. **እራሳቸውን ማገልገል**

እናታችን አዒሻ(ረ.ዐ) "ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ቤት ውስጥ ምን ምን ስራ ይሰራሉ?" ተብላ ስትጠየቅ "ልክ እንደ ሰው ናቸው፡፡ ልብሳቸውን ያጥባሉ፣ ፍየላቸውን ያልባሉ፣ እራሳቸውን ያስተናግዳሉ፡፡" (ሙስነድ ኢማሙ አህመድ)

ኸረ እንደውም የስነምግባራቸው ማማር እና የትህትናቸው ከራሳቸው አልፎ ሌላን ሰው ያገለግላሉ፡፡አዒሻ(ረ.ዐ) ረሱል ቤት ውስጥ ስለሚሰሩት ስራ ስትጠየቅ እንዲህ ትላለች "ቤተሰቦቸውን እያገዙ ይቆዩና አዛን ሲሰሙ ለሰላት ይወጣሉ፡፡" (ቡኻሪ)

## <u>ፍትሃዊ ምስክሮች</u>

- ጀርመናዊው ገጣሚ ጉተህ እንዲህ ይላል፡- በታሪክ ማዕድ ውስጥ የሰው ልጆችን ምርጥ ፈለግኩኝ፡፡ የአረቡ ነብይ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) ሆኖ አገኘሁት፡፡
- ፕሮፌሰር ኬይዝ ሙር The developing Human በሚለው መፅሀፉ ውስጥ እንዲህ ይላል፡- ቁርአን የአላህ ንግግር መሆኑ ምንም ዓይነት ጥርጥር የለኝም፡፡ በቁርአን ውስጥ የተጠቀሰው የሽል ገለፃ በሰባተኛ ክፍለ ዘመን በነበረው ሳይንሳዊ እውቀት ሊገለጽ አይችልም፡፡ ብቸኛው የሚያሳምነን እና ማምለጫው መንገድ እነዚህ ገለፃዎች ከአላህ ወደ ሙሐመድ የወረዱ መሆናቸው ነው፡፡
- ወውል ዳውራንት የስልጣኔ ታሪክ በመለው መፅሀፍ ውስጥ እንዲህ ይላል፡- "ስለ አንድ ሰው ትልቅነት በሰዎች ዘንድ ባለው ከበሬታ የምንወስን ከሆነ የኢስላም ነብይ የታላቆች ሁሉ ታላቅ ነው፡፡ ጠርዘኛነትን እና ሽወዳዎችን አስወግዷል። ከክርስትናም፣ ከአይሁድም ሆነ እዛ አገር ከነበሩ ሌላ ሀይማኖተች የበለጠ ግልጽ፣ ገር እና ጠንካራ የሆነ ሀይማኖት አቋቁሟል፡፡ እስከዛሬ ድረስም የሱ ሀይማኖት አስተማማኝ በሆነ ጥንካሬ ላይ ይገኛል፡፡
- ጆርጅ ዶይ "ህይወት" በሚለው መጽሀፉ ውስጥ እንዲህ ይላሉ፡- በሙሀመድ መልዕክተኛነት መጠራጠር ማለት ነገራቶችን ሁሉ በሚያስተናብረው የፈጣሪ ሀይል መጠራጠር ማለት ነው፡፡

- አለም ዌልዝ “እውነተኛው ነብይ” በሚለው መፅሀፉ ውስጥ እንዲህ ይላል፡- ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) እውነተኛ ለመሆናቸው ግልጽ ማስረጃ መጀመሪያ ያመኑት ሰዎች ቤተሰቦቹ እና ቅርብ የሆኑ ሰዎች መሆናቸው ነው፡፡ ስለሱ ሚስጥራዊ ነገር ሁሉ እነሱ በደንብ ያውቃሉ፡፡ በእውነትኝነቱ ላይ ትንሽ ጥርጣሬ ቢኖራቸው አያምኑለትም ነበር፡፡
- ኦሪየንታሊስቱ ሄል የአረብ ስልጣኔ በሚለው መፅሀፉ ውስጥ እንዲህ ይላል፡- በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ እስልምና በተስፋፋበት ፍጥነት የተስፋፋ ሀይማኖቶ ታይቶ አይታወቅም፡፡ በእርግጥም ሙሐመድ ለዚህ ዓለም ሕዝቦችን አፍርቷል፤ በምድር ላይ አላህ እንዲመለክ አመቻችቷል፤ የሕዝቦችን እኩልነት ፅንሰ ሀሳብ ጠንስሷል፤ ከእረብሻ እና ፉክክር ውጪ ምንም የማያውቁ በነበሩ ሕዝቦች ላይ ስርዓትን፣ መረጋጋትን፣ መከባበርን እና ልቅናን አስፍኗል፡፡
- የስፔኑ ኦሪየንታሊስት ጃን ሌክ ‘The Arabs’ በሚለው መጽሀፉ ውስጥ እንዲህ ብሏል፡- የሙሐመድን ሕይወት አላህ በቁርዓን ከገለፀው በላይ ማብራራት አይቻልም፡-*“(ሙሐመድ ሆይ!) ለዓለማትም እዝነት ሊደርገን እንጂ አልላክንህም።”* (አንቢያ 107)

  በእርግጥም ሙሐመድ ትክክለኛ እዝነት ነው፡፡ እኔም በናፍቆት ስሜት “ሰለዋት” አወርድባቸዋለሁ፡፡
- በርናርድሾው እስልምና ከ100 ዓመታት በኋላ በሚለው መጽሀፉ ውስጥ እንዲህ ይላል፡- በዚህ ዓለም ያለሰው ሁሉ እስልምናን ይቀበላል፡፡ በግልጽ በትክክለኛ ስሙ ባይቀበሉት እንኳን በሌላ መልኩ ይቀበሉታል፡፡ ምዕራባውያን እስልምናን የሚቀበሉበት ቀን ይመጣል፡፡ በእርግጥም እስልምና ላይ በውሸት የተሞሉ መፅሀፎችን እያነበቡ ምዕተ ዓመታቶች አልፈዋል፡፡ ስለ ሙሐመድ ብዙ መፅሀፎች ተፅፈዋል ነገር ግን በእንግሊዝ አማካኝነት እንዳይታተሙ እገዳ ላይ ናቸው፡፡

## የነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ባለቤቶች

ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ባለቤታቸው ኸዲጃ(ረ.ዐ) ከሞተች በኋላ 11 ሴቶችን አግብተዋል፡፡ ከአዒሻ በስተቀር ሁሉም በእድሜ ትልቅ የሆኑና አግብተው የሚያውቁ ነበሩ፡፡ አዒሻን ግን ያገቡት በድንግልና ነው፡፡ ከነሱ ውስጥ ስድስቱ የቁረይሽ ጎሣ አባል ሲሆኑ አምስቶቹ ግን ከሌላ ናቸው፡፡ የኢብራሂም እናት ደግሞ ግብፃዊት ነች፡፡ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡፡ “ግብፃዊያን ክርስቲያን ከማረካችሁ ተንከባከቧቸው፡፡ ለእነሱ ሀላፊነት እና ዝምድና አላቸው፡፡” (አብዱረዛቅ)

ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እነዚህን ሴቶች ያገቡበት ብዙ ምክንያቶች አሉ፡-

1ኛ. ሀይማኖታዊ ሕግጋትን ለማስተማር፡-

> ለምሳሌ ዘይነብ ቢንት ጀህሽን(ረ.ዐ) ያገቡበት ሁኔታ፡፡ በጃሂልያ ዘመን አረቦች አንድ ሰው እንደ ልጅ ያስጠጋውን ሰው ያገባትን ሴት አያገቡም ነበር፡፡ ምክንያቱም እንደ ልጅ ያስጠጉትን ሰው እንደ አብራካቸው ክፋይ ስለሚያስቡት ነው፡፡ ይህንን ተገቢ ያልሆነ ህግ ለማፍረስ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) የዘይድ ሚስት የነበረችውን ዘይነብን አገቧት፡፡ አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-
>
> فَلَمَّا قَضَىٰ زَيْدٌ مِّنْهَا وَطَرًا زَوَّجْنَاكَهَا لِكَيْ لَا يَكُونَ عَلَى الْمُؤْمِنِينَ حَرَجٌ فِي أَزْوَاجِ أَدْعِيَائِهِمْ إِذَا قَضَوْا مِنْهُنَّ وَطَرًا ۚ وَكَانَ أَمْرُ اللَّهِ مَفْعُولًا [٣٣:٣٧]
>
> *“ዘይድም ከእርሷ ጉዳይን በፈፀመ ግዜ በምዕመናኖች ላይ ልጅ ሊደርገው ባስጠጓቸው (ሰዎች) ሚስቶች ከእነርሱ ጉዳዩን በፈፀሙ ግዜ (በማግባት) ችግር እንዳይኖርባቸው እርሷን አጋባንህ፡፡ የአላህም ትዕዛዝ ተፈፃሚ ነው፡፡” (አል አህዛብ 37)*

2ኛ. ፖለቲካዊ ምክንያት፡-

የታላላቅ ጎሳ ሴቶችን በማግባት የእነዚህን ሰዎች ልብ መሣብ፡፡ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) የቁረይሽ ታላላቅ ጎሣዎች እና የአረብ ታላላቅ ጎሣዎችን ሴቶች አግብተዋል፡፡ ባልደረቦቻቸውንም ይህንን እንዲተገብሩ ያዙ ነበር፡፡ አብዱራህማን ኢብኑ አውፍን(ረ.ዐ) ወደ 'ደውመተ ጀንደል' በላኩት ግዜ እንዲህ ብለውታል፡- "እሺ ካሉህ የንጉሳቸውን ልጅ አግባ" (ጦበሪ)

Cl. Cahan እንዲህ ይላል፡-

"ምናልባት አሁን አሁን ባመጣነው አስተሳሰብ አንዳንድ የሕይወት ክፍሎቻቸው ላይ ቅሬታ ሊመጣብን ይችላል፡፡ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ኸዲጃ(ረ.ዐ) ከሞተች በኋላ 9 ሚስት በማግባት ዱንያዊ ፀጋን በመውደድ አስጠርጥሯቸዋል፡፡ ነገር ግን ያለው እውነታ አብዛኛዎችን ሴቶች ያገቧቸው ለፖለቲካዊ ምክንያት እንጂ ስሜታቸውን ለማርካት አልነበረም፡፡ አላማቸውም የተወሰኑ የተከበሩ ጎሳዎችን ዝምድና አግኝቶ ተቀባይነትን ማትረፍ ነበር፡፡"

3ኛ. ለማህበራዊ ጥቅም ሲባል

ይህ ሲባል ባሎቻቸው በአላህ መንገድ ላይ ሲታገሉ የሞቱባቸውን ሴቶች ማግባት ነው፡፡ እነዚህ ሴቶች ምንም እድሜያቸው ትላልቅ ቢሆንም ለነሱ በማዘን እና ለነሱም ለሞቱት ባሎቻቸውም ክብር ለመስጠት ሲባል አግብተዋቸዋል፡፡

የጣሊያኗ ፀሀፊ L. Veccia Vaglieri "ስለ እስልምና መከላከል" በሚለው መፅሀፏ ውስጥ እንዲህ ትላለች፡፡ የተቃራኒ ፆታ ስሜት በሚያይልበት የወጣትነት ዘመናቸው፣ እንዲሁም እንደ ህብረተሰብ የኖሩባቸው ሰዎች ብዙ ማግባትን እንደ ግዴታ የሚያዩ ሆኖ ሳለ በተጨማሪም ከመሬት ተነስቶ ፍቺ መፈፀም እንደቀልድ በሚታይበት ማህበረሰብ ውስጥ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) ግን ያገቡት አንዲትን ሴት ኸዲጃን ነበር፡፡ እሷም በእድሜ በብዙ ዓመት ትበልጣቸው ነበር፡፡ ነገር ግን ተፋቅረውና ተዋድደው ለ25 ዓመታት መኖር ችለዋል፡፡ እድሜያቸው 50 ከመሙላቱ በፊት እና ኸድጃ ሳትሞት በፊት ሁለተኛ ሚስት አላገቡም፡፡ ከዛ በኋላ ያገቧቸውን ሴቶች በሙሉ ከአኢሻ በቀር ስንመለከት ማህበረሰባዊ ወይም ፖለቲካዊ ጥቅምን ያዘለ ነበር፡፡ አንዳንድ ግዜ ያገቧቸውን ሴቶቸ ለማክበር እና ለማላቅ አስበው ሲሆን ሌላ ግዜ ደግሞ ከተወሰኑ ጎሣዎች ጋር የአማችነት ዝምድና በመፍጠር የጎሣው አባላት ዘንድ እስልምና እንዲስፋፋ ለማደረግ ነው፡፡ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) ያገቧቸው ሴቶች ድንግል፣ ወጣት እና ቆንጆ ያልነበሩ ሆኖ ሳለ እንዴት በቅንዝረኛነት ይጠረጠራሉ? ነብዩ ሰው እንጂ አምላክ አልነበሩም፡፡ ልጅ የመውለድ ፍላጎት ይኖራቸዋል፡፡ ምናልባትም ሚስት እንዲጨምሩ ያደረጋቸው አንደኛው ምክንያት ይህ ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም ከኸዲጃ አግኝተዋቸው የነበሩት ልጆች ሞተውባቸው ነበር፡፡ ብዙ የገቢ ምንጭ ሳይኖራቸው የብዙ ቤተሰባቸውን ወጪ ኃላፊነት ተሸክመዋል፡፡ ነገር ግን ይህ ከመሆኑም ጋር ፍትሀዊ በሆነ መልኩ ማንንም ከማንም ሳያበላልጡ ሚስቶቻቸውን በእኩልነት አስተዳድረዋል፡፡ በእርግጥም እሳቸው ያደረጉት ነገር ከሳቸው በፊት የነበሩት ነብያቶች እንደሙሣ እና ሌሎች ነብያቶች ያደረጉትን ነገር ነው፡፡ ምንም እንኳን እነዚህ ነብያቶች በዚህ ተግባራቸው ባይብጠለጠሉም፡፡ ከሌላ ነብያቶች በተለየ መልኩ ነብዩ ሙሐመድን ብቻ በዚህ ተግባር የሚብጠለጠሉት ስለሳቸው ህይወት ጥቃቅን ነገር እንኳ ሳይቀር ስለምናውቅ እና ሌሎችን ነብያቶች ግን በዚህ መልኩ የህይወት ታሪካቸውን ስለማናውቅ ነውን?

እንግሊዛዊው ፀሀፊ ቶማስ ካርሊል 'The Heroes' በሚለው መጽሀፉ ውስጥ እንዲህ ይላል፡- ምንም ያህል ውሸት እና ቅጥፈት ቢወራበትም ሙሐመድ ስሜቱን የሚከተል ሰው አልነበረም፡፡ ሙሐመድ ስሜታዊ ሰው ነው፤ ስሜቱን ማርካት

እንጂ ሌላ አላማ የለውም ብለን የደመደምን እለት ትልቁን ስህተት ተሳስተናል፡፡ እርሱና ስሜተኝነት ምነኛ በጣም የተራራቁ ነገራቶች ናቸው?

## ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) ነብይ ስለመሆናቸው የተወሰኑ ፅሁፋዊ ማስረጃዎች

### ከቅዱስ ቁርዓን

አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

مَّا كَانَ مُحَمَّدٌ أَبَا أَحَدٍ مِّن رِّجَالِكُمْ وَلَٰكِن رَّسُولَ اللَّهِ وَخَاتَمَ النَّبِيِّينَ ۗ وَكَانَ اللَّهُ بِكُلِّ شَيْءٍ عَلِيمًا [٣٣:٤٠]

*"ሙሐመድ ከወንዶቻችሁ የአንድም ሰው አባት አይደለም፡፡ ግን የአላህ መልዕክተኛና የነቢዮች መደምደሚያ ነው። አላህም በነገሩ ሁሉ ዐዋቂ ነው፡፡" (አህዛብ 40)*

ዒሳም(ዐ.ሰ) ነብዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) ከሱ በኋላ እንደሚመጡ አበስሯል፡፡ አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

وَإِذْ قَالَ عِيسَى ابْنُ مَرْيَمَ يَا بَنِي إِسْرَائِيلَ إِنِّي رَسُولُ اللَّهِ إِلَيْكُم مُّصَدِّقًا لِّمَا بَيْنَ يَدَيَّ مِنَ التَّوْرَاةِ وَمُبَشِّرًا بِرَسُولٍ يَأْتِي مِن بَعْدِي اسْمُهُ أَحْمَدُ ۖ فَلَمَّا جَاءَهُم بِالْبَيِّنَاتِ قَالُوا هَٰذَا سِحْرٌ مُّبِينٌ [٦١:٦]

*"የመርየም ልጅ ዒሳም፡- 'የእስራኤል ልጆች ሆይ! እኔ ከተውራት በፊቴ ያለውን የማረጋግጥና ከእኔ በኋላ በሚመጣው መልዕክተኛ ስሙ አህመድ በኾነው የማበስር ስሖን ወደ እናንተ(የተላክሁ) የአላህ መልዕክተኛ ነኝ..." (አስሶፍ 6)*

## ከሀዲስ

ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- የእኔና ከእኔ በፊት ያሉ ነብያቶች ምሣሌ አንድ ቤትን እንደሰራ ሰው ነው፡፡ ቤቱን ቢያስውበውም አንድ ብሎኬት ግን ይቀረዋል፡፡ ሰዎች ይጎበኙታል፣ ይገረሙበታልም፡፡ "ይህንን ብሎኬት ብታሟላ ምንኛ ባማረ!" ይሉታል፡፡ "ይህች የቀረችው ብሎኬት እኔ ነኝ፡፡ እኔ የነብያቶች መደምደሚያ ነኝ፡፡" (ሶሂህ ቡኻሪ)

### ካለፉት ሰማያዊ መፅሀፍቶች

አጣዕ ኢብኑ የሳር(ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፡- አብደላህ ኢብን ዐምር ኢብነል አስን(ረ.ዐ) አገኘሁት እና "በተውራት ውስጥ ስለተገለፀው የነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ባህሪ ንገረኝ" አልኩት፡፡ እሱም "አዎን! በእርግጥም ቁርአን ውስጥ በተጠቀሱት የተወሰኑ ባህርያቶች ተውራት ላይም ተጠቅሰዋል፡፡ አንተ ነብይ ሆይ እኛ መስካሪ፣ አብሳሪ፣ አስጠንቃቂ እና ለሀይማኖት ጠባቂ አድርገን ልከንሀል፡፡ አንተ ባሪያዬ እና መልዕክተኛዬ ነህ፡፡ "ሙተወኪል" ብዬ ሰይሜሀለው፡፡ ቁጡ እና ልበደረቅ አይደለም። በየገቢያው የሚጯጯህ አይደለም፡፡ መጥፎን ነገር በመጥፎ ነገር የሚመልስ ሳይሆን ይቅር ባይ እና መሀሪ ነው፡፡ ትክክለኛው ሀይማኖት ምድር ላይ እስከሚመለስ ድረስ አይሞትም፡፡ የሚላከውም ሰዎች 'ላሊላሀኢለሏህ' እንዲሉ፣ የታወረ አይን፣ የተደናቀረ ጆሮን እና የደረቀ ልብን ሊከፍት ነው፡፡"

እጣዕ ኢብኑ የሳር "ከዛ በኋላ የአይሁድ ሊቅ የነበረውን ካዕብን አግኝቼ ስጠይቀው "የታወሩ አይኖችን፣ የደረቁ ልቦችን እና የተደናቆሩ ጆሮዎችን ከማለት ውጪ የተለየ ነገር አልነገረኝም" ብሏል፡፡ (ሱነን በይሀቂ)

ፕሮፌሰር አብዱል አህድ ዳውድ እንዲህ ይላል፡-

"...ነገር ግን እኔ ሙግቴን የትኛውንም ዓይነተ የቋንቋ ክርክር ሊያስተናግዱ በማይችሉ የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍሎች ላይ ለማድረግ ሞክሬያለው፡፡ ወደ ላቲን፣ ግሪክ ወይም አራማይክ ቃላት አልሄድም፡፡ ምክንያቱም ጥቅም ስለማይኖረው ነው፡፡

Biritish & foreign bible society አሳትሞ ካስወጣው መፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ የሚከተለውን ጥቅስ እንድታዩት እፈልጋለው፡፡

በኦሪት ዘዳግም ምዕራፍ 18 የተፃፈውን ጥቅስ እናንብብ "ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነብይ አስነሳላቸዋለው፡፡ ቃሌንም በአፉ አደርጋለው፡፡"

እነዚህ ንግግሮች ሙሐመድን የማይመለከቱ ከሆነ ገና አልተፈፀሙም ወይም አልተከሰተም ማለት ነው፡፡ እየሱስ በእራሱ አንደበት እሱ እንዳልሆነ ተናግሯል፡፡ ሀዋርያቱም ጭምር በተመሳሳይ አቋም ላይ ነበሩ፡፡ የእየሱስ ነብይነተ የተሟላ እንዲሆን እንኳን ሁለተኛ ጊዜ መምጣቱን እየተጠባበቁ ነበር፡፡ እስካሁን ድረስ የእየሱስ የመጀመሪያ መከሰት "ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነብይ" ያለውን እንደማያመለክት የማያከራክር ነጥብ ነው፡፡ ሁለተኛውም መከሰት ቢሆን የዚህ ጥቅስን መልዕከት ይይዛል ማለት ይከብዳል፡፡ ራሱ ቤተክርስቲያኑ እንደሚያስተምረው እየሱስ እንደገና ሲመጣ ዳኛ  ሆኖ እንጂ መመሪያን ይዞ አይደም፡፡ ነገር ግን ቃል የተገባውና ሲጠበቅ የነበረው ብርሃናማውን መመሪያ በቀኝ እጁ ይዞ የሚመጣ ነው፡፡

ከሙሣ ጋር የተዛመደው ይህ ቃል የተገባው ነብይ ሌላው የማንነቱ ማረጋገጫ፡- "ከፋራን የሚወጣው የፈጣሪ ብርሃን" የሚለው ነው፡፡ 'ፋራን' ማለት የመካ ተራራዎች ማለት ነው፡፡ በኦሪት ዘዳግም(33:2) እንደሚከተለው ተፅፏል፡- "እግዚአብሔር ከሲና መጣ፣ በሰይሪም ተገለጠ፡፡ ከፋራን ተራራ አበራላቸው፡፡ ከአስር ሺ ቅዱሳን ጋር መጣ፡፡ በስተቀኙም የእሳት ሕግ ነበረላቸው፡፡"

በዚህ ጥቅስ ፈጣሪ በፀሀይ ብርሃን ተመስሏል፡፡ ከሲናይ በኩል መጥቷል፡፡ ከሰይሪም ተገልጧል፡፡ ነገር ግን በተሟላ መልኩ ያንፀባረቀው ከፋራን ተራራ ነው፡፡ እሱም 10,000 ቅዱሳንን እና ለነሱ ደግሞ በቀኝ እጁ መመሪያ መያዝ አለበት፡፡ማንኛውም እስራኤላዊ እየሱስን ጨምሮ ከ'ፋራን' ጋር የሚያገናኛቸው ነገር የለም፡፡ ሀጀር እና ልጇ ኢስማኤል ናቸው ወደ ቤርሳቤህ ምድረ በዳ ተንቀሳቅሰው በ'ፋራን' ኑሮዋቸውን የመሠረቱት፡፡ (ኦሪት ዘፍጥረት 21:21) "እናቱም ከምድረ ግብፅ ሚስት ወሰደችለት።" የመጀመሪያው የኢስማኤል ልጁ አድናንም እስከአሁን ድረስ በፋራን ምድረ በዳ ለሚኖሩ አረቦች ሁሉ የዘር ግንድ ሆነ፡፡ ታዲያ ሙሐመድ እንደሚታወቀው በአድናን በኩል የኢስማኤል ልጅ መሆናቸው፣ ከዛ በኋላ በፋራን ተራራዎች ላይ ነብይ መደረጋቸው፤ 10 ሺ ምዕመናንን ይዘው ወደ መካ መመለሳቸው እና ለሕዝቦቻቸው ብርሃናማ መመሪያ ማምጣታቸው ጥቅሱ ላይ የተተነበየው ነብይ መሆናቸውን አያመላክትምን?

ትንቢተ ዕንባቆም ላይ የተጠቀሰውን ነብይ ትኩረት ሰጥቶ ማየት አስፈላጊ ነው፡፡ እሱም እንዲህ ይለል፡-

"ቅዱሱም ከፋራን ተራራ ይመጣል፡፡ ክብሩ ሰማያትን ከድኗል፤ ምስጋናውም ምድርን ሞልቷል፡፡"

እዚህ ጋር 'ምስጋና' የሚለው ቃል በጣም ወሳኝ ነው፡፡ ምክንያቱም ሙሐመድ ማለት ምስጉኑ ማለት ስለሆነ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የፋራን ነዋሪዎች አረቦች ናቸው፡፡ በተጨማሪም ራዕይ(ወሕይ) እንደሚወርድላቸው ቃል ተገብቶላቸው ነበር፡፡

"ምድረበዳውና ከተማዎቹ የቄዳርም(አድናን) ሰዎች የሚቀመጡባቸው መንደሮች ድምጻቸውን ያንሱ፤ በሴላ የሚኖሩ እልል ይበሉ፥ በተራራዎችም ራስ ላይ ሁነው ይጨኹ፡፡ ለእግዚአብሔር ክብርን ይስጡ። ምስጋናውንም በደሴቶች ይናገሩ፡፡ እግዚአብሔር እንደ ኃያል ይወጣል እንደ ሰልፈኛም ቅንአት ያስነሳል፣ ይጮኻል ድምፁንም ያሰማል፡፡ በጠላቶቹም ላይ ይበረታል፡፡ (ትንቢተ ኢሳያስ 42:11-12)

እዚህ ጋር ትኩረት መስጠት ያለብን ሁለት ሌላ ነብያቶች ከቄዳር ጋር በማያያዝ ተተንብየዋል፡፡ አንደኛው በትንቢተ ኢሳያስ 60(1-7) የተጠቀሰው ነው፡፡

“ብርሃንሽ መጥቷልና፤ የእግዚአብሔርም ክብር ወጥቶልሻልና፤ ተነሺ አብሪ፡፡ ...የግመሎች ብዛት፣ የምድያምና የጌፌር ግመሎች፣ ይሸፍኑሻል፤ ኹሉ ከሳባ ይመጣሉ፤ ...የቄዳር መንጋዎች ኹሉ ወደ አንቺ ይሰበሰባሉ የነባዮትም አውራ በጎች ያገለግሉሻል፤ እኔን ደስ ሊያሰኙ በመሰዊያዬ ላይ ይወጣሉ የክብሬንም ቤት አከብራለሁ፡፡”

ሌላኛው ትንበያ እዛው ትንቢተ ኢሳያስ ውስጥ ነው፡፡

ትንቢተ ኢሳያስ 21:13-17፦ ስለ ዐረብ የተነገረ ሸክም የድዳናውያን ነጋዴዎች ሆይ፥ በዐረብ ዱር ውስጥ ታድራላችሁ፡፡ በቴማን የምትኖሩ ሆይ፥ ወደ ተጠሙት ሰዎች ውሃ አምጡ እንጀራ ይዛችሁ የሸሹትን ሰዎች ተቀበሏቸው፡፡ ከሰይፍ ከተመዘዘው ሰይፍ፥ ከተለጠጠውም ቀስት ከፀኑም ሰልፍ ሸሽተዋልና፡፡ ጌታ እንዲህ ብሎኛልና፦ እንደ ምንደኛ ዓመት ባንድ ዓመት ውስጥ የቄዳር ክብር ሁሉ ይጠፋል፤ ከቀስተኛዎች ቁጥረ የቀሩት የቄዳር ልጆች ኃያላን ያንሳሉ፤

እነዚህን የኢሳያስ ትንቢቶች ስለ “ከፋራን የሚመጣ የእግዚአብሔር ብርሃን” በሚያወራው የኦሪት ዘዳግም ምዕራፍ ላይ አንብብ፡፡

እስማኤል በፋራን ምድረበዳ ተቀምጦ ከነበር ከዛም የአረቦችን አባት ቄዳረን(ኢድናንን) ወልዶ ከነበር፤ የቄዳርም ልጆች ከፈጣሪ ራዕይ እንደሚመጣላቸው ከተፃፈ፤ የቄዳርም ሕዝቦች መቀበላቸውን ለማሳየትና ታላቁን ቤት ለማክበር እርድ ማረድ ካለባቸው፡፡ ጨለማም ምድርን ለተወሰኑ ምዕተ ዓመታት መሸፈን ካለበት፡፡ ከዛም ይህች ምድር ከአምላኳ ብርሃንን የምትቀበል ከሆነ፤ እና የቄዳር ክብር እነዚያን ሁሉ ጦረኞች እና እነዚያ ሀያል የቄዳር ልጆች ከተመዘዙ ሰይፎች እና ከተለጠጡ ቀስቶች መሸሽ በኋላ በአንድ ዓመት ውስጥ መጥፋት ካለባቸው፤ ከፋራን የሚመጣው ቅዱስ፤ ከሙሐመድ ውጪ ሊሆን የሚችል ሰው አለን?

በቄዳር በኩል የኢስማኤል ዘርና በፋራን ምድረ በዳ የኖረ ብቸኛው ነብይ ሙሐመድ ነው፡፡ ምድርን ጨለማ በሸፈናት ወቅት አረቦች የጌታን ራዕይ የተቀበሉበት ብቸኛው ነብይ ሙሐመድ ነው፡፡ በእሱም አማካኝነተ የጌታ ብርሃን ከፋራን ተራራ በኩል አንፀባረቀ፡፡ መካም ብቸኛዋ የጌታ ስም የሚላቅበት እና የቄዳር ሕዝቦች በመታዘዝ መስዋት ለማቅረብ የሚመጡባት ሀገር ናት፡፡ ሙሐመድም ወገኖቹ ስቃይ እና መከራ ስላበዙበት ከመካ ለመሰደድ ተገዷል፡፡ በሽሽት ላይ ሳለ ተጠምቶ ነበር፡፡ ከተመዘዙ ሰይፎች እና ከተለጠጡ ቀስቶችም አምልጧል፡፡

ከስደቱም አንድ ዓመት በኋላ ከቄዳር ዘሮች ጋር በበድር ጦርነት ተገናኝተዋል፡፡ ይህም በቁረይሾች እና በነብዩ መሐል የተካሄደው የመጀመሪያው ጦርነት ነው፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ የቄዳር ልጆች እና ቀስተኞቹ እየቀነሱ ሄዱ፡፡ በመጨረሻም የቄዳር ሀያልነት ሁሉ ጠፋ፡፡ የተቀደሰው ነብይ(ሙሐመድ) እነዚህን ሁሉ ትንቢቶች አሟልቷል ብለን መቀበል ካልቻልን ትንቢቶቹ ገና ፍፃሜ አላገኙም ማለት ነው፡፡ በትንቢተ ኢሳያስ 60 የጌታ ስም የሚከበርበት የክብሬን ቤት ተብሎ የተጠቀሰው መካ የሚገኘው የተከበረው የአላህ ቤት እንጂ የክርስትና ተንታኞች እንደሚሉት የእየሱስ ቤተክርስቲያን አይደለም፡፡ ምክንያቱም በ7ኛው አንቀፅ እንደተጠቀሰው የቄዳር መንጋዎች ወደ እየሱስ ቤተክርስቲያን ሄደው ስለማያውቁ ነው፡፡ በእርግጥም የቄዳር ነዋሪዎች በዓለም ላይ በቤተክርስቲያን አስተምህሮ ተፅዕኖ ውስጠ ያልወደቁ ብቸኛው ሕዝቦች ናቸው፡፡ በተጨማሪም በኦሪት ዘዳግም 33 ላይ የተጠቀሱት 10,000 ቅዱሳን በጣም ወሳኝ ናቸው፡፡ “ከፋራን ተራራ አበራላቸው፤ ከአዕላፋትም ቅዱሳኑ መጣ...” የፋራንን ታሪክ ስታነብ ከዚህ ትንበያ ጋር የሚገጥመው ብቸኛው ክስተት ሙሐመድ መካን በድል ከፍቶ በተቆጣጠረበተ ሰዓት ነው፡፡ ከመዲና 10,000 ተከታዮቹን ይዞ ተመልሶ የተከበረው ቤት ካዕባ ገባ፡፡ ሌሎችን መመሪያዎች ወደ አመድነት የለወጠ መመሪያ ለአለም አበረከተ፡፡”

በእየሱስ አፍም የተነገረው ‘አልሀዲ’ (እውነተኛ መንፈስ) ከሙሐመድ ውጪ ሌላ አካል ሊሆን አይችልም፡፡ ስነመለኮት ቤተክርስቲያን እንደተረጎሙት መንፈስ ቅዱስ ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም እየሱስ እራሱ እንደዚህ ይላልና ነው፦ “እኔ

ርቄ መሄዴ ለናንተ የተሻለ ነው፡፡ ምክንያቱም እኔ ርቄ ካልሄድኩኝ 'አልሀዲ' አይመጣላችሁም፡፡ እኔ የሄድኩኝ ግዜ ግን ወደናንተ እልከዋለሁ፡፡"

እነዚህ ንግግሮች በግልፅ የሚያስረዱት አፅናኙ የሚመጣው ኢየሱስ ከሄደ በኋላ መሆኑን ነው እየሱስም ይህን በተናገረ ወቅት ይህ ሰው አብሮት አለመኖሩን ያሳያል፡፡ ታዲያ የመንፈስ ቅዱስ መምጣት በኢየሱስ መሄድ ላይ የተመረኮዘ ከሆነ እየሱስ እና መንፈስ ቅዱስ የተለያዩና የማይገናኙ አካሎች ናቸው ብለን ልናስብ ነው? ከዚህ በተለየ መልኩ ደግሞ የእየሱስ ገለፃ የሚያመላክተው መንፈስን ሳይሆን የሰውን ልጅ መሆኑን ነው፡፡

"ከራሱ አይናገርም ነገር ግን የሰማውን ነገር ለሰዎች ያስተላልፋል" ታዲያ መንፈስ ቅዱስ እና አላህ የተለያዩ አካል ናቸው? መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ከራሱም ከአላህም የሰማውን ነገር ይናገራል ብለን ልንደመድም ነውን?

የእየሱስ ንግግር በግልጽ የሚያመለክተው ከአላህ ስለሚላክ መልዕክተኛ ሰው ነው፡፡ እሱም እውነተኛው መንፈስ ብሎ ጠርቶታል፡፡ በተመሣሣይ መልኩ ቁርአንም ስለነብዩ ሙሐመድ እንዲህ ይላል፡-

بَلْ جَاءَ بِالْحَقِّ وَصَدَّقَ الْمُرْسَلِينَ [٣٧:٣٧]

*"አይደለም እውነቱን(ሃይማኖት) አመጣ፡፡ መልዕክተኞቹንም እውነተኝነታቸውን አረጋገጠ" (ሷፋት 37)*

**<u>ከኢንጂል (ወንጌል)</u>**

እየሱስ(ዐ.ሰ) በወንጌል እንዲህ ይላል "… በዚያም ወቅት አምላክ እኔን ከምድር ላይ ይወስደኝና እኔን አሳልፎ የሸጠውን ከሀዲ መልኩን በመቀየር እኔን እንዲመስል ያደርገዋል፤ ሰዎችም እኔ የተገደልኩ ይመስላቸዋል፡፡ እርሱ ይህን የውርደት ሞት ከሞተ በኋላ ከብሬን ተነፍጌ ለረዥም ዘመን በአለም እኖራለሁ፡፡ ነገር ግን ቅዱሱ የአምላክ መልክተኛ ሙሐመድ በሚመጣ ጊዜ ይሄ ውርደት ከእኔ ይወገዳል (የባርናባስ ወንጌል 112:13-16)

በተመሳሳይ መልኩ በባርናባስ ወንጌል ምዕ 39 እንደተፃፈው ማለት ነው፡፡

> "አዳምም በሁለት እርግሮቹ ሲቆም በሕዋ ላይ የተንጠለጠለች ፅሁፍ ያያል፡፡ ፅሁፉም "ከአላህ ውጪ የሚመለክ አምላክ የለም፡፡ ሙሐመድም መልዕክተኛው ነው።" በአባታዊ ርህራሄ የመጀመሪያው ሰው እነዚህን ንግግሮች ሳመ። ከዛም አይኑን አበሰና እንዲህ አለ "እሱ ወደ አለም የሚመጣበት ቀን የተባረከ ነው፡፡"

## <u>ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እውነተኛ መልዕክተኛ ስለመሆናቸው ግልፅ ማስረጃዎች</u>

1. ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) መፃፍና ማንበብ አይችሉም፡፡ ከሕዝቦቻቸው መካከል እንደሳቸው መፃፍና ማንበብ የማይችሉ ጥቂት ነበሩ፡፡ ይህ የሆነበትም ምክንያት ቁርዓን ሙሐመድ በእጁ እየፃፈው ነው የሚል መከራከሪያ ነጥብ እንዳያነሱ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

وَمَا كُنتَ تَتْلُو مِن قَبْلِهِ مِن كِتَابٍ وَلَا تَخُطُّهُ بِيَمِينِكَ ۖ إِذًا لَّارْتَابَ الْمُبْطِلُونَ [٢٩:٤٨]

*"ከርሱ በፊትም መፅሀፍን የማታነብ በቀኝህም የምትፅፈው አልነበርክም፡፡ ያንግዜ አጥፊዎች በእርግጥ በተጠራጠሩ ነበር፡፡" (አልአንከቡት 48)*

አረቦች ተመሳሳዩን ማምጣት ያቃታቸውን መፅሀፍ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ይዘው መጡ፡፡ እንደበተ ርቱዕነቱ እና ውብ መሆኑ ማረካቸው፡፡ በዚህም አማካኝነት የረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ታላቅ ተዓምር ቁርአን ሆነ፡፡ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ፡-

“ሁሉም ነብይ፥ ነብይ ሲደረግ የተላከበት ሰዎች ዘንድ የሚያሳምን ተዓምር ይዞ ነው፡፡ እኔ ደግሞ ይዤ የመጣሁት ከአላህ ዘንድ የሚመጣልኝ ራዕይ (ወሕይ) ነው፡፡ በየውመል ቂያማ ከሁሉም የኔ ተከታዮች የበዙ እንዲሆኑ ምኞቴ ነው፡፡”

የነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ሕዝቦች በጣም በቋንቋ ክህሎት የመጠቁ ስለነበሩ ይችሉ ከሆነ እንደ ቁርአን ያለ ንግግር እንዲያመጡ ተጠየቁ፡፡ ይህ ሲያቅታቸውም አንድን የቁርዓን አንቀጽ ተመሳሳይ ማምጣት ይችሉ እንደሆነ ተጠየቁ፡፡

وَإِن كُنتُمْ فِي رَيْبٍ مِّمَّا نَزَّلْنَا عَلَىٰ عَبْدِنَا فَأْتُوا بِسُورَةٍ مِّن مِّثْلِهِ وَادْعُوا شُهَدَاءَكُم مِّن دُونِ اللَّهِ إِن كُنتُمْ صَادِقِينَ

*“በባሪያችንም ላይ ካወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ብትሆኑ ከብጤው አንዷትን ምዕራፍ አምጡ፡፡ እውነተኞችም እንደሆናችሁ ከአላህ ሌላ መስካሪዎቻችሁን ጥሩ፡፡” (አልበቀራ 23)*

ኧረ እንደውም የሰው ልጆች በሙሉ ተሰብስበው ተመሳሳዩን እንዲያመጡ ጥያቄ ቀርቧል፡-

قُل لَّئِنِ اجْتَمَعَتِ الْإِنسُ وَالْجِنُّ عَلَىٰ أَن يَأْتُوا بِمِثْلِ هَٰذَا الْقُرْآنِ لَا يَأْتُونَ بِمِثْلِهِ وَلَوْ كَانَ بَعْضُهُمْ لِبَعْضٍ ظَهِيرًا

*“ሰዎችም ጋኔኖችም የዚህ ቁርዓን ብጤ በማምጣት ላይ ቢሰበሰቡ ከፊላቸው ለከፊሉ ረዳት ቢሆንም እንኳ ብጤውን አያመጡም” በላቸው፡፡ (17:88)*

2. ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ምንም እንኳን የከፋ መከራና ከባድ መሰናክሎች የግድያ ሙከራን ጨምሮ ከሕዝቦቻቸው ቢገጥማቸውም፡ በዳዕዋቸው ላይ ፀንተው መዘውተራቸው፡፡ የአላህን ሀይማኖት በማስፋፋት ላይ የሚገጥማቸውን መከራ፣ እንግልት እና ስቃይ ሁሉ ታግሶ በማሳለፈ ስራቸውን ቀጥለዋል፡፡ አስመሳይ እና አታላይ ቢሆኑ ኖሮ (አላህ ከዚህ አጥርቷቸዋል እንጂ) ጥሪያቸው ቀጣይነት አይኖረውም ነበር፡፡ ሕዝቦቻቸው ሲያምጹባቸው፣ የመሪዎቹም ውሳኔ ጠንከር ያለ መሆኑንና ለሕይወታቸው አስጊ መሆኑን የተገነዘቡ ግዜ ያቆሙት ነበር፡፡

   Dr. M.H. Durrani እንዲህ ይላሉ፡፡

   “ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) ንቅናቄውን እስከመጨረሻ ድል ድረስ የቀጠለበት ጠንካራ እምነት እና ሀይለኛ ቁርጠኝነት እውነተኛ ለመሆኑ ግልፅ ማስረጃ ነው፡፡ በመንፈሱ ውስጥ ትንሽዬ እንኳን ጥርጣሬ እና ሕውከት ቢኖርበት ኖሮ ለ20 አመታት ሙሉ ቀጣይነት የነበረውን አውሎንፋስ መቋቋም አይችልም ነበር፡፡ ግብ ላይ ቆራጥ ከመሆን፣ ስራ ላይ ጽኑ ከመሆንና ራሰን አሳልፎ ከመስጠት የበለጠ ምን ግልጽ ማስረጃ ይኖራል፡፡ እነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) ትክክለኛ ነብይ መሆኑን መደምደም ያስችሉናል፡፡ የኛ ነብይ ሙሐመድ እንግዲህ ይህ ነው፤ ብርቅዬ ባህሪው በራሱ ተዓምር ነው፤ ለበጎ ምግባር እና ለመልካም ስብዕና ምሳሌ ነው፤ ለታማኝነት እና ለእውነትኝነት ሞዴል ነው፡፡ ሕይወቱ፣ አስተሳሰቡ፣ እውነተኝነቱ፣ ጽኑነቱ፣ አላህን ፍራቻው፣ ቸርነቱ፣ እምነቱ፣ እያንዳንዳቸው ነብይ ስለመሆኑ ማስረጃ ናቸው፡፡ ማንኛውም ሰው ጭፍን ሳይሆን ሕይወቱን እና ተልዕኮውን ያጠና ሰው በእርግጠንነት ነብይ መሆኑን ይመሰክራል፤ ይዞ የመጣውም ቁርአን እውነተኛ ከአላህ መሆኑን ያምናል፡፡ ሁሉም እውነትን የሚፈልግ አስተዋይ ፍትህዊ ሰው እዚህ ውሳኔ ልዩ መድረሱ የማይቀር ነገር ነው፡፡

3. የሰው ልጅ በተፈጥሮ የዚህችን አለም ፀጋ ገንዘብም፣ መጠጥም ምግብም ይሁን ሴት እንደሚወድ የታወቀ ነገር ነው፡፡ አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

زُيِّنَ لِلنَّاسِ حُبُّ الشَّهَوَاتِ مِنَ النِّسَاءِ وَالْبَنِينَ وَالْقَنَاطِيرِ الْمُقَنطَرَةِ مِنَ الذَّهَبِ وَالْفِضَّةِ وَالْخَيْلِ الْمُسَوَّمَةِ وَالْأَنْعَامِ وَالْحَرْثِ ۗ ذَٰلِكَ مَتَاعُ الْحَيَاةِ الدُّنْيَا ۖ وَاللَّهُ عِندَهُ حُسْنُ الْمَآبِ [٣:١٤]

*ከሴቶች፣ ከወንዶች ልጆችም፣ ከወርቅና ከብርም፣ ከተከማቹ ገንዘቦችም፣ ከተሰማሩ ፈረሶችም፣ ከግመል ከከብትና ከፍየልም፣ ከአዝመራም የሆኑ ፍላጎቶችን መውደድ ለሰዎች ተሸለመ፡፡ ይህ ሁሉ የቅርቢቱ ሕይወት መጠቀሚያ ነው፡፡ አላህም እርሱ ዘንድ መልካም መመለሻ(ገነት) አለ፡፡" (አልኢምራን 14)*

የሰው ልጅ እነዚህን መጠቀሚያዎች ለማግኘት በተለያዩ መዳረሻ መንገዶች ይለፋል፡፡ ነገር ግን ሰዎች በሚጠቀሙት መዳረሻ መንገድ ይለያያሉ፡፡ በሕጋዊ መንገድ ለማግኘት የሚጥሩ እንዳሉ ሁሉ በሕገወጥ እና ባልተፈቀደ መንገድ ለማግኘት የሚሯሯጡ አሉ፡፡ ይህንን ካወቅን ዘንድ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ጥሪያቸውን እንደጀመሩ ሕዝቦቻቸው ጥሪውን እንዲያቆሙ በዱንያዊ ፀጋ ድርድር አቅርበውላቸዋል፡፡ የሚፈልጉትን ሁሉ እንደሚሰጡት ቃል ገብተው ነበር፡ የቁረይሽ መሪ መሆን ከፈለገ በላያቸው ላይ እንደሚሾሙት፣ ሚስት ከሆነ ምኞቱ ውብ የተባለችውን ሴት እንደሚድሩለት፣ ገንዘብ ከሆነ ፍላጎቱ እንደሚሰጡት ነገር ግን ይህንን አዲስ ሃይማኖት እንዲተውና ሰበካም እንዲያቆም ድርድር አቅርበዋል፡፡

እሳቸውም በማያወላውል ልብ እንዲህ ሲሉ መለሱ፡-

"በአላህ ይሁንብኝ ይህንን ጉዳይ እንድተው ፀሀይን በቀኝ እጄ ጨረቃን ደግሞ በግራ እጄ ቢያስቀምጡ አላህ ይፋ እስኪያወጣው አልያም እስከሞት ድረስ የምተወው አይደለሁም!!!"

አታላይ እና አስመሳይ ቢሆኑ ኖሮ (አላህ ከዚህ አፅንቷቸዋል እንጂ) እድሉን ተጠቅመው ድርድሩን ይቀበሉ ነበር፡፡ ምክንያቱም በድርድሩ ላይ የቀረበላቸው ነገር በዚህች አለም ላይ ሁሉም ሰው የሚመኘው ነገር ስለሆነ ማለት ነው፡፡

Dr. M.H. Durran: እንዲህ ይላሉ፡-

"ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) በመካ ለ13 ዓመተ በተከታታይ መከራን ተሸክመዋል፡፡ በተመሣሣይ መልኩ በመዲና ሳሉ ለ8 ዓመት ተቸግረዋል፡፡ ይህን ሁሉ ግዜ መከራ ሲያስተናግዱ የፀጉርን ልክ ያህል እንኳ ከአቋማቸው ንቅንቅ አላሉም፡፡ አላማቸው ላይ ፅኑ እና ጠንካራ ነበሩ፡፡ ሕዝቦቹ ይህንን ሀይማኖት ከተወ እና መጣራቱን ካቆመ የሀገሪቱ ንጉስ እንደሚያደርጉት ቃል ገቡለት፡፡ ይህን ሁሉ ፀጋ እምቢ ብሎ በሀይማኖቱ ላይ በመፅናቱ የሚያገኘውን እንግልት መረጠ። ለምን? ገንዘብን፣ ክብርን፣ ንግስናን፣ እረፍትን እና መዝናናትን ለማግኘት ለምን አልተንቀሳቀሰም? የዚህን ጥያቄ መልስ የፈለገ ሰው በጥልቀት ማስተዋል ይጠበቅበታል፡፡

4. በአንድ ንጉስ ግዛት ውስጥ ያሉ ሰዎችም ይሁኑ ንብረቶች በንጉሱ ትዕዛዝ ስር መሆናቸው የታወቀ ነገር ነው፡፡ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) ግን ይህች አለም ጠፊ እና ግዜያዊ መሆኗን ጠንቅቆ ያውቃል፡፡ ኢብራሂም ቢን አልቀማ(ረ.ዐ) እንዳስተላለፈው አብደሏህ እንዲህ ብሏል፡- ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) በሰሌን ላይ ተኝተው ሲነሱ ቆዳቸው ላይ ምልክት አወጣ፡፡ እኔም አንቱ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ እናቴም አባቴም መስዋት ይሁንልህ! ፍቀድልን እና ፍራሽ ነገር እናነጥፍልህ" አልኩኝ፡፡ ረሱልም(ሰ.ዐ.ወ) "የእኔና የዱንያ ህይወት ምሳሌ በአንድ ዛፍ ስር እንደተጠለለ መንገደኛ ነው፡፡ ከዛም በኋላ ጥሏት ጉዞውን ይቀጥላል" አሉኝ።(ኢብኑ ማጃህ)

ኑዕማን ኢብኑ በሺር(ረ.ዐ) እንዲህ ይላል፡- በእርግጥም ነብያችሁን ረሀቡን የሚያስታግስበት ዝቅተኛ ታምር አጥቶ ተመልክቸዋለሁ፡፡" (ሶሂህ ሙስሊም)

አቡሁረይራ(ረ.ዐ) እንዳስተላለፈው፡- የሙሐመድ ቤተሰቦች ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) እስኪሞቱ ድረስ ለ3 ተከታታይ ቀን ጠግበው አያውቁም፡፡(ሶሂህ ቡኻሪ)

ምንም እንኳን የአረብ ምድረ ሰላጤ በቁጥጥሩ ስር የነበረ ቢሆንም፤ ሙስሊሞች ላገኙት በጎ ነገር ሁሉ ምክንያት እሱ ቢሆንም አንዳንድ ግዜ የሚበቃውን ምግብ እንኳ አያገኝም ነበር፡፡ ባለቤታቸው አዒሻ(ረ.ዐ) እንዲህ ትላለች፡- ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) የጦር ልብሳቸውን አስይዘው ከአይሁድ ምግብ ገዝተዋል፡፡(ቡኻሪ)

ይህ ማለት የሚፈልገውን ነገር ማግኘት አልቻለም ነበር ማለት አይደለም፡፡ በእርግጥም ገንዘብ እና ፀጋዎች በሙሉ መስጂድ ውስጥ በእጁ ይገቡ ነበር፡፡ ነገር ግን ለምስኪኖች እና ለድሆች ሳያከፋፍል ከቆመበት አይንቀሳቀስም፡፡ እንዲሁም ከባልደረቦቹም መካከል ሀብታሞች ነበሩ፡፡ እሱን ለማገልገል ይሽቀዳደሙ ነበር፡፡ ያላቸውን ውድ እና ምርጥ ሀብት ሁሉ ይሰጣሉ፡፡ ስለዚህች ዱንያ ፀጋ ቸልተኛ የሆነበትም ምክንያት የዱንያን ትክክለኛ ምንነት ያውቅ ስለነበር ነው፡፡ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- "በአላህ ይሁንብኝ የዱንያ እና የአኼራ ምሳሌ አንድ ጣትን ባህር ውስጥ ጨምሮ እንደማውጣት ነው፡፡ (ጣቱ) ምን ይዛ እንደምትመለስ ይመልከት፡፡"(ሶሂህ ሙስሊም)

Lady E. Cobold ወደ መካ ጉዞ በሚለው መፅሃፏ እንዲህ ትላለች "ሙሐመድ የአረቢያ ምድረ ሰላጤ መሪ ቢሆንም... እሱ ግን ስለ ስሙ ተጨንቆ አያውቅም፡፡ ስም ለማግኘትም እንቅስቃሴ አድርጎ አያውቅም፡፡ የአላህ መልክተኛ እና የሙስሊሞች አገልጋይ በሚለው መጠሪያ ስም ተብቃቅቶ ኖሯል፡፡ ቤቱን በራሱ ያፀዳ ነበር፤ ጫማውን በእጁ ይጠግን ነበር፤ ቸር እና አዛኝ ነበር፤ ድሀ ወይም ችግረኛ የጠየቀው ግዜ ብዙውን ግዜ ለራሱ እንኳን የማይበቃውም ቢሆን እጁ ላይ ያለውን ነገር አሳልፎ ይሰጣል፡፡"

5. አንዳንድ ግዜ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ማብራራት የሚጠበቅባቸው አጋጣሚ ይመጣ እና በዛ ጉዳይ ላይ ራዕይ ስላልወረደላቸው ያንን ጉዳይ መፍታት ያቅታቸዋል፡፡ ራእይ እስኪወርድላቸውም ድረስ በጣም ይጨነቃሉ፡፡ ከእነዚህ አጋጣሚዎች አንዱ በቤተሰባቸው ክብር ላይ የተወራው የውሸት ዜና አንዱ ነው፡፡ እውነታው ሳይወጣ ለአንድ ወር ጊዜ ያህል ጠላቶቻቸው ወሬ እየነዙባቸው እና እየተሳለቁባቸው ቆዩ፡፡ በመጨረሻም ከአንድ ወር የጭንቅ ግዜ በኋላ ራዕይ ወርዶ የባለቤታቸውን ዓኢሻ(ረ.ዐ) ንጽህና አወጀ፡፡ አታላይ እና አስመሳይ ቢሆኑ ኖሮ (አላህ ከዚህ አፅድቷቸዋል እንጂ) ወሬው መወራት በጀመረበት ቅፅበት ውስጥ ውሸት መሆኑን ተናግረው የቤተሰባቸውን ክብር ይጠብቁ ነበር፡፡
አላህ (ሰ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

وَمَا يَنطِقُ عَنِ الْهَوَىٰ [٥٣:٣]

"ከልብ ወለድም አይናገርም" (53፡3)

6. ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ከሰው በላይ እንዲያከብሩት እና እንዲያልቁት አልጠየቀም፡፡ እንደውም አንድ ሰው በራሱ ፍላጎት ተነስቶ ሲያልቃቸው ደስ አይላቸውም ነበር፡፡ አነስ ኢብኑ ማሊክ(ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት (ለሶሃቦች) ከረሱል(ሰ.ዐ.ወ) በላይ ተወዳጅ ሰው አልነበረም፡፡ ሲያዩት ግን አይቆሙም ነበር፡፡ ምክንያቱም ይህን ተግባር እንደሚጠላ ስለሚያውቁ ነው፡፡ (ሱነን ቲርሚዚ)
Washington Irving እንዲህ ይላል፡-
"ምንም እንኳን በጦርነቶች ላይ ድል ቢቀዳጁም ኩራተኛ እና አክብሩኝ ባይ አልሆኑም፡፡ ምክንያቱም የሚዋጉት ለእስልምና ብለው እንጂ የራሳቸውን ጥቅም ለማስከበር ስላልነበረ ነው፡፡ ስልጣኑ ታላቅ ደረጃ በደረሰበት ወቅት እንኳን በፊት በነበረበት መተናነስ እና ቀለል ያለ ኑሮ ዘውትሯል፡፡ ክፍል ውስጥ ባሉ ሰዎች ላይ ሲገባ አክብረው እንዲነሱለት

አልያም ሞቅ ያለ አቀባበል እንዲያደርጉለት አይፈልግም፡፡ ምንም እንኳ ታላቅ ስርወ መንግስት የመሰረተ ቢሆንም በስልጣኑ ላይ ፍትሀዊ ሆኖ አሳልፏል፡፡ ስልጣኑን ለቤተ ዘመዶቹ ለማውረስ እንኳን አስቦ አያውቅም፡፡"

7. ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) በሰራቸው ስራዎች ወይም በወሰነው ውሳኔ ላይ ወቀሳ እና እርማቶች የያዙ የቁርዓን አንቀጾች መውረዳቸው።

ሀ. አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

يَا أَيُّهَا النَّبِيُّ لِمَ تُحَرِّمُ مَا أَحَلَّ اللَّهُ لَكَ ۖ تَبْتَغِي مَرْضَاتَ أَزْوَاجِكَ ۚ وَاللَّهُ غَفُورٌ رَّحِيمٌ [٦٦:١]

*"አንተ ነብይ ሆይ! አላህ ለአንተ የፈቀደልህን ነገር ሚስቶችህን ማስወደድን የምትፈልግ ስትሆን (ባንተ ላይ) ለምን እርም ታደርጋለህ? አላህም እጅግ መሐሪና አዛኝ ነው፡፡" (66፡1)*

ይህ የወረደበት ምክንያት ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) የተወሰኑ ባለቤቶቻቸውን ለማስደሰት ማርን መብላት በራሳቸው ላይ እርም በማድረጋቸው ነበር፡፡ አላህ የፈቀደላቸውን ነገር በራሳቸው ላይ እርም ማድረግ እንደሌለባቸው ወቀሳ መጣባቸው፡፡

ለ. አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

عَفَا اللَّهُ عَنكَ لِمَ أَذِنتَ لَهُمْ حَتَّىٰ يَتَبَيَّنَ لَكَ الَّذِينَ صَدَقُوا وَتَعْلَمَ الْكَاذِبِينَ [٩:٤٣]

*"አላህ ከአንተ ይቅር አለ፡፡ እነዚያ እውነተኞቹ ላንተ እስከሚገለፁልህና ውሸታሞቹንም እስከምታውቅ ድረስ ለነርሱ (እንዲቀሩ) ለምን ፈቀድክላቸው፡፡" (9፡43)*

እዚህ ላይ ውሸታም መናፍቃንን ከተቡክ ዘመቻ ለመቅረት ያቀረቡትን ሰበብ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ምክንያት ስላቀረቡ ብቻ እውነተኝነታቸውን ለማረጋገጥ ምንም ጥረት ሳያደርጉ ለመቀበል መቸኮላቸውን ትክልል እንዳልነበረ ነግሯቸዋል፡፡

ሐ. አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

مَا كَانَ لِنَبِيٍّ أَن يَكُونَ لَهُ أَسْرَىٰ حَتَّىٰ يُثْخِنَ فِي الْأَرْضِ ۚ تُرِيدُونَ عَرَضَ الدُّنْيَا وَاللَّهُ يُرِيدُ الْآخِرَةَ ۗ وَاللَّهُ عَزِيزٌ حَكِيمٌ [٨:٦٧]

*"ለነብይ ምድር ላይ እስኪያደክም ድረስ ለእርሱ ምርከኞች ሊኖሩት አይገባም፡፡ የቅርበቱን አለም ጠፊ ጥቅም ትፈልጋላችሁ፡፡ አላህም መጨረሻይቱን ይሻል፡፡ አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው፡፡" (8፡67)*

መ. አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

لَيْسَ لَكَ مِنَ الْأَمْرِ شَيْءٌ

*"ላንተ ከነገሩ ምንም የለህም..." (3፡128)*

ሠ. አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

عَبَسَ وَتَوَلَّىٰ ۝ أَن جَاءَهُ الْأَعْمَىٰ ۝ وَمَا يُدْرِيكَ لَعَلَّهُ يَزَّكَّىٰ

*"ፊቱን አጨፈገገ፤ ዞረም ዕውሩ ስለመጣው፡፡ ምን ያሳውቅሃል? (ከኃጥያቶቹ) ሊጥራራ ይችላል..." (80፡1-3)*

አታላይ እና አስመሳይ ቢሆኑ ኖሮ (አላህ ከዚህ አጥርቷቸዋል እንጂ) እራሳቸውን የሚወቅሱ አንቀፆች ቁርአን ውስጥ ባልተገኘ ነበር፡፡

Lightner "የእስልምና ሀይማኖት" በሚለው መፅሀፉ ውስጥ እንዲህ ይላል፡- "ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) ሀብታም እና የተከበሩ ሰዎችን ጥሪ ሲያደርጉ በመጣባቸው ድሀ ሰው ላይ ፊታቸውን በማጨፍገጋቸው አላህ ጠንከር ያለ ወቀሳ ሰንዝሮባቸዋል፡፡ ክርስቲያን መሀይማኖች እንደሚሉት ቢሆን ኖሮ እንዲህ አይነት አንቀፆች ቁርአን ውስጥ ባልተገኙ ነበር፡፡"

8. ነብይ ስለመሆናቸው ካሉት እርግጠኛ ማስረጃዎች መካከል አንዱ በሱረቱል መሠድ ላይ በእርግጠኝነት የተፃፈው የአጎታቸው የአቡ ለሃብ ጀሀነም መግባት ነው፡፡ ይህም ምዕራፍ የወረደው ገና ጥሪያቸውን በጀመሩበት ግዜያት ነበር፡፡ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) አስመሳይ እና አታላይ ቢሆኑ ኖሮ (አላህ ከዚህ ነገር አጥርቷቸዋል እንጂ) አጎታቸው አቡ ለሃብ ሊሰልም የሚችልበት አጋጣሚ ይኖራል ብለው ስለሚያስቡ እንደዚህ አይነት እርግጠኛ ውሳኔ አይወስኑበትም ነበር፡፡

Dr. Gary miller እንዲህ ይላሉ፡-

"አቡ ለሃብ እስልምናን በጣም ከመጥላቱ የተነሳ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) በሄዱበት ቦታ ሁሉ እየተከተለ ንግግሩን ለማሳጣት ይጥር ነበር፡፡ እንግዳ ሰዎችን ሙሐመድ ሲያናግር ካየ አናግሯቸው እስኪጨርስ ይጠብቅና 'ሙሐመድ ምንድ ነው ያላችሁ?' ብሎ ይጠይቃቸዋል፡፡ "እሱ ነጭ ነው ብሏችሁ ከሆነ ጥቁር ነው፡፡ ቀን ነው ብሏችሁ ከሆነ ደግሞ ማታ ነው" ይላቸው ነበር፡፡ ምንም ነገር ቢሆን ከሙሐመድ የሰማውን ተቃራኒውን ነገር ይናገራል፡፡ አቡ ለሀብ ከመሞቱ 10 ዓመታት በፊት ሱረቱል መሰድ ወረደች፡፡ ይህች ምዕራፍ አቡ ለሀብ ወደ ጀሀነም እንደሚገባ በእርግጠኝነት ትናገራለች። በሌላ ቋንቋም አቡ ለሀብ እስልምናን ሳይቀበል ይሞታል ማለት ነው፡፡ በእነዚህ 10 ዓመታት ውስጥ ረሱልን(ሰ.ዐ.ወ) ለማስዋሸት እና ዳዕዋቸውን ለማፍረስ ከአቡ ለሀብ የሚጠበቅበት የነበረው ሰዎች ዘንድ ወጥቶ "ሙሐመድ እኔ እስልምናን እንደማልቀበል እና ጀሀነም እንደምገባ ተናግሯል፡፡ ነገር ግን አሁን እኔ እስልምናን ተቀብዬ ሙስሊም ለመሆን ወስኛለሁ!! አሁንስ ሙሐመድ እውነተኛ ነውን? ይወርድልኛል የሚለው ራዕይስ እውነት ከአላህ ነው?" ማለት ብቻ ነበር። ነገር ግን ይህንን ማድረግ አልቻለም፡፡ ምንም እንኳን አቡ ለሀብ በሚሰራው ስራ ሁሉ የረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ተቃራኒ ቢሆንም በዚህ ጉዳይ ግን ሊቃረናቸው አልቻለም፡፡ እንደውም ሁኔታው ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ለአቡ ለሀብ "አንተ በጣም ትጠላኛለህ። ዳዕዋዬንም ልታበላሽ ትለፋለህ፡፡ ነገሩ እንዲዚህ ከሆነ ይኸውልህ ፍላጎህን የምታሳካበት ጥሩ እድል ሰጥቸሃለው እና ተጠቀምበት" የሚሉት ይመስላል፡፡ ነገር ግን አቡ ለሃብ በ10 መታት ውስጥ ይህንን ማድረግ አልቻለም፡፡ አልሰለመም፤ ኧረ እንደውም ለማስመሰልም አልሞከረም፡፡

10 ዓመታት ሁሉ በአንድ ደቂቃ ውስጥ እስልምናን የሚያጠፋበት እድል ተሰጥቶት ነበር፡፡ ነገር ግን ቁርአን የሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) ንግግር ሳይሆን ሩቁን እና ድብቁን ከሚያውቀው፤ አቡለሃብ እስልምናን እንደማይቀበል ከሚያውቀው አምላክ የተወረደ ነው፡፡ ቁርዓን ከአላህ ዘንድ የመጣ ባይሆን ኖሮ ሙሐመድ አቡለሀብ 10 አመታት ሙሉ እንደማይሰልም በምን እርግጠኛ መሆን ቻሉ፡፡

እንደዚህ አይነት አደገኛ ውሳኔዎችን ከአላህ ዘንድ ካልሆነ ማን ሊያስቀምጥ ይችላል፡፡"

تَبَّتْ يَدَا أَبِي لَهَبٍ وَتَبَّ ۝ مَا أَغْنَىٰ عَنْهُ مَالُهُ وَمَا كَسَبَ ۝ سَيَصْلَىٰ نَارًا ذَاتَ لَهَبٍ ۝ وَامْرَأَتُهُ حَمَّالَةَ الْحَطَبِ ۝ فِي جِيدِهَا حَبْلٌ مِّن مَّسَدٍ

*"የአቡ ለሀብ ሁለት ኢጆች ከሰሩ (ጠፉ፤ እርሱ) ከሰረም፡፡ ከእርሱ ገንዘቡና ያም ያፈራው ሁሉ ምንም አልጠቀመውም፡፡ የመንቀልቀል ባለቤት የኾነችን እሳት በእርግጥ ይገባል፡፡ ሚስቱም(ትገባለች)፤ እንጨት ተሸካሚ ስትሆን፡፡ በአንገትዋ ላይ ከጭረት የሆነ ገመድ ያለባት ስትሆን፡፡" (111፡1-5)*

9. በአንዳንድ አንቀፆች ላይ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ሙሐመድ በሚለው ስማቸው ፈንታ አህመድ መባላቸው፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

   *"የመርየም ልጅ ዒሳም፡- "የእስራኤል ልጆች ሆይ! እኔ ከተውራት በፊት ያለውን የማረጋግጥ እና ከእኔ በኋላ በሚመጣው መልዕክተኛ ስሙ አህመድ በኾው የማበሰር ስሆን ወደ እናንተ (የተላክሁ) የአላህ መልክተኛ ነኝ" ባለ ጊዜ (አስታውስ)፡፡ በግልፅ ተዓምራቶቹ በመጣቸው ግዜ "ይህ ግልጽ ድግምት ነው" አሉ፡፡"*

   ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) አስመሳይ እና አታላይ ቢሆኑ ኖሩ (አላህ ከዚህ ጠብቋቸዋል እንጂ) በሕዝቦቻቸው ዘንድ የሚታወቁበትን ስም ትተው 'አህመድ' የሚለውን አይጠቀሙም ነበር፡፡

10. እስልምና ሀይማኖቱ እስከ ዛሬ ድረስ መቆየቱ እና በፍጥነት ዓለም ላይ እየተስፋፋ መሆኑ፡፡ እልፎች እስልምናን ከሌላ ሀይማኖቶች በመምረጥ እየተቀበሉት ነው፡፡ ይህ የሚሆነው ደግሞ ወደ እስልምና የሚጣሩ በቂ ሰዎች እና ድርጅቶች በሌሉበት እና የእስልምና ጠላቶች እስልምናን ለማጥፋት ቀን ከሌት እየለፉ ባለቡት ወቅት ነው፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ሀይማኖቱ ከአላህ(ሱ.ወ) ጥበቃ በማግኘቱ ነው፡፡

    አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

    إِنَّا نَحْنُ نَزَّلْنَا الذِّكْرَ وَإِنَّا لَهُ لَحَافِظُونَ

    *"እኛ ቁርኣንን እኛው አወረድነው፡፡ እኛም ለእርሱ ጠባቂዎቹ ነን፡፡" (15፡9)*

    እንግሊዛዊው ፀሐፊ Thomas Carlyle እንዲህ ይላል፡፡

    "ውሸታም የሆነ ሰው አስጋራሚ የሆነ ሀይማኖትን ሲያስገኝ አይታችሁ ታውቃላችሁ? በግንባታ ላይ ጥልቅ እውቀት የሌለው ሰው ፎቅ ቤት መስራት አይችልም፡፡ እሰራለሁ ብሎ ከተነሳም ሊሰራ የሚችለው ትክክለኛ ቤትን ሳይሆን ዝም ብሎ የአሸዋ ክምርን ነው፡፡ 14 ምዕተ አመታትንም በቢሊዮኖች የሚሆኑ ነዋሪዎችን ይዞ ሊቆይ አይችልም፡፡ ወዲያውኑ ይፈራርሳል፡፡ አንድ ሰው ከተፈጥሮ የሚፈልገውን ነገር ለማግኘት እንቅስቃሴው ሁሉ በተፈጥሮ ህግ የተገደበ ሊሆን ይገባል፡፡

    ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ቁርአንን ጠብቀዋል፡፡ አላህም በመፅሀፍ እና ከግዜ ወደ ግዜ በሰዎች ልብ ውስጥ ጠብቆታል። በእርግጥም ቁርአንን መሸምደድ፣ ማንበብ እና መማር ሁሉም ሙስሊም የሚተገብረውና የሚሽቀዳደምበት ተግባር ነው፡፡ ምክንያቱም ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋልና ነው፡-"ከእናንተ ውስጥ በላጩ ቁርአንን ተምሮ ያስተማረው ነው።"

ፊደሎችን ለመለወጥ፣ ቁርአን ላይ ለመጨመር እና ለመቀነስ ብዙ ሙከራዎች ተደርገዋል፡፡ ነገር ግን አንደኛቸውም ተሳክቶላቸው አያውቅም፡፡ ምክንያቱም በፍጥነት እና በቀላል መንገድ ስለሚይያዝ እና ከትክክለኛው ቁርአን ስለሚልለዩ ነው፡፡

ሁለተኛው የእስልምና መሰረታዊ መፅሀፍ የሆነው ሀዲስ ደግሞ ታማኝ እና ስራቸው ይህ ብቻ በሆኑ ሰዎች ተጠብቋል፡፡ ከሀዲሶች ውስጥ የትኛው ትክክል እና የትኛው ደካማ እንደሆነ አጣርተው ለይተዋል፡፡ 'ሙስጠለሀል ሐዲስ' የተሰኘውን ዘርፍ ያጠና ሰው እነዚህ ሰዎች የለፉትን ልፋት እና ትክክለኛውን ሀዲስ ከፈጠራ ለመለየት ያደረጉትን ከፍተኛ ጥንቃቄ ይረዳል፡፡ እነሱ ትክክል ነው ያሉትን ሀዲስም ከመጠራጠር ይወገዳል፡፡

Michael Hart እንዲህ ይላል፡-
"ሙሐመድ በእርግጥም ከአለማችን ታላላቅ ሀይማኖት ውስጥ አንዱን መስርቶ አስፋፍቷል፡፡ ከአለማችንም ታላላቅ የፖለቲካ መሪዎችም ውስጥ አንዱ መሆን ችሏል፡፡ በዚህ ዘመን 13 ምዕተ አመታት ካለፈው በኋላ እንኳን አስተምህሮው ሀይለኛ እና ተፅዕኖ ፈጣሪ ነው፡፡

11. ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) የመጣባቸው መርሆዎች እውነተኝነት እና ለሁሉም ዘመን እና ቦታ ተስማሚ መሆኑ፡፡ እስልምናን በመተግበር የሚገኙ ፍሬዎች እና ውጤቶች በሙሉ እስልምና የመጣው ከአላህ ዘንድ መሆኑን ይመሰክራሉ፡፡ ከሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) በፊት ብዙ ነብያቶች መምጣታቸው እሱን ነብይ እንዳይሆን የሚከለከለው ነገር አለን? የሚከለከለው ነገር እንደሌለ እየታወቀ ከሱ በፊት ያሉትን ነብያቶች እየተቀበላችሁ እሱን የምትክዱት ለምንድ ነው?

12. አንድ ሰው ብቻውን እንደ እስልምና ስለማህበራዊ ኑሮ፣ ስለ ጦርነት፣ ስለትዳር፣ ስለኢኮኖሚ፣ ስለፖለቲካ እና ስለ ሌላም የሕይወት ዘርፎች የተሟላ ህግጋቶችን የያዘ ሀይማኖት መፈልሰፍ አይችልም፡፡ እንዴት አንድ መፃፍ እና ማንበብ የማይችል ሰው እንደዚህ ያለ ሀይማኖት ይፈለስፋል ተብሎ ይጠረጠራል? ታዲያ ይህ እውነተኛ ነብይ መሆኑን እና ከስሜቱ እንደማይናገር ግልጽ ማስረጃ አይደለምን?

13. ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ዳዕዋቸውን በይፋ የጀመሩት 40 አመት ከሞላቸው በኋላ መሆኑ፡፡ ሰዎችን እንዲጠሩ የታዘዙት የወጣትነት፣ የግንፍልተኝነት እና የሐይለኝነት ግዜ አልፎ የአስተዋይነት እና እረፍት እረፍት በሚያሰኝበት ግዜ ነው፡፡

R. Landau እስልምና እና አረብ በሚለው መጽሀፉ ውስጥ እንዲህ ይላል፡-

.

.

.

.

.

.

## ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛ ናቸው ብሎ መመስከር ምንን አካቶ ይይዛል?

1. እሳቸው የተላኩት ለሳቸው ሀገር እና ሕዝብ እንዲሁም በነሱ ዘመን ለነበሩ ሰዎች ብቻ ሳይሆን ለሰው ልጅ በሙሉ እንደሆነ ማመን:: መልዕክታቸው ያለ ቦታ እና ግዜ ገደብ እስከጨረሻ ቀን ላሉ ሰዎች በሙሉ ነው::
   አላህ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

   تَبَارَكَ الَّذِي نَزَّلَ الْفُرْقَانَ عَلَىٰ عَبْدِهِ لِيَكُونَ لِلْعَالَمِينَ نَذِيرًا

   "ያ ፋርቃንን በባሪያው ላይ ለዓለማት አስፈራሪ ይኾን ዘንድ ያወረደው (አምላክ) ክብር እና ጥራት ተገባው::" (25፡1)

2. ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ከአላህ(ሱ.ወ) በሚያስተላልፉት መልዕክተ ላይ ከስህተት እንደተጠበቁ ማመን:: አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

   وَمَا يَنطِقُ عَنِ الْهَوَىٰ ۝ إِنْ هُوَ إِلَّا وَحْيٌ يُوحَىٰ

   "ከልብ ወለድም አይናገርም:: እርሱ (ንግግሩ) የሚወርድ ራእይ እንጅ ሌላ አይደለም:: እርሱ (ንግግሩ) የሚወርድ ራዕይ እንጂ ሌላ አይደለም::" (53፡3-4)
   ሀይማኖታዊ ባልሆኑ ጉዳዮች ላይ ግን ልክ እንደ ሰው ናቸው:: ኢጅቲሀድ ያደርጉ ነበር:: ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-
   "እኔ ዘንድ ተካስሳችሁ ትመጣላችሁ:: አንደኛችሁ ከሌላኛው ክርክር ላይ አንደበተ ርቱዕ ይሆንና በምሰማው መሠረት ለሱ እፈርድለታለሁ:: ከወንድሙ ሀቅ የሰጠሁት ሰው እኔ የምፈርድለት ነገር የእሳት ቁራጭ ነውና፡ ከፈረድኩለት ነገር ምንንም አይውሰድ::" (ቡኻሪ እና ሙስሊም)

3. የረሱል(ሰ.ዐ.ወ) መልላክ ለሰው ልጆች እዝነት መሆኑን ማመን::
   አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

   وَمَا أَرْسَلْنَاكَ إِلَّا رَحْمَةً لِّلْعَالَمِينَ [٢١:١٠٧]

   "(ሙሐመድ! ሆይ) ለአለማትም እዝነት አድርገን እንጂ አልላክንህም::" (21፡107)

   አላህ(ሱ.ወ) እውነትን ተናግሯል:: በእርግጥም ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) ለዓለማት እዝነት ናቸው:: የሰውን ልጅ ባሪያን ከማምለክ የባሪያዎችን አምላክ ወደ ማምለክ፣ ከተለያዩ ሀይማኖቶች አድሎ ወደ እስልምና ፍትህ እንዲሁም ከዱንያ ጥበት ወደ አኼራ ስፋት አሸጋግሯል::

4. የመልዕክተኞች መደምደሚያ እና ከሁሉም በላጭ መሆናቸውን በጥብቅ ማመን:: ከሳቸው በኋላ ነብይ ሊመጣ አይችልም:: አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

   مَّا كَانَ مُحَمَّدٌ أَبَا أَحَدٍ مِّن رِّجَالِكُمْ وَلَٰكِن رَّسُولَ اللَّهِ وَخَاتَمَ النَّبِيِّينَ ۗ وَكَانَ اللَّهُ بِكُلِّ شَيْءٍ عَلِيمًا [٣٣:٤٠]

*"ሙሐመድ ከወንዶቻችሁ የአንድም ሰው አባት አይደለም፡፡ ግን የአላህ መልዕክተኛ እና የነቢዮች መደምደሚያ ነው፡፡" (33፡40)*

ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- "ከሌሎች ነብያቶች በ6 ነገሮች እንድበልጥ ተደርጊያለው፡- 'ጀዋሚአል ከላምን' ተሰጥቶኛል(በተወሰኑ ቃላት ሰፊ መልዕክት ማስተላለፍ)፣ በጠላቶች ልብ ውስጥ መፈራትን ተደርጎልኛል፣ ወደ ሰው ልጅ በሙሉ ተልኬያለው፣ የነብያቶች መደምደሚያ ተደርጌያለው፣ የምርኮ ገንዘብ ሀላል ተደርጎልኛል፣ መሬት በሙሉ መስጅድ እና ጦሃራ ተደርጎልኛል፡፡" (ሙስሊም እና ቲርሚዚ)

5. በሁሉም ነገር የተሟላ ሀይማኖት አስተላልፈዋል፡፡ ማንም ሰው ሊጨምር ወይም ሊቀንስ አይችልም፡፡ አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

الْيَوْمَ أَكْمَلْتُ لَكُمْ دِينَكُمْ وَأَتْمَمْتُ عَلَيْكُمْ نِعْمَتِي وَرَضِيتُ لَكُمُ الْإِسْلَامَ دِينًا ۚ

*"ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ፡፡ ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ፡፡ ለእናንተም ኢስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ፡፡" (5:3)*

እስልምና ሁሉንም ነገር ያቀፈ እና ያካተተ ሀይማኖት ነው፡፡ በፖለቲካውም፣ በኢኮኖሚያዊውም ሆነ በማህበራዊ ዘርፍ ያጓደለው ነገር የለም፡፡

እንግሊዛዊው Kwelem 'አቂደቱል ኢስላሚያ' በሚለው መጽሀፍ ውስጠ እንዲህ ይላል፡-

"የቁርአን ድንጋጌዎች በአምልኮአዊ እና ሀይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ ብቻ ያነጣጠረ አይደለም፡፡ ለእስልምናው ዓለም ሁሉን ነገር ያካተተ ሕገመንግስት ነው፡፡ የጦርነት ጉዳይን፣ የሲቪል አገልግሎትን፣ የንግድን፣ የዳኝነትን፣ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግጋቶችን አጠቃሎ የያዘ ነው፡፡ ከዛም ባለፈ መልኩ ከሀይማኖታዊ ጉዳዮች አንስቶ እስከ ዱንያዊ ጉዳዮች፤ ሕይወት ከማዳን አንስቶ እስከ ስለጤንነት ጉዳይ፤ ከሕዝባዊ ሙብቶች አንስቶ እስከ ግለሰባዊ ሙብት፣ ከግለሰባዊ ጥቅሞች አንስቶ እስከ ማህበረሰባዊ ጥቅሞች፣ ከሰናይ ምግባሮች አንስቶ እስከ እኩይ ምግባራት፤ ከዱንያዊ ቅጣቶች አንስቶ እስከ አኼራዊ ቅጣት የሚተነትን አጠቃላይ መመሪያ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ምንም ሀይማኖታዊ መሰረቶችን ካላካተተው ባብዛኛው ታሪኮችን እና ፈጠራዎችን ካጠራቀመው መፅሀፍ ቅዱስ አንፃር ቁርዓን በጣም ይለያል፡፡

6. ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) ከአላህ ዘንድ የተጫነበትን አደራ አድርሷል፣ ተልዕኮውንም ተወጥቷል ህዝቦቹንም መክሯል ብሎ ማመን፡፡ ጥሩ የተባለን ነገር ሁሉ አመላክተዋል፡፡ በሱም ላይ አዝዘዋል፤ መጥፎ የተባለን ነገር ሁሉ አስጠንቅቀዋል ከልክለዋልም፡፡ በስንብቱ ሀጅ ዲስኩራቸው ላይ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- "አዋጅ! የአላህን መልክት አላደረስኩምን?" እነሱም(ሰሀቦች)፡- "አዎን አድርሰዋል" አሉ፡፡ ረሱልም(ሰ.ዐ.ወ) "አላህ ሆይ! ምስክር ሁነኝ" አሉ። (ቡኻሪ እና ሙስሊም)

7. ነብዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) ከተላኩ በኋላ አላህ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ብቸኛ ሀይማኖት እሳቸው ላይ የወረደው ሀይማኖት መሆኑን ማመን፡፡ ከሳቸው ሀይማኖት ውጪ ባሉ ሀይማኖቶች መንገድ ጌታን ማምለክ አይቻልም፡፡ አላህም አይቀበልም፡፡ ሁሉንም ሰው አላህ(ሱ.ወ) የሚተሳሰበው እሳቸው ይዘው በመጡት ድንጋጌዎች ነው፡፡ ምክንያቱም አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ብሏልና፡-

وَمَن يَبْتَغِ غَيْرَ الْإِسْلَامِ دِينًا فَلَن يُقْبَلَ مِنْهُ وَهُوَ فِي الْآخِرَةِ مِنَ الْخَاسِرِينَ [٣:٨٥]

*"ከኢስላም ሌላ ሀይማኖትን የሚፈልግ ሰው ፈፅሞ ከርሱ ተቀባይ የለውም:: እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎቹ ነው::" (3:85)*

8. ለሳቸው መታዘዝ

አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

وَمَن يُطِعِ اللَّهَ وَالرَّسُولَ فَأُولَٰئِكَ مَعَ الَّذِينَ أَنْعَمَ اللَّهُ عَلَيْهِم مِّنَ النَّبِيِّينَ وَالصِّدِّيقِينَ وَالشُّهَدَاءِ وَالصَّالِحِينَ ۚ وَحَسُنَ أُولَٰئِكَ رَفِيقًا [٤:٦٩]

*"አላህንና መልዕክተኛውንም የሚታዘዝ ሰው እነዚያ ከእነዚያ አላህ በእነርሱ ላይ ከለገሳቸው ነብያት፣ ከፃድቃንም፣ ከሰማዕታትም፣ ከመልካሞቹ ጋር ይኾናሉ:: የእነዚያም ጓደኝነት አማረ::" (4:69)*

እሳቸውን መታዘዝ ማለት ስሩ ያሉትን ነገር መስራት ከከለከሉት ነገር መከልከል ናቸው:: አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ይላል:-

وَمَا آتَاكُمُ الرَّسُولُ فَخُذُوهُ وَمَا نَهَاكُمْ عَنْهُ فَانتَهُوا

*"መልክተኛውም የሰጣችሁን (ማንኛውንም) ነገር ያዙት:: ከእርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ::" (አልሀርሽ 7)*

አላህ (ሱ.ወ) እሳቸውን የሚያምፅ ሰው ቅጣቱ ምን እንደሆነ አብራርቷል:-

وَمَن يَعْصِ اللَّهَ وَرَسُولَهُ وَيَتَعَدَّ حُدُودَهُ يُدْخِلْهُ نَارًا خَالِدًا فِيهَا وَلَهُ عَذَابٌ مُّهِينٌ [٤:١٤]

*"አላህንና መልዕክተኛውንም የሚያምጽ ወሰኖቹንም የሚተላለፍ በውስጧ ዘውታሪ ሲኾን እሳትን ያገባዋል:: ለርሱም አዋራጅ ቅጣት አለው::" (4:14)*

9. ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) የሰጡትን ፍርድ ወዶ መቀበል እና እሳቸው የደነገጉትን ነገር አለማመፅ::

አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ይላል:-

فَلَا وَرَبِّكَ لَا يُؤْمِنُونَ حَتَّىٰ يُحَكِّمُوكَ فِيمَا شَجَرَ بَيْنَهُمْ ثُمَّ لَا يَجِدُوا فِي أَنفُسِهِمْ حَرَجًا مِّمَّا قَضَيْتَ وَيُسَلِّمُوا تَسْلِيمًا

*"በጌታህም እምላለሁ በመካከላቸው በተከራከሩበት ፍርድ እስከሚያስፈርዱህ ከዚያም ከፈረድከው ነገር በነፍሶቻቸው ውስጥ ጭንቀትን እስከማያገኙና ፍጹም መታዘዝንም እስከሚታዘዙ ድረስ አያምኑም፤ (ምእመን አይኾኑም)::" (4:65)*

በተጨማሪም እሳቸው ያመጡትን ሕግ ምድር ላይ ካሉት የትኛውም ዓይነት ህግ እና ደንብ ማስቀደም:: አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

أَفَحُكْمَ الْجَاهِلِيَّةِ يَبْغُونَ ۚ وَمَنْ أَحْسَنُ مِنَ اللَّهِ حُكْمًا لِّقَوْمٍ يُوقِنُونَ [٥:٥٠]

*"የመሀይምንነትን ፍርድ ይፈልጋሉ፤ ለሚያረጋግጡም ሰዎች ከአላህ ይበልጥ ፍርዱ ያማረ ማን ነው?" (5:50)*

10. የረሱልን(ሰ.ዐ.ወ) ሱና መከተል

አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

قُلْ إِن كُنتُمْ تُحِبُّونَ اللَّهَ فَاتَّبِعُونِي يُحْبِبْكُمُ اللَّهُ وَيَغْفِرْ لَكُمْ ذُنُوبَكُمْ ۗ وَاللَّهُ غَفُورٌ رَّحِيمٌ [٣:٣١]

*“በላቸው፡- አላህን የምትወዱ እንደሆናችሁ ተከተሉኝ፤ አላህ ይወዳችኋልና፡፡ ኃጢአቶቻችሁንም ለናንተ ይምራልና፡፡ አላህም መሀሪ እና አዛኝ ነው፡፡” (አልዒምራን)*

የእሳቸውን ፈለግ አጥብቆ መያዝ፡፡ እሳቸው በሄዱበት መሄድ እና ለሕይወትህ ሞዴል አድርገህ መያዝ፡፡ አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

“ለእናንተ አላህንና የመጨረሻውን ቀን የሚከጅል ለሆነ ሰው፣ አላህንም ብዙ ለሚያወሳ በአላህ መልዕክተኛ መልካም መከተል አልለላችሁ፡፡”

እሳቸውን ለመከተል የፈለገ ሰው የህይወት ታሪካቸውን መማርና ማወቅ ይኖርበታል፡፡ ዘይኑል ዓቢዲን(ረሂሙሁላህ) (አልይ ኢብኑ ሁሰይን ኢብኑ አልይ ኢብኑ አቢጣሊብ) እንዲህ ይላሉ፡- “ቁርአንን እንደምንማረው ሁሉ የረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ዘመቻዎች እንማር ነበር፡፡”

11. ረሱልን(ሰ.ዐ.ወ) አላህ ባከበራቸው መልኩ ማክበር፡፡ በጣም ከደረጃቸው ከፍ ማድረግ እንዲሁም ዝቅ ማድረግም የለብንም፡፡ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- “ከደረጃዬ በላይ ከፍ አታድርጉኝ፤ አላህ ረሱል ከማድረጉ በፊት ባሪያው አድርጎኛልና፡፡” (ጦበራኒ)

12. ስማቸው ሲወሳ ሶላዋት በሳቸው ላይ ማውረድ

አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

إِنَّ اللَّهَ وَمَلَائِكَتَهُ يُصَلُّونَ عَلَى النَّبِيِّ ۚ يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا صَلُّوا عَلَيْهِ وَسَلِّمُوا تَسْلِيمًا [٣٣:٥٦]

*“አላህና መላእክቱ በነቢዩ ላይ የአክብሮት እዝነትን ያወርዳሉ፡፡ እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በእርሱ ላይ የአክብሮት እዝነትን አውርዱ፡፡ የማክበርንም ሰላምታ ሰላም በሉ፡፡”* (33፡56)

ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

“ስግብግብ ማለት አጠገቡ ተወስቼ ሰለዋት ያላወረደብኝ ሰው ነው፡፡” (ቲርሚዚ)

13. ረሱልን(ሰ.ዐ.ወ) መውደድ እና ማክበር፤ ከሌላ ነገር ውዴታ የሳቸውን ማስቀደም፡፡ ምክንያቱም ከአላህ ቀጥሎ ሰዎች ትክክለኛውን መንገድ እንዲይዙ እና በመጪው ዓለም ደስታን እንዲያገኙ ሰበብ የሆኑት እሳቸው ስለሆኑ ነው፡፡

አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

قُلْ إِن كَانَ آبَاؤُكُمْ وَأَبْنَاؤُكُمْ وَإِخْوَانُكُمْ وَأَزْوَاجُكُمْ وَعَشِيرَتُكُمْ وَأَمْوَالٌ اقْتَرَفْتُمُوهَا وَتِجَارَةٌ تَخْشَوْنَ كَسَادَهَا وَمَسَاكِنُ تَرْضَوْنَهَا أَحَبَّ إِلَيْكُم مِّنَ اللَّهِ وَرَسُولِهِ وَجِهَادٍ فِي سَبِيلِهِ فَتَرَبَّصُوا حَتَّىٰ يَأْتِيَ اللَّهُ بِأَمْرِهِ ۗ وَاللَّهُ لَا يَهْدِي الْقَوْمَ الْفَاسِقِينَ [٩:٢٤]

*"አባቶቻችሁና ወንዶች ልጆቻችሁ፣ ወንድሞቻችሁም፣ ሚስቶቻችሁም፣ ዘመዶቻችሁም፣ የሰበሰባችኋቸው ሀብቶችም፣ መክሰሩዋን የምትፈሩዋት ንግድም፣ የምትወዷቸው መኖሪያዎችም እናንተ ዘንድ ከአላህና ከመልክተኛው በርሱ መንገድም ከመታገል ይበልጥ የተወደዱ እንደኾኑ አላህ ትእዛዙን እስከሚያመጣ ድረስ ተጠባበቁ» በላቸው፡፡ አላህም አመጸኞች ሕዝቦችን አይመራም፡፡" (9፡24)*

እሳቸውን መውደድ ያለውን ጠቀሜታ የመቀስቀሻ ቀን መቼ ነው ብሎ ለጠየቃቸው ሰውዬ በሰጡት መልስ ግልፅ አድርገዋል፡፡ "የመጨረሻይቱ ቀን መቼ ነው?" አላቸው እሳቸውም "ምን አዘጋጅተህላታል?" አሉት፡፡ ሰውየውም አሰብ አደረገና "ያረሱሉሏህ! ያዘጋጀሁት ብዙ ፆም፣ ሶላት ወይም ሶደቃ የለም ነገር ግን አላህንና መልዕክተኛውን እወዳለሁ" አላቸው። እሳቸውም፡- "(የመቀስቀሻው ቀን) አንተ ከምትዳቸው ጋር ነህ፡፡" (ቡኻሪና ሙስሊም)

ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- 3 ነገር ያሉበት ሰው የኢማንን ጥፍጥና በእርግጥ አግኝቷል፡፡ አላህና መልዕክተኛው እሱ ዘንድ ከነሱ ውጭ ካለ ነገር ሁሉ የበለጡ ተወዳጅ ሲሆኑ፤ አንድን ሰው ሲወድ ለአሏህ ብቻ ብሎ ሲሆን፤ አላህ ካዳነው በኋላ ወደ ኩፍር መመለስን እሳት ላይ መጣልን እንደሚጠላ አድርጎ ሲጠላ ነው፡፡" (ሙስሊም)

ረሱልን(ሰ.ዐ.ወ) መውደድ እሳቸው የወደዱትን ሰው መውደድን ያካትታል፡፡ ለምሳሌ ቤተ ዘመዶቻቸውን እና ባልደረቦቻቸውን፡፡ በተመሳሳይ መልኩ እሳቸው የጠሉትን መጥላት፣ ወዳጅ አድርጎ የያዙትን መወዳጀት፣ የራቁትን መራቅን ሁሉ ያካትታል፡፡ ምክንያቱም ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ሲወዱም ሆነ ሲጠሉ በአላህ መንገድ ላይ ስለሆነ ነው፡፡

14. እሳቸው ይዘው የመጡትን ዲን በብልሀት እና በመልካም ግሳፄ ለማስፋፋት እና ላልደረሰው ሰው ለማድረስ ዳዕዋ ማድረግ፡፡ ይህን የምንፈፅመውም ያልተማረን በማስተማር እና የዘነጋን በማስታወስ ነው፡፡
አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

ادْعُ إِلَىٰ سَبِيلِ رَبِّكَ بِالْحِكْمَةِ وَالْمَوْعِظَةِ الْحَسَنَةِ ۖ وَجَادِلْهُم بِالَّتِي هِيَ أَحْسَنُ ۚ إِنَّ رَبَّكَ هُوَ أَعْلَمُ بِمَن ضَلَّ عَن سَبِيلِهِ ۖ وَهُوَ أَعْلَمُ بِالْمُهْتَدِينَ [١٦:١٢٥]

*"ወደ ጌታህ መንገድ በብልሃትና በመልካም ግሳጼ (በለዘብታ ቃል) ጥራ፡፡ በዚያችም እርሷ መልካም በኾነችው (ዘዴ) ተከራከራቸው፡፡ ጌታህ እርሱ ከመንገዱ የተሳሳተውን ሰው ዐዋቂ ነው፡፡ እርሱም ቅን የኾኑትን ሰዎች ዐዋቂ ነው፡፡* (16፡125)

ረሱልም (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል "አንዲትንም አንቀፅ ቢሆን ከኔ አስተላልፉ" (ሙስሊም)

15. ለሳቸው እና ለሱናቸው ዘብ መቆም፡፡
ይህን የምናደርገውም በሳቸው ላይ የሚነሱ ቅጥፈቶችን በማጋለጥ እና ስለእርሳቸው ሀቁን ለማያውቁ ሁሉ በማሳወቅ ነው፡፡ እንዲሁም ለሱናቸው ዘብ መቆም ማለት የእስልምና ጠላቶች እና ምቀኞች የሚነዙትን አሉባልታ እና ማጥላያ በመቃወምና እውነታውን ግልፅ በማውጣት ነው፡፡

16. ሱናቸውን አጥብቆ መያዝ

ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- "የእኔን እና ከኔ በኋላ ያሉ ቅኑን መንገድ የተመሩትን ኸሊፋዎች ፈለግ አደራ፡፡ በመንጋጋችሁ ነክሳችሁ ያዟት፡፡ መጤ ነገራቶችን ወየውላችሁ፡፡ ሁሉም "ቢድዓ" ደግሞ ጥመት ነው፡፡" (ቡኻሪ እና ሙስሊም)

## መደምደሚያ

ይህንን ጥናታዊ ጽሁፍ በፈረንሳዊው ገጣሚ Lamartaine ንግግር እንደመድመዋለን፡፡

እንዲህ ይላል፡-

በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ አስቦትም ይሁን ሳያስበው እንደዚህ እጅግ ግዙፍ የሆነ አላማ ይዞ የተነሳ የለም፡፡ በእርግጥ ሀሳቡ የሰው ልጅ መሸከም ከሚችለው በላይ ነው፡፡ በዚህ ተግባር በሰው ልጅ እና በፈጣሪ መካከል ግርዶሽ የሆኑትን ጥሜቶች ሁሉ አስወግዷል፡፡ በዚህም አማካኝነት ፈጣሪ ከሰው ልጅ ጋር ሰውም ከፈጣሪ ጋር ይገናኛል፡፡ ሕዝቡ በነበሩበት ጣዖት የማምለክ እና ስሜትን የመከተል ምስቅልቅል መሀል የተቀደሰውን እና ፍትሀዊ የሆነውን የአምላክ ጽንሰ ሀሳብ መትከል አስችሎታል፡፡ ከሰው ልጅ አቅም በላይ የሆነን ስራ አንድ ሰው እንደዚህ ባለ ቀላል ዘዴ መወጣቱ ከዚህ በፊት ተሞክሮ የማይታወቅ ነገር ነው፡፡ ይህን ስራ ሲሰራ እቅድ አውጪም ሆነ ተግባሪው እራሱ ነበር፡፡ ግዙፍ ፕሮጀክት ላይ የበረሃ ዳርቻ ላይ ከሚኖሩ ጥቂት የምዕመናን እጅ በቀር የሚያግዘው ሠራዊት አልነበረውም፡፡

በመጨረሻም አንድ ሰው እንደዚህ አይነት ግዙፍ እና ቀጣይነት ያለው አብዮት ሲያመጣ ታይቶም ሆነ ተሰምቶ አይታወቅም፡፡ ምክንያቱም ከተመሰረተ ከሁለት አስርት ዓመታት ባነሰ ግዜ ውስጥ ኢስላም በእምነት እና በጦ መሳሪያ የአረቢያን ባህረ ሰላጤ መቆጣጠር ችሎ ነበር፡፡ ከዛም በመቀጠል በአላህ ስም ፐርሺያን፣ ኹራሳንን፣ ማዕከላዊ ኤስያን፣ ምዕራብ ሕንድን፣ ሶርያን፣ ግብፅን፣ ኢትዮጵያን፣ ሰሜን አፍሪካን፣ በሙሉ የሜድትራንያን ባህር አብዛኛውን ደሴቶች፣ ስፔንን እና የተወሰኑ የፈረንሳይን ክፍሎችን ሁሉ ተቆጣጥሩ፡፡

ግዙፍ አላማ፣ ቀላል ግብን ማሳኪያ ዘዴ እና ግሩም ውጤት፡፡ አንድን ሰው ምጡቅ ለማለት የተቀመጡ ሶስት መስፈርቶች እነዚህ ከሆኑ ማን ነው ደፍሮ ከነብዩ ሙሀመድ ጋር በዚህ ማዕረግ ሊፎካከር የሚችለው? ታላቅ የሚባሉት ሰዎች እኮ የፈለሰፉት ወይ መሣሪያ ነው፣ ወይ ህግ ነው አልያም ስርወመንግስት ብቻ ነው፡፡ ማስገኘት የቻሉት ነገር ቢኖር አብዛኛውን ግዜ በአይናቸው እያዩዋቸው የሚፈራርሱ ቁሳዊ መዋቅሮች ናቸው፡፡ ይህ ሰው ግን ያንቀሳቀሰው ሰራዊት፣ ህግጋት፣ ግዛት፣ ህዝብ እና ስርወመንግስት ብቻ አልነበረም፡፡ ነገር ግን ከእነዚህ ጋር በዛን ወቅት የአለምን ሕዝብ አንድ ሦስተኛ ይወክሉ የነበሩትን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን አብሮ አንቀሳቅሷል፡፡ እያንዳንዷ ቃል ህግ በሆነችው መፅሀፍ ተመርኩዞ ሁሉም ቀለም፣ ቋንቋ እና ብሔር የተቀላቀለበት መንፈሳዊ ዜግነት ፈጥሯል፡፡

የዚህ ዜግነት ባለቤት የሚለዩበትን ነገር አሳወቀ፡፡ እሱም በአላህ ላይ ማጋራትን መጥላት እና አንድን እና ብቸኛውን አምላክ መገዛት ነው፡፡ በዚህ መልኩ ከጣኦቶች እና በአላህ ላይ ከማጋራት በተቃራኒ ጎን በቁርጠኝነት በመቆም መስፈርት ምዕመናኖችን መልምሏል፡፡ የምድር 1/3 ነዋሪዎች ሀይማኖቱ ውስጥ መግባት መቻላቸው በእርግጥም ተዓምር ነው፡፡ ወይም ተዓምር ሳይሆን የአዕምሮ ምጥቀት ነው፡፡ በጣኦታት ምስቅልቅል መሀል የአንድ አምላክ ፅንሰ ሀሳብ ማንሳቱ በራሱ ታላቅ ተዓምር ነው፡፡ ይህች ፅንሰ ሀሳብ ከምላሱ ከወጣች በትንሽ ግዜያት ውስጥ ሁሉንም ጣኦት አውድማ እና አንኮታኩታ ከምድር በአንድ ሦስተኛ ክፍል ላይ እሳቷን መለኮስ ችላለች፡፡

ሕይወቱ፣ ስለዓለም ያለው ጭንቀት፣ በሀገሩ ላይ በነበሩ ምስቅልቅል ጥመቶች ላይ የተቀዳጃቸው ድል፣ ከጣኦት አምላኪያን ጋር በነበረው ግጥሚያ ላይ ያሳየው ድፍረት፣ በመካ ውስጥ ለ15 ዓመት በሙሉ ለገጠመው መከራ የመሸከም ጥንካሬው፣ ከሕዝቡ በገጠመው ዘለፋ እና የስም ማጥፋት ዘመቻ ላይ መታገሱ እነዚህ ሁሉ ጥሪውን በማስተላለፍ ላይ ከመዘውተሩ ጋር፣ ከብልሹ ስነምግባር እና ከመሀይማን ተግባር ጋር የነበረው ጦርነት፣ ድል እንደሚያደርግ የነበርው ጥልቅ እምነት፣ በአስቸጋሪ ጊዜያቶች የነበረው እርጋታ፣ በድል ግዜ የነበረው መተናነስ፣ ወደስልጣንና ከብር ሳይሆን ወደ አንድ አቅጣጫ ያተኮረው ምኞቱ፣ የማይቋረጥ የነበረው ፀሎቱ፣ ከአላህ ጋር መነጋገሩ፣ መሞቱ እና ሞትን አሸንፎ ከመነሳቱ ጋር ሁሉም አንድ ላይ ሁነው አስመሳይ እና አታላይ ሰው ፊት እንዳልቆምን እና በማይነቃነቅ እምነት ፊት መቆማችንን ይመሰክራሉ፡፡

እነዚህ ሁሉ መሠረቱን እንዲያቋቁም ሀይል ሰጡት፡፡ እምነቱንም በሁለት መሠረታዊ ነገራቶች ላይ ገነባ፡፡ አንደኛው አላህ አንድ መሆኑ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ቁሳዊ አምላክ አለመሆኑ ነው። በመጀመሪያው መሰረት አላህ ምን እንደሆነ ስናውቅ፤ በሁለተኛው ደግሞ አላህ ምን እንዳልሆነ እንረዳለን፡፡

ፈላስፋ፣ ሕግ አርቃቂ፣ የጦር መሪ፣ ተንታኝ፣ መልዕክተኛ፣ ምክንያታዊውን ሀይማኖት መላሽ፣ የ20 ክፍለ ግዛቶች እና ድንበር የሌለው የምዕመናን ልቦች አስተዳዳሪ፤ ሙሐመድ ማለት ይህ ነው፡፡ የአንድ ሰው ታላቅነት የሚመዘንባቸውን መስፈርቶች በተመለከትን ግዜ እራሳችንን እንጠይቅ ከሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) የበለጠ ታላቅ ሰው እውን አለን?

ያረሱለላህ! እናቴም አባቴም መስዋት ይሁንልህና በዚህች አነስተኛ መፅሀፍ ውስጥ የሚገባህን እንዳልተወጣሁኝ አውቃለሁ። ማንኛውም መፅሀፍ ቢሆን ስለዚያ በመልላኩ ኢጋሪዎችን ያወደመው ታላቅ ነብይ ዘርዝሮ እና ተንትኖ አይጨርስም፡፡ እኔም ይህችን አነስተኛ መጽሀፍ እሳቸው ላይ የተለጠፉ ቅጥፈቶችን አራሚ፤ እሳቸውን ለማወቅ የሚኖርን ጉጉት ጨማሪ፣ ጥሩ ወደ ተባለ ነገር ሁሉ አመላካች እና መጥፎ ከተባለ ነገር ሁሉ አስጠንቃቂ እንድትሆን አላህን እማፀንዋለው፡፡ እሷ ውስጥ ያሉ ንግግሮችም ወደ አላህ ውዴታ እና ወደ ጀነት የሚያዳርሱ እንዲሆኑም ምኞቴ ነው፡፡

አባቶቻችን እና አያቶቻችንን በጭፍን የመከተል ዘመንን በማስረጃ ላይ በተመረኮዘ እምነት እንቀይር፡፡ ስንጀምርም መያዝ እና መቀበል የምንፈልገውን ነገረ ጠንቅቆ በማወቅ እና በጥልቀት በማስብ ይሁን፡፡